አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ-ምረቃ መርሀ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

# በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ

በ

የሺጥላ ምንይልሸዋ

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2000 ዓ.ም.

# በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ


## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድኅረ-ምረቃ መርሀ ግብር


ለአማርኛ ማስተማር (TEAM) ኤም. ኤ. ዲግሪ

በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ ጥናት


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



በ

የሺጥላ ምንይልሸዋ


ሰኔ 2000 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ድኅረ-ምረቃ መርሀ ግብር

# በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ

በ


**የሺጥላ ምንይልሸዋ**


ሰኔ 2000 ዓ.ም.

የፈተና ቦርድ አባላት

| | |
|---|---|
| [illegible] | |
| አማካሪ | ፊርማ |
| ኑሩ መሐመድ (ዶ/ር) | |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |
| [illegible] (ዶ/ር) | |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |

# ማውጫ

ገጽ

ምስጋና ......................................................................i
የሰንጠረዥ ማውጫ ........................................................ii
አጠቃሎ ....................................................................iii

ምዕራፍ አንድ መግቢያ ..........................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ ..........................................................1
1.2 የጥናቱ ዓላማ ........................................................2
1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ..................................................3
1.4 የጥናቱ ክልል ........................................................3
1.5 የጥናቱ ወሰን ........................................................4

ምዕራፍ ሁለት የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ...........................................5

2.1 የንባብ ምንነት ......................................................5
2.1.1 አንብቦ የመረዳት ምንነት ..........................................7
2.1.2 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት ........................................8
2.2. አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ..................................10
2.2.1 ቅድመ ንባብ ደረጃ ..................................................12
2.2.2 የጊዜ ንባብ ደረጃ ..................................................13
2.2.3 ድህረ ንባብ ደረጃ ..................................................14
2.3. የምንባቦች የይዘት ግልፅነትና ተስማሚነት ..............................16
2.4 አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር የሚቀርቡ መልመጃዎች ባህርይ ..........21

ምዕራፍ ሶስት የአጠናን ዘዴ ........................................................ 27

3.1 የት/ቤት፣የተማሪዎችና የመምህራን አመራረጥ ................................ 27

3.1.1. የት/ቤት አመራረጥ ..................................................27

3.1.2. የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ ......................................28

3.1.3. የመምህራን አመራረጥ ..............................................29

3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ............................................ 29

3.2.1. የሰነድ ምርመራ ........................................................30

3.2.2. ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ...............................30

3.2.3. ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ...............................30

3.3 የመረጃ አጠነቃቀርና አተናተን ................................................. 31

ምዕራፍ አራት የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት ................................... 32

4.1. በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኝ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘት ትንተና ............................................................................ 32

4.2. ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና............. 43

4.3. ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ............ 55

4.4. ከሰነድ ምርመራ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና ........................................................ 63

ምእራፍ አምስት ማጠቃለያና አስተያየት ......................................... 68

5.1 ማጠቃለያ ....................................................................... 68

5.2. አስተያየት ....................................................................... 69

ዋቢ ጽሑፎች ........................................................................ 71

አባሪ አንድ ምንባቦቹ ለእይታ ያላቸውን ሁኔታ በተመለከተ...............76

አባሪ ሁለት በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አይነት....................................78
አባሪ ሦስት ለመምህራን የቀረቡ የጽሑፍና የአስተየየት መጠይቆች........79
አባሪ አራት የተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ..................................83

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድርስ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ ከርዕስ ማስተካከል ጀምሮ ያላሰለሰ የሙያ ድጋፍና ምክራቸው ላልተለየኝ አማካሪዬ አቶ ጌታቸው እንዳላማው (ረዳት ፕሮፌሰር) ልባዊ የሆነ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለጥናቱ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን በመሸፈን ለረዳኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ላቅ ያለ ምስጋናዬ ይድረሰው።

መረጃ ለመሰብሰብ ለተባበሩኝ በድሬዳዋና በሐረር ለሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ መምህራንና ተማሪዎች ከፍ ያለ ምስጋና ሳቀርብ፣ በተለይ የተማሪዎችን መጠይቅ በኮምፒዩተር በማሰመታትና በማባዛት ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ የሳቢያን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ በየነ ደገፉና ለአማርኛ ቋንቋ ዲፓርትመንት ተጠሪ መምህር ገበየሁ ምስጋናዬ የላቀ ነው።

የሞራል ድጋፉ ያልተለየኝ አንተነህ የሺጥላ፣ የኔ ድጋፍ በከፍተኛ ደረጃ የሚያስፈልጋቸው ከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የነበሩት እንግዳትና ፀደኒያ፣አሁንም ያሉት እፀገነትና መቅደላዊት የሺጥላ፣ እንዲሁም የአባት ፍቅር በሚያስፈልገው ወቅት የተለየሁት ናኦድ የሺጥላ ይጎድልብናል፣ ይቸግረናል ሳይሉ እንድማር በመገፋፋት፣ ሞራል በመስጠት ለዚህ እንድበቃ ያደረጉኝ ልጆቼ ባለውለታዎቼ ናቸውና ምስጋና ይገባቸዋል።

ከሁሉም በላይ ሀላፊነቱን በሙሉ ተሸክማ እኔንም ሆነ ልጆቼን ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳትል ለዚህ ደረጃ ማብቃቱ ሳያንሳት ከመምህራን መጠይቅ ጀምሮ ይህንን የጥናት ወረቀት ረቂቅ በኮምፒዩተር በመምታት፣ በማንኛውም ሁኔታ ድጋፏ ያልተለየኝ ባለቤቴ ወ/ሮ ንግስት ገብረየስ በኔ የከፍተኛ ትምህረት ሕይወት ውስጥ ትልቁን ስፍራ ትይዛለች። ስለዚህ ማመስገኑ ቀረቤታዬን የሚቀንስብኝ ስለመሰለኝ ዝምታን መርጫለሁ።

በተጨማሪም እህቶቼ ሠናይትና ሸዋነሰሽ ገብረየስ፣ ወ/ሮ እቴቱ በቀለና ወንድሜ አቶ ምትኩ ገ/ማሪያም በሞራልና አስፈላጊ በሆኑ ነገሮች ሁሉ ድጋፋቸው ስላልተለኝ ሳላመሰግናቸው አላልፍም።

በመጨረሻም ጥናታዊ ጽሑፌን በኮምፒዩተር በማስተካከልና በመጻፍ የረዳችኝ እህቴ ሠላማዊት ተማም፣ መጠይቆችን በማስሞላት፣ የሞራል ድጋፍ በመስጠት ያልተለየኝ ወንድሜ ኒኒስ ምሳ አያልቅበት እንዲሁም የሚያስፈልጉኝን መረጃ መጻሕፍት አፈላልገው በማቅረብ በተለያየ መንገድ ድጋፋቸው ያልተለየኝ ጓደኞቼ ሙክሚል በድሩና ረምዚ አብዱረህማን፣ በተጨማሪም በሐሳብና በምክር ድጋፋቸውን የቸሩኝ ጓደኞቼ ተስፋ አከለ፣ አንለይ አዳነ፣ ያየህ ንጉሴና ጌታቸው ሲበን ባለውለታዎቼ ናቸው።

## የሰንጠረዥ ማውጫ


ገጽ

ሠንጠረዥ 1 በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች አይነት ....................................................................33

ሠንጠረዥ 2 በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪየ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች የወጡ መልመጃዎች መጠን ........................ ...............41

ሠንጠረዥ 3 በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች........42

ሠንጠረዥ 4 መጠይቁን የሞሉት መምህራን ዳራዊ ሁኔታ---------------------------.43

ሠንጠረዥ 5 ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸውን ተስማሚነት በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች-----------------------------------------------------------------------44

ሠንጠረዥ 6 ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፣ ዕድሜና አካባቢ ያላቸውን ተስማሚነት በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች------------------------------------------45

ሠንጠረዥ 7 የምንባቦችን ይዘቶች ግልጽነት አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች-------48

ሠንጠረዥ8 የምንባቦችን ይዘቶች ተስማሚነት በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች --49

ሠንጠረዥ 9 የምንባቦቹን ይዘቶች የተውጣጡ መሆን አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች----------------------------------------------------------------------51

ሠንጠረዥ10 በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ አንብቦ የመረዳትን መልመጃዎች በተመለከተ --------------------------------------52

ሠንጠረዥ 11 አንብቦ የመረዳት ጥያቄ አይነቶችና አቀራረብ...............................53

ሠንጠረዥ 12 ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸውን ተስማሚነት በተመለከተ ---------------------------------------------------------------55

ሠንጠረዥ13 ምንባቦቹ ለተማሪዎች ችሎታ፣ ዕድሜና አካባቢ ያላቸውን ተስማሚነት በተመለከተ ---------------------------------------------------------------57

ሠንጠረዥ14 የምንባቦቹን ይዘቶችና ግልጽነት በተመለከተ----------------------------58

ሠንጠረዥ15 የምንባቦቹን ተስማሚነት በተመለከተ-----------------------------------59

ሠንጠረዥ16 ምንባቦቹ ከልዩ ልዩ ጽሑፎች የተውጣጡ መሆናቸውን በተመለከተ-----59

ሠንጠረዥ17 በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ አንብቦ የመረዳትን መልመጃዎችን በተመለከተ------------------------------------61

# አጠቃሎ (Abstract)

ይህ ጥናት የንባብ ትምህርት ዋነኛ አካል የሆነው አንብቦ የመረዳት ትምህርት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን በመፈተሽ ላይ የሚያተኩር ነው። ምንባቦቹ የተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላትና አለማሟላታቸውን፣ የምንባቦቹ ይዘቶች ለተማሪዎቹ ያላቸውን ግልጽነትና ተስማሚነት፣ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ባህርይ ወዘተ. ላይ ትኩረት ተደርጓል። ጥናቱ ይዞት የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ የሰነድ ምርመራ፣ የጽሑፍ መጠይቅና የመምህራን አስተያየት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሲሆኑ፣ ገላጭ የትንተና ዘዴ በዋነኛነት ሥራ ላይ ውሏል። በነዚህ መሳሪያዎች አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው እንደሚያመለክቱት በመጽሐፉ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን የሚያሳዩ በርካታ ጠንካራ ጎኖች ያሉትን ያህል ሊሻሻሉ የሚገባቸው ጥቂት ክፍሎችም አሉት። ለዚህም ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት የሚስማሙ መሆናቸው፣ ምንባቦቹ ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች የተውጣጡ፣ እውናዊ (Authentic) መሆናቸው፣ መልመጃዎቹ ቅድመንባብ የመወያያ ጥያቄዎችን ለማገናዘብ የሚያስችሉ፣ መልመጃዎቹ የምንባቦቹን የተለያዩ ክፍሎች የዳሰሱ መሆናቸው፣ ትምህርቱ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን ከሚያሳዩ ጠንካራ ጎኖች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። በሌላ በኩል የትዕዛዞችና የመልመጃዎች አቀራረብ ያውነት (consistency) አለመኖር፣ ለአንብቦ መረዳት መዳበር እገዛ የሚያደርጉ እንደ ግምገማ፣ በአረፍተ ነገሮች መካከል ስለሉ ዝምድናዎች የሚጠይቁ ጥያቄዎች አለመካተት ደካማ ጎኖች ናቸው። በተጨማሪም ለአንብቦ መረዳት ትምህርት መዳበር የትምህርቱ በተገቢ መንገድ መቅረብ ብቻ ፋይዳ እንደሌለውና ሌሎች ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችም መኖራቸውን የመምህራን አስተያየት ይጠቁማል። በመጨረሻም በጥናቱ የተገኙትን ውጤቶች በመንተራስ የመፍትሔ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ዛሬ በአገራችን ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የሚሰጠው ራሱን የቻለ አላማ ኖሮት ሲሆን፣ በአላማው ላይ ከሚነሱት ዋነኛ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ <<የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር>> የሚል ነው። የታሰበው አላማ ከግብ ሊደርስ የሚችለው የልጆቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታና ንዐማን ክሂሎችን ለማዳበር ያግዛሉ ተብለው የታሰቡ ይዘቶች በተገቢው መንገድ በመጽሐፉ ወስጥ ተደራጅተው ሲቀርቡ ነው። ተማሪዎቹ በታቀደው ይዘት ተጠቅመው በተደጋጋሚ መለማመድ ሲችሉ፣ የታሰበው ግብ ሊገኝ ይችላል።

ንባብ ደግሞ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ይበልጥ አስፈላጊና መሰረታዊ ከሆኑት ክሂሎች ውስጥ አንዱ መሆኑን McDonough and Shaw ( 1993 ፣6) ና Lindsay and knight ( 2006፣ 70-71) አመልክተዋል። እንዲሁም በ Nuttall (1982) እምነት ማንበብ ያስመረዳት ዋጋ የለውም።

ተማሪዎች በአብዛኛው የሚማሩት ከንባብ ሂደት በሚገኝ ግንዛቤ በመሆኑ የንባብ ትምህርት መቅረቡ ለሕይወታቸው አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን አንብበው እንዲረዱ ያግዛቸዋል። ይህም የብዙ መምህራን እምነት ነው (Silberstain 1994)። እንደነ Hutchinson and Torres (1994 ፣315) ከሆነ ተማሪዎች በትምህርት ሂደት ውይይት ሲያካሂዱ፣ መልመጃዎችን ሲሰሩ፣ የቋንቋ ተግባራትን ሲያከናውኑ፣ ሲያጠኑ፣ የቤት ስራ ሲሰሩ ወዘተ. በመማሪያ መፃሪያው በሚገባ እንዲጠቀሙበትም የንባብ መማሪያ መፃሪያዎች ሲዘጋጁ የተማሪውን ፍላጎት፣ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ወዘተ. ማገናዘብ አስፈላጊ ነው። ይህ ካልተሟላ በመምህሩም ሆነ በተማሪው የማስተማር መማር ሂደት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅእኖ በቀላሉ የሚገመት አይደለም (ኦስም 1995፣ Aebersold and Field 1997 ፡ ና Day and Bamford 1998)።

በሌላም በኩል Cunningsworth ( 1995፣ 73) ተማሪዎች ጥሩ (ተስማሚ) የመማሪያ መጽሐፍ ማግኘት ከቻሉ ከት/ቤት ውጭም ንባብን በራሳቸው ሲያዳብሩት እንደሚችሉ፣ ለዚህም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ተማሪውን የሚያስደስቱ፣ የክፍል ደረጃውን

ከግንዛቤ የሚያስገቡና በተቻለ መጠን እውናዊ (Authentic) የሆኑ፣ የንባቡን ሂደት የሚያግዙ ምክንያታዊ ክንዋኔዎችን (Activities) ያካተቱና በደንብ የቀረቡ መሆን አለባቸው።

ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አላማዎች አንዱ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ይሁን እንጂ ወላጆችና መምህራን ተማሪዎች የቀረቡላቸውን የትምህርት ይዘቶች አንብበው የመረዳት ችሎታቸው ዝቅተኛ መሆኑን ሲገልጹ ይሰማሉ። ለዚህ በምክንያትነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ተላውጦዎች ውስጥ አንዱ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ነው። አንዳንድ አንብቦ የመረዳት ችሎታን አስመልክተው የተካሄዱ ጥናቶችም የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑን፣ ለዚህ ድክመትም በምክንያትነት ከጠቀሷቸው ውስጥ አንዱ የመማሪያው መጽሐፍ ነው። ለምሣሌ ፡- ተሾመ ፎርሲዶ በ 1997 የ10ኛ ክፍል ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና ፍጥነት ሲመረምሩ በተጓዳኝ በመጽሐፉ ውስጥ ስለሚገኙ ምንባቦች ገጽ -68- ላይ «በአስረኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፍሐፍ ውስጥ የንባብ ክሂልን ለማዳበር የቀረቡት ምንባቦች ማራኪነት (ሳቢነት) የሚጎድላቸው፣ በአብዛኛው ከረጅም ልቦለድ ጽሑፍ ተቀንጭበው የተወሰዱና የአሰልችነት ባሕሪ ስላላቸው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ጉድለት አለባቸው» ብለዋል።

ይህም ሃሳብ አጥኚው ከነበረው ልምድና በየኢጋጣሚው ስለልጆቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከሚሰማው ጋር ተዳምሮ በ9ኛው ክፍል መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብስ ምን ይመስላል? እንዲል አድርጎታል። በዚህም በዘጠነኛው ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ለመፈተሽ ተነሳስቷል። በሂደቱም የሚከተሉትን ይመረምራል።

ሀ. ምንባቦቹ የተማሪዎችን ፍላጎት ያሟላሉ ወይስ አያሟሉም?

ለ. ምንባቦቹ ከችሎታቸው፣ ከእድሜያቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ይጣጣማሉ ወይስ አይጣጣሙም?

ሐ. የምንባቦቹ ይዘቶች ለተማሪዎቹ ምን ያህል ግልፅና ተስማሚ ናቸው ?

መ. ምንባቦቹ የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን (genres) አካተዋል?

ሠ. አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዙ መንገዶች ቀርበዋል? የሚሉትን ይፈትሻል።

## 1.2 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን መፈተሽ ነው። ዝርዝር አላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

1. የምንባቦቹ አመራረጥ የተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላትና አለማሟላታቸውን ማየት፣
2. ምንባቦቹ ከችሎታቸው፣ ከእድሜያቸውና ከአካባቢያቸው ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን መመርመር፣
3. የምንባቦቹ ይዘቶች ለተማሪዎቹ ያላቸውን ግልፅነትና ተስማሚነት ማወቅ፣
4. ምንባቦቹ የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን (genres) ማካተታቸውን መመልከት፣
5. አንብቦ የመረዳት ትምህርት (መልመጃ) አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን መፈተሽ ነው።

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ለማዳበር የበኩሉን እገዛ ያደርጋል ተብሎ ይታመናል።በዚህ መሰረትም:-

1. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ምንባቦች የተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላትና አለማሟላታቸውን፣ ከችሎታቸው፣ ከእድሜያቸውና ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸውን ስምሙነት ለስርአተ ትምህርት አዘጋጆች ጥቆማ ይሰጣል።
2. የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መሳሪያዎችን ለሚያሻሽሉና ለሚያዘጋጁ ወገኖች የበኩሉን ድጋፍ ያደርጋል።
3. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያለው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ተገቢ ስለመሆንና አለመሆን ለመምህራን መረጃ ይሰጣል።
4. ሌሎች ተመሳሳይ ጥናቶችን ለሚያካሂዱ አጥኚዎች የመነሻ ሐሳብ በመስጠት የበኩሉን እገዛ ያደርጋል።

## 1.4 የጥናቱ ክልል

ይህ ጥናት ተሻሽሎ በ1997 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለውን አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ይፈትሻል:: ለዚህም ዋነኛው መረጃ የሚሰበስበው ከሰነድ ምርመራ ሲሆን፣ በደጋፊነትም ከመምህራንና ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ እንዲሁም ከመምህራን አስተያየት መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል::

ሌላው ደግሞ አጥኚው ጥናቱን በድሬዳዋና በሐረር ከተማ በሚገኙ ት/ቤቶች ያደረገው የአካባቢው መምህራንና ተማሪዎች ተደጋጋሚ የሆነ መረጃ በመስጠት ያልተሰላቹና አጥኚው በሚገባ የሚያውቀው አካባቢ በመሆኑ ለመረጃ መሰብሰብ ከፍተኛ ትብብር የሚገኝ ስለሆነ ባለው አመችነት ነው::

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦችና አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ አንብቦ የመረዳት ትምህርትን ተግባራዊ ለማድረግ ማገዛቸውን መፈተሽ፣ ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ችሎታ፣ እድሜና አካባቢ.... ጋር ያላቸውን ስምምነት፣ የምንባቦቹ ይዘቶች ለተማሪዎቹ ምን ያህል ግልፅና ተስማሚ እንደሆኑና እንዳልሆኑ እንዲሁም አንብቦ የመረዳትን መልመጃዎች ባህርይ ማየት ነው::

# ምዕራፍ ሁለት
# የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

## 2.1 የንባብ ምንነት

ንባብን በአንድ ቃል መግለፅ እንደማይቻል ምሁራን ይናገራሉ:: ስለሆነም ንባብ ምንድ ነው? ለሚለው ጥያቄ የተለያየ ምላሽ ለመስጠት ይሞክራሉ:: Davies(1995፣1) "ንባብ ግላዊ ነው:: ንባብ በጊዜና በቦታ ተወስኖ የሚገኝን የአንድ ፀሐፊ መልእክት በመከተል ምላሽ ለመስጠት የምንሞክርበት አእምሮታዊ ተግባር ነው:: ግላዊ ተግባር ስለሆነም የአነባበቡን ሂደትና ለፀሐፊውም የሚሰጠውን ምላሽ በቀጥታ ላናስተውለው እንችላለን" ይላሉ:: ከዚህም ንባብ አንድ ሰው በግሉ የሚያካሒደውና አእምሯዊ ተግባር መሆኑን እንረዳለን::

በሌላም በኩል ንባብ ማለት የተጻፈን ጽሑፍ ወይም በጽሑፍ የሚገኙ ምልክቶችን የማየትና የመረዳት ሂደት ሲሆን፣ እነዚህ ምልክቶችም ተቀናጅተው ና ተደራጅተው ሰፋፊ አምዶችን ይመሰርታሉ (Williams 1984፣2):: እንደ Wallace (1992፣4) አገላለጽ ደግሞ ንባብ ከአንድ ጽሑፍ ጋር ተግባቦትን ለመፍጠር እንደ መተርጎሚያ መንገድ የምንገለገልበት ነው:: እንዲሁም Nuttall (1982 ፣2) ንባብ:-

ሀ. ፊደላትን መለየት፣ መቁጠር ፣መነጠል

ለ. ድምፅን ማፍለቅ፣ ንበት፣ መናገር ወዘተ.

ሐ. አንድን ጽሑፍ መረዳት፣ ትርጉም መጨበጥ ወዘተ. ነው::

ከዚህም ንባብ በተለያየ መንገድ ሊገለፅ እንደሚችል መገንዘብ አያዳግትም::

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በተጨማሪም Harmer (1991፣17-18፣183-184)፣ Sheng (2000) ንባብ ከተቀባይ ክሂሎች (receptive skills) የሚካተት ሲሆን፣ ከምናነበው ጽሑፍ ውስጥ ቁምነገሩን ነቅሶ ማወጣትን፣ የምንባቡን ዝርዝር ሐሳብ መረዳትን አንብቦ መረጃን መቀበልና ማስተላለፍ፣ የቃላትን አውዳዊ ፍች መረዳትን ወዘተ አጠቃልሎ የያዘ መሆኑን ያመለክታሉ:: ይህም ንባብ በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የቀረበን ቁምነገር አንብቦ ለመረዳት የሚደረግን ጥረት ያመለክታል::

እንዲሁም Grellet (1981፣8) “ንባብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከር ና ራስን ጥያቄ መጠየቅ የሚለትን የሚያጠቃልል ንቁ ተሳትፎ የሚያሻው ሂደት ነው።” ከዚህም ንባብ አንባቢ ከምንባቡ አውድ በመነሳት የአዳዲስ ቃላትን ፍችዎች የሚገምትበት ገና ከመነሻው ባገኘው መረጃ ላይ በመመርኮዝ የምንባቡን ዋና ይዘትና ወደፊት ምን እንደሚገጥመው የሚተነብይበት፣ የሚያነበውን ጽሑፍ መረዳትና አለመረዳቱን ራሱን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያመሳክርበት ሂደት መሆኑን እንረዳለን:: በሌላም በኩል የተለያዩ ምንባቦችን ሲያነብ የተለያዩ ችሎታዎችንና ስልቶችን መጠቀም እንዳለበት እንገነዘባለን::

ንባብ የአንባቢውን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ፣ ከአንድ አእምሮ ወደ ሌላው አእምሮ፣ ከጸሐፊው ወደ አንባቢው መልእክት የሚተላለፍበት ዘዴ ነው:: በዚህ ወቅትም ጥሩ የሆነ መግባባትና ግንዛቤ እንዲፈጠር ጸሐፊው፣ አንባቢውና ጽሑፉ እያንዳንዳቸው የራሳቸውን አስተዋጽኦዎች ያበረክታሉ (Nuttall : 1982፣18):: ይኸውም አንድ ጽሑፍ እንዲነበብ የሚያስፍራቸው ሐሳቦች አንባቢው የሚያነበውን ሐሳብ ለመረዳት ያለው የችሎታ ብቃትና ፍላጎት፣ የጽሑፉ ግልጽነት፣ የአጻጻፍ ሁኔታ ወዘተ. የየራሳቸው ፋይዳ አላቸው::

ንባብ ግላዊ (ተናጠላዊ) ተግባር ስለሆነ በዝምታ መነበብ አለበት:: ቀጥሎም ተማሪዎቹ ባነበቡት ላይ ተመስርተው ለቀረቡት ተግባራት መልስ ሲሰጡ መወያየት ይችላሉ (Atkins et-al 1995፣55):: ንባብ ውስብስብና ቅንጅት ያላቸው ብዙ ንኡሳን ሂደቶችን ያካተተ ነው በማለት ሊበየን ይችላል (Gough and Peterson 1996፣1):: ቀጥሎም ንባብ ፊደላትን በመለየት ይጀምራል:: የአይን እንቅስቃሴው ወደ ሌሎች ፊደላት ስለሚያመራ በመቀጠል የቃላት ልየታ(words recognition) ይከሰታል:: ተራ የቃላት ልየታ በቂ ስለማይሆን ሂደቱ ወደ ቃላት ፍች መወሰን ያመራል:: የቃላት ፍች አሻሚ ስለሆነ አንባቢ አሻሚነትን ለማስወገድ ይጥራል:: የእያንዳንዱ ቃል ተገቢ ፍች ከተለየ በኋላ ቃላቱን ያቀናጃቸዋል:: ከዚህ በኋላ የዓረፍተ ነገሩን ፍች ለመሰወን የአንባቢው ቀደምት እውቀት ታክሎበት ከቀዳሚዎቹ አረፍተ ነገሮች ፍች ጋር ዝምድና እየተፈጠረ አንብቦ መረዳት ይከሰታል:: ከዚህ የንባብ ሂደትም አንብቦ መረዳት አንዱና ዋናው የንባብ ክፍል እንደሆነ እንረዳለን::

እንደ Nuttall (2000፣4) አገላለጽ ንባብ ጸሐፊው በሥራው ውስጥ ያስፈረውን ቁምነገር ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው:: ተደራሲው በንባብ ሂደት የጽሑፉን ፍሬ ሐሳብ ለመረዳትና አስፈላጊ መረጃን ከውስጥ ለይቶ ለማውጣት የጸሐፊውን ሐሳብ ይመረምራል:: ስለዚህ ንባብ የሌሎችን ሐሣብ ለመረዳት እንዲሁም ለመግባባት አላማና ሂደት ወዘተ. የምንጠቀምበት ተግባር ነው:: ይህንኑ ሐሣብ David(2005፣1) ያጠናክሩታል::

### 2.1.1 አንብቦ የመረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት የሚፈለገውን መረጃ ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ ፈልቅቆ ማውጣትን የሚይዝ ጽሑፍን የመገንዘብ ሂደት ነው። አንባቢው በተገቢው ፍጥነት የሚፈለገውን መረጃ የሚያወጣበት የማይፈልገውንም እያበጠረ የሚለይበትና ተራ ያልሆነ ጥልቅ ግንዛቤ የሚያመለክትበት ነው ( Smith 1985፣14 ፣ አለም 1995 ፣ 11፣ Williams 1990፣3):: እንደ Greenwood(1981፣89) አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት መገንዘብ ነው። በአንድ ጽሑፍ ውስጥ ያለን መልእክት ለመረዳት ታዲያ የእያንዳንዱን ቃል ፍች ማወቅ የግድ አይደለም። በጽሑፉ ውስጥ በግልጽ የተቀመጠው መልእክትና መልእክቱን ለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር ጉዳዮች መረዳት ግን አስፈላጊ ነው። ይህም ሲባል አንባቢ በግልጽ በተቀመጠው መልእክት ላይ ብቻ ተወስኖ መቅረት አለበት ማለት ሳይሆን፣ በግልጽ የተቀመጠውን መልእክት መነሻ በማድረግ፣ በመመርመር የሚደርስበትን ድብቅ መልእክትም መረዳት ይጠበቅበታል። በዚህ ወቅትም በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙትን አያያዦች አገባብ አገልግሎትና ፍች መረዳት የግድ ነው። በተጨማሪም የምንባቡን ቅደም ተከተላዊ የሐሳብ አገላለጽ የጽሑፉ የተለያዩ እንቀጾች ያላቸውን የርስ በርስ ትስስር መረዳት ተገቢ ነው።

አንብቦ መረዳት የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ የሐሣብ አገላለጽ፣ አንዱ አረፍተነገር ከሌላኛውና ከተከታዩ ጋር ያለውን የሐሣብ ግንኙነትና ግጥምጥምነት የሚፈጥሩ አያያዦች የጸሐፊው ሐሣብ የሚገፀባረቅባቸው በመሆናቸው ሊተኮርባቸው የሚገቡ ናቸው (Nuttal 2000፣28):: በእርግጥ አንብቦ የመረዳት አንብቦ መረዳት አንድ ጽሑፍ የያዘውን መረጃ መገንዘብ ነው። በእርግጥ አንብቦ የመረዳት ደረጃ ሊለይ ይችላል። ይህም ከሚነበበው ነገር፣ ከሚነበብበት አላማ፣ ከአነባበብ ዘዴው መለያየት ሊከሰት ይችላል። ለምሳሌ በአንድ ስሌዳ ላይ የተለጠፈ ማስታወቂያና በአንድ መጽሔት ላይ የታተመ ሳይንሳዊ ጥናት በተመሳሳይ መንገድ አይነበብም። የማስታወቂያው ፍሬ ነገር በገረፍታ ንባብ ሊደርስበት ሲቻል፣ የሳይንሳዊ ጥናቱን ቁም ነገር ለመረዳት ግን ትኩረት ያልተለየው ጥልቅ ንባብ ያስፈልጋል (Grellet 1981፣ 3-4)::

አንብቦ መረዳት ማለት ፍች ማግኘት ማለት ነው። አንብቦ መረዳት የሚለው ቀጥተኛ ፍች አንብቦ መረዳት ጸሐፊው በሕትመት ላይ ያዋላቸውን ፍች በእጁ ላይ ማያያዝ ማለት ነው። በሌላም በኩል ማገኛ እነዚ ምልክቶች በአእምሮ ውስጥ ማያያዝና ማሰላሰል ሊሆን ይችላል። በሌላም በኩል ማግኛ ወ-ም አላማ ያለው አንባቢ የሚያከናውነው ከምንባቡ ፍችን፣ ሐሳብንና መረጃን ማግኘትና ማውጣትን ያካትታል።

ሌላው Smith (1985፣124) አንብቦ መረዳት አንባቢ ይዞት ለሚነሳ ጥያቄ መልስ ማግኘት ማለት ነው። የሚነበብን ጽሑፍ አስመልክቶ ጥያቄ መጠየቅ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ባሕሪ ነው። አንባቢ ለጠየቀው ጥያቄ መልስ አገኘ ማለት በአንባቢውና በጸሐፊው መካከል ተግባቦት መኖሩን ያሳያል። በጽሑፉና በአንባቢው መካከል ተግባቦት አለ ማለት የሚቻለውም መረዳት ሲኖር ነው። ስለሆነም አንብቦ መረዳትንና ተግባቦትን መለያየት አይቻልም ማለት ነው። ባጭሩ አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚፈለገውን መረጃ ለይቶ ማውጣት መቻል ነው ልንለው እንችላለን።

አንብቦ መረዳትን በሁለት ከፍሎ መመልከት ይቻላል። እንደ Grellet (1981፣5) ና Sheng (2000፣ 13-15) አገላለጽ አንደኛው በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የሰፈሩ ጉዳዮችን መገንዘብ ነው፣ በስሩም በጽሑፉ ውስጥ የቀረቡትን ዋና ዋና ሐሣቦች መገንዘብ ፣ በግልጽ የሚታዩ ሁኔታዎችን፣ ክስተቶችን፣ ድርጊቶችን ወዘተ. ቅደም ተከተል ማስታወስ፣ ግልጽ የሆኑ አንድነቶችንና ልዩነቶችን መለየት፣ የምክንያትንና የውጤትን መሰናሰል ማስታወስ ወዘተ. ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎቹ ተጠየቃዊ እውቀትንና ግምትን በመጠቀም በጽሑፉ ውስጥ በግልፅ ያልሰፈሩ ሐሣቦችን አንብበው የሚረዱበትን ሁኔታ ይመለከታል። ይህም ካሉት መረጃዎች በመነሳት የምንባቡን ጭብጥ መለየት፣ ደጋፊ ሐሳቦችን ለይቶ ማወቅ፣ ከምክንያትና ከውጤት ጥብቅ ትስስር የተነሳ ቀጣዩን ነገር መገመት፣ በምንባቡ ውስጥ በይፋ የሰፈረን ፍንጭ በመጠቀም የገጸ ባሕሪያትን ባሕሪይ መገንዘብና የደራሲውን የቋንቋ አጠቃቀም መረዳትን ያካትታል።

እስከ አሁን ከቀረቡት ሐሣቦች መረዳት እንደሚቻለው አንብቦ መረዳት በአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ ቃላትን ከመገንዘብ ባሻገር ጠቃሚና አዳዲስ መረጃዎችን ለቅሞ ለማውጣት የሚያስችል ሂደትና የማንፈልገውን ደግሞ የምንተውበትን ሁኔታ ያጠቃልላል።

## 2.1.2 የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት

ንባብ የሰው ልጅ በጊዜና በቦታ ርቀት ምክንያት ሊያጣቸው የነበሩትን ነገሮች እንዲያገኝ በማድረግ ከፍተኛ አገልግሎት ከሚሰጡት የመገናኛና የመግባቢያ ዘዴዎች አንዱ ነው። ንባብ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ያለውን ስፍራ ተስፋዬ (1981፣60) «ማንበብ በተለይ ባሁኑ በሰለጠነው ዘመን አስፈላጊ ከሚባሉት ሙያዎች ውስጥ የሚደመር ነው። ማንበብ እውቀት የማግኛ መንገድ ብቻ ሳይሆን እንደ ዋና፣ ኳስ ጨዋታ፣ ሽርሽርና እንደ አደን ሁሉ መዝናኛ ሆንዋል» በማለት ይገልጻሉ።

አንባቢያን ካሉት የመረጃ ምንጮች መካከል እደፍላጎታቸው እየመረጡ ንባብን ለራሳቸው ጥቅም ሊያውሉ ይችላሉ:: ለምሣሌ ዛሬ በአለም ላይ ከሚፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችና እወቀቶች ጋር ለመተዋወቅና ራስን ለማዝናናት፣ በዓለም ላይ ያሉ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ለማወቅ ወዘተ. ንባብ ከፍተኛ አገልግሎት አለው:: የንባብ ትምህርት የተማሪውን የንባብ ችሎታ ለማዳበር፣ አንብቦ ጠቃሚና የማይጠቅመውን ለይቶ እንዲረዳ፣ የስነጽሑፍ ችሎታውን ለማሳደግ፣ ታሪክ እንዲያውቅ፣ ለጠቅላላ እውቀት፣ አእምሯዊ ብቃት ለማጎልበት ወዘተ. የመሳሰሉ በርካታ ጥቅሞች አሉት( Bright 1981፣ 52):: ሰዎች አንድን ጽሑፍ የሚያነቡት አንድ የሚጠቅም ነገር፣ መረጃ ወይም ደስታ ለማግኘት ነው:: በመጀመሪያ አላማዬ ብለው ያቀዱትንና ያሰቡትን ነገር ለማግኘት ሲሉ ያነባሉ (Nuttall 1982፣3):: እንደ Grellet (1981፣6) ከሆነ ደግሞ ንባብ:-

ሀ. ለሕይወት ወይም ለመኖር / ለሕልውና/

ለ. ለደስታ

ሐ. ለመማር ያስፈልጋል በማለት አስፍረዋል:: ከዚህም ንባብ የሰዎችን ሕይወት ለመምራት አላማ ተነድፎለት ሊከናወን የሚገባ አስፈላጊ ተግባር መሆኑን እንረዳለን::

አንድን ጽሑፍ አንብቦ መልእክቱን የመረዳት ችሎታን ለማዳበር፣ በማንበብ አጠቃላይ እወቀትን ለመገብየት፣ ከተለያዩ የንባብ ባሕሪያት ጋር ለመተዋወቅና ሂሳዊ የንባብ ችሎታን ለማጎልበት የንባብ ትምህርት አስፈላጊ ነው (Williams 1990፣19ና Grant 1990፣60 )::በሌላም በኩል የንባብ ትምህርት ተማሪዎች ንባብን እንዲማሩ፣ አንበበው ተፈላጊ መረጃን ማውጣት እንዲችሉ፣ ለመዝናናት ሲሉ እንዲያነቡ ለማድረግ አስፈላጊ እንደ ሆነ በመግለጽ Harris and Sipay ( 1990፣95-96)ቀጥለው እነዚህን ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግም የንባብ ትምህርቱ ሦስት የንባብ አይነቶችንና ተግባራትን ማጠቃለል እንዳለበት አመልክተው ቀጣዮቹን በዝርዝር ያቀርባሉ:::

1. እድገታዊ ንባብ:- ይህ ዓይነቱ ንባብ የንባብ ክሂሎችንና ስልቶችን ለማዳበር የሚያስችሉ ተግባራትን የሚያካትት ነው::
2. አገልግሎታዊ ንባብ:- ይህ ደግሞ መረጃዎችን ማውጣት ዋና አላማቸው ያደረጉ ንባቦችን ሁሉ ይመለከታል::
3. የመዝናናት ንባብ:- መዝናናትን ደስታን መጎናጸፍና መደነቅን ዋና አላማዎቻቸው የሚያደርጉ ተግባራትን የሚያካትት ንባብ ነው:: የተግባራቱ አላማ የንባብ ዝንባሌን

ለማሳየት፣ የንባብ ዝንባሌን ለማዳበርና ለማሻሻል ወይም ስነጽሑፋዊ ሂስን ለማጎልበት ሊሆን ይችላል።

ተማሪዎች አንድን ጽሑፍ የሚያነቡት ተፈላጊ መረጃን ለማግኘት፣ ለመደሰት ወይም ለመዝናናት ወዘተ ሊሆን ይችላል። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግም ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የንባብ ዓይነቶችና ተግባራት ያጠቃለለ የንባብ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት አያዳግትም።

የንባብን ትምህርት አስፈላጊነት አስመልክቶ McDonough and Shaw (1993፣102-103) እንደሚከተለው ያቀርባሉ።

- መረጃ ለማግኘት፣
- መመሪያዎችን ተቀብሎ (በስራችን ወይም በእለት ተእለት ሕይወታችን ውስጥ) ለመተግበር፣
- ከጓደኞቻችን ጋር ሐሣብ ለመለዋወጥ፣
- አንድ ነገር መቼና የት እየተከናወነ እንደሆነ ለማወቅ፣
- በጋዜጦች፣ በመጽሔቶች፣ በዘገባዎች የሚቀርቡትን ሐሣቦች ለመረዳትና ለመዝናናት ወይም ለመደሰት ናቸው።

የንባብ ትምህርት የራሱ ግብና ስልት ያለው ሲሆን፣ ራሣቸውን ችለው፣ አቀላጥፈው ማንበብና መረዳት የሚችሉ ተማሪዎችን ለማፍራትም በጣም አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው(Ur 1996፣150)። ንባብ የአንድን ሕብረተሰብ ዳራዊ ሁኔታ ወይም መሰረት፣ የሌሎችን አለማት ሰዎች የአኗኗር ዘዴና ባሕል ለማወቅ ይረዳል። ንባብ ለትምህርት ብቻ ሣይሆን፣ በሕይወታችን ለምንፈፅመው ማንኛውም ተግባር መረጃ በመስጠት ጠቃሚ ሚና ይጫወታል።

## 2.2. አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ

የንባብ ትምህርት ተማሪውን ውጤታማና ራሱን የቻለ አንባቢ እንዲሆን ለማድረግ በሚያግዝበት መንገድና የንባብ ስልቶችን በሚያዳብርበት መልክ መቅረብ አለበት። ውጤታማ ንባብ የስነልቦናዊ ስነልሳንን የንባብ ፅንሰ ሐሣብ መሰረት ማድረግ አለበት። ንባብ የስነ ልቦናዊ ስነልሳን የመተንበይ ሂደት ነው። የንባብ ሂደትም በቋንቋና በአሳቤ መካከል ያለ የመገመት፣ የመምረጥ፣ የመመዘን፣ የማዋሐድና የመተርጎም ኡደታዊ ሂደት ነው በማለት Mei-Yun (1997፣180)Goodman(1982)ን በመጥቀስ ያብራራሉ።

ይህን የሥነ ልቦናዊ ስነልሳን የንባብ ግንዛቤ መሰረት በማድረግ የንባብን ትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ሊያደርግ እንደሚችል ይታመናል:: ምክንያቱም ጥሩ አንባቢ ለንባብ ከቀረበለት ጽሑፍ በመነሣት የጽሑፉን ይዘት የመገመት፣ በንባብ ሂደት ያገኘውን ሐሣብ የመመዘንና ከግምቱ ጋር በማዋሐድ የምንባቡን አጠቃላይ ፍሬ ሐሣብ የመረዳት ባሕርይ ስላለው ግንዛቤውን መሰረት ማድረግ ለትምህርት አቀራረብ የጥሩ አንባቢን ባሕርይ ለማላበስ ያስችላል::

የውጤታማ ንባብ አላማ ጥሩ አንባቢ የሚጠቀምባቸውን የማንበብ ስልቶችና ንዑሳን ክሂሎችን መጠቀም የሚችል ውጤታማ አንባቢ ተማሪ ለማፍራት ስለሆነ፣ Mei-Yun(1997) የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚያግዝ የትምህርት አቀራረብ ባሕሪያትን ማለትም በምክንያት ማንበብ፣ የመገመት ስልትን መጠቀም፣ ያለፈ እውቀትን ለግንዛቤ ማዋልና ንኡሳን ክሂሎችን የመጠቀም ችሎታን መርህ ሊያደርግ ይገባዋል:: ስለዚህ ተማሪዎችን ውጤታማ አንባቢ እንዲሆኑ ለማገዝ፣ የትምህርቱን አቀራረብ በመስተጋብራዊ የንባብ ግንዛቤ ላይ መመስረት የተሻለ ነው::

በመስተጋብራዊ የንባብ ሂደት፣ ማንበብ የቃላት ፍችና ሰዋስዋዊ ስርዓትን ማወቅ ብቻ የሚጠይቅ ሳይሆን፣ ለንባብ ከቀረበው ጽሑፍ ጋር መስተጋብር መፍጠርንም ይጠይቃል (Papalia1987):: ተማሪው ለንባብ ከቀረበለት ጽሑፍ ጋር መስተጋብር መፍጠር አንብቦ የመረዳት ችሎታውን እንዲያዳብር፣ ቀደምት እውቀቱን የመጠቀም ችሎታውንና የመተንበይ ክሂሉን እንዲያጎለብት ማገዝ ያስፈልጋል:: ለዚህም ተገቢ የሆነ የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎችን በማዘጋጀት ተማሪውን ማሳተፍ ይገባል(Johnson 1982) ::

ይህን የንባብ ግንዛቤ መሠረት አድርጎ የሚቀርብ አንብቦ የመረዳት ትምህርት የሚያተኩረው ግንዛቤን ለማዳበር በሚደረግ የንባብ ሂደት ላይ እንጂ ምን ያህል እንደተገነዘቡ በማወቅ ውጤት ላይ አይደለም (Greenwood 1981፣53):: ለመረዳት የሚደረግ የንባብ ሂደት የሚጠይቀውን የንባብ ስልት ለማዳበር የሚያግዝ ወቅታዊ የሆነና ተቀባይነት ያለው የትምህርት አቀራረብ ቅድመ ንባብ፣ ጊዜ ንባብና ድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ያካተተ የትምህርት አቀራረብ እንደሆነ የመስኩ ምሁራን የሚገልጹ ሲሆን፣ በዚህ አቀራረብ ማስተማር ደግሞ የተሻለ ውጤታማ መሆኑን Lindsay and .knight(2006፣74-81) በመግለጽ ሦስቱንም ቀጥሎ በቀረበው መሰረት ይዘረዝሯቸዋል::

በተጨማሪም Grellet (1981)፣ Nuttall (1982)፣ Ur(1996)ይህንኑ ሐሳብ ቀደም ብለው አስረድተዋል::

## 2.2.1 ቅድመ ንባብ ደረጃ

አንድ ምንባብ ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄ ካለው የተማሪዎችን ፍላጎት በማነቃቃት አንብበው የመረዳት ችሎታቸውን እንደሚያዳብር Aebersold and Field (1997፣67-68) በመግለጽ ተማሪዎቹ ስለርእሱ እንዲያስቡ በማድረግ ምንባቡን የማንበብ ፍላጎታቸውን ያነቃቃል፣ አንባቢዎቹ ስለ አንድ የተለየ ርእስ መጠነኛ እውቀት ካገኙ በትክክልና በፍጥነት ማንበብ ይችላሉ:: Day and Bamfored (1998፣76-78)ና Lindsay and knight (2006፣ 74) የሚመረጠው ርእሰ ጉዳይና ቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነሳሳት ወሳኝ ናቸው ::

ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ጠቃሚዎች ናቸው :: ምክንያቱም የተማሪዎቹ ትኩረት ከሚያነቡት ጽሑፍ በሚያገኙት መረጃ ላይ እንዲሆን ያደርጋል:: በቅድመ ንባብ ደረጃ መካሄድ ያለባቸው ክንዋኔዎች አላማዎችም የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት፣ ቀደምት እውቀታቸውን ከጽሑፉ ይዘት ጋር ለማስናሰልና የምንባቡን ፍሬሐሳብ እንዲገምቱ ለማስቻል ነው :: በሌላም በኩል የቅድመ ንባብ ደረጃ ክንዋኔዎች ተማሪዎች ምን እንደሚያነቡ ማስተዋወቂያና ለቀጣዩ ደረጃ (ለጊዜ ንባብ) ተግባራትን ማስተዋወቂያ ነው McDonough and shaw (2003፣ 95) በዚህ ወቅትም መምህራን:-

1. በቅድሚያ የምንባቡን ርእስ ለተማሪዎች ያስተዋውቀሉ፣ ቀጥለውም:-
   - ተማሪዎቹ ምንባቡን ለምን እንደሚያነቡ በማስተዋወቅ የማንበብ ፍላጎታችውን ያነቃቃሉ፣ ያወያያሉ::
   - ለንባብ በቀረበው ርእስ ዙሪያ ያላቸውን ግንዛቤ የሚጠይቁ መነሻ ጥያቄዎች በማቅረብ ቀደምት እውቀታቸውን ከምንባቡ ይዘት ጋር እዲያስተሳስሩ ያነቃቋቸዋል::
   - የምንባቡ ይዘት ስለምን ጉዳይ ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ ያደርጋሉ፣ ይህም ተማሪዎችን በቡድንና በጥንድ በመመደብ በምንባቡ መሠረት ሊመለሱ

የሚችሉ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ፣ አልያም በምንባቡ ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ሐሳቦችን እንዲሰነዝሩ በማድረግ ፣ ከተማሪዎቹ በሚገኘው መልስ ላይ ያወያያሉ::

- የንባብ ሂደትን ሊያደናቅፉ የሚችሉ ቁልፍ ቃላትን በማቅረብ ያወያያሉ ::

2. የምንባቡን አጠቃላይ ሐሳብ ለማወቅ የሚያስችሏቸው ጥያቄዎችን በማቅረብ ያወያዩዋቸዋል:: ምንባቡ ስለምን ጉዳይ እንደሚያወራ ለማወቅ የሚያግዟቸው ጥያቄዎችን በማቅረብና እንዲወያዩ በመገፋፋት ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ::

በአጠቃላይ የቅድመ ንባብ ዋና አላማ ከዋናው የንባብ ሂደት በፊት የተማሪዎቹን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት የክፍል ደረጃቸውንና እድሜያቸውን ከግምት ያስገቡ የንባብ ትምህርት ይዘቶችን በመጠቀም ተማሪዎቹ እንዲሳተፉና ለእለቱ ትምህርት ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ ማገዝ ነው:: የቅድመ ንባብ ክንዋኔዎችና ጥያቄዎች ዋና ትኩረት ግን ልጆቹ የሚያነቡትን ምንባብ በጥሩ ሁኔታ እንዲረዱና ፍላጎታቸው እንዲነቃቃ ለማድረግ ነው::

## 2.2.2 የጊዜ ንባብ ደረጃ

የጊዜ ንባብ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎቹ የምንባቡን መልእክት በአግባቡ እንዲረዱ ማገዝ ነው:: ስለሆነም መምህራን የልጆቹን ችሎታ ለማጎልበት ከቀረበው ምንባብ ውስጥ ፍሬሐሳቡን እንዲገምቱ ፍንጭ የሚያሳዩ መሪ ጥያቄዎችን ከምንባቡ መነበብ በፊት በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ከሚያነቡት ጽሑፍ ጋር እያዛመዱ በጥረታቸው መልእክቱን ፈልፍለው የማውጣት ችሎታቸውን ማዳበር ይችላሉ (Marani 1997 ፣72) ::

የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች መረጃዎችን በጥልቀት ለማግኘት ምቹ ሁኔታዎችን ከመፍጠራቸውም በላይ ቀጥሎ የሚነበበውን ጽሑፍ ይዘት ለመተንበይ፣ አንብቦ የመረዳት ሁኔታ ለመከታተል፣የተነበበውን ከቀጣዩ መረጃ ወይም ከቀደምቱ እውቀት ጋር ለማያያዝ መንገድ ይመራሉ (Zhenyu 1997፣42):: በተለይ ተማሪዎች የሚያነቡበትን ምክንያት እንዲያውቁ የሚረዱ ጥያቄዎች የልጆቹን ትኩረት ለመሳብና አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር ያላቸው ጥቅም ቀላል አይደለም(Harris and Sipay1990፣571) ::

በተጨማሪ Wiener and Bazerrnan( 1997፣13 ) ተማሪዎቹ በጊዜ ንባብ ደረጃ፡-

- በንባብ ሂደት በአእምሯቸው የሚፈጠሩ ሐሳቦችን ፣ ስሜቶችንና ጥያቄዎችን መጻፍ፣
- በምንባቡ ውስጥ በንጽጽር የቀረቡ ሐሳቦችን፣ ሰዎችን፣ ሁኔትዎችን ወዘተ. መለየት፣
- የጸሐፊውን አላማ መለየት፣
- የቃላትን ቀጥተኛና አውዳዊ ፍች መገንዘብ፣
- የጽሑፉን ይዘትና ፍሬ ሐሳብ መረዳት ፣
- ጸሐፊው ለየትኞቹ አንባቢዎች እንደጻፈው መገመት፣
- የጹሑፉን ድምጸት ማወቅና ጸሐፊው በርእሰ ጉዳዩ ላይ ያለውን አመለካከት መገመትና የጹሑፉን መዋቅር ለመገንዘብ መሞከር ያስፈልጋቸዋል፡፡

እንዲሁም በዚህ የንባብ ክሂል ትምህርት አቀራረብ ደረጃ ተማሪዎች በቅድመ ንባብ ወቅት ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ ሊፈልጉ ይችላሉ፡፡

### 2.2.3 ድህረ ንባብ ደረጃ

የድህረ ንባብ ትምህርት አላማ የተነበበውን ምንባብ ማጠቃለልና ከተማሪዎቹ እውቀት፣ዝንባሌና አተያይ ጋር ማዛመድ ነው:: በዚህ ወቅት ተማሪዎች በምንባቡ መስማማት ወይም አለመስማማታቸውን ፣ መውደድ አለመውደዳቸውን አስተያየት በመስጠት የራሳቸውን ፍርድ እንዲሰጡ ይጠየቃሉ:: የድህረ ንባብ ትምህርት ተግባራት ከሚነበበው ምንባብ የሚወጡ ቢሆኑም በቀጥታ ምንባቡን ላይመለከቱም እንደሚችሉ Williams (1990፣39) ያመለክታሉ፡፡

በሌላም በኩልLindsay and knight (2006፣74-81) በድህረ ንባብ ደረጃ የመምህራን ተግባር ምን መሆን እንዳለበት እንደሚከተለው ይገልጻሉ፡፡

1. ከንባብ በኋላ መምህራን ተማሪዎቹ፡-

- ምንባቡ የሚገልጸውን ሐሳብ መረዳት መቻላቸውን ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎችን ያቀርባሉ::
- ምንባቡን እንዲገመግሙ ያበረታታሉ::
- የምንባቡን ሐሳብ ከራሳቸው ገጠመኝ ጋር እንዲያዛምዱ የሚረዱ ክንዋኔዎችን ያቀርባሉ::

2. ተጨማሪ ክንዋኔዎችን ያቀርባሉ::
   - ሌሎች ክሂሎችንም በተቀናጀ መንገድ ለመጠቀም የሚያመቹ ተግባራትን ያዘጋጃሉ::
   - ምንባቡን መነሻ በማድረግ ድርሰት እንዲፅፉ፣ ንግግር እንዲያዘጋጁ፣በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚጋብዙ ተግባራት ይቀርባሉ:: ለዚህም ደግሞ የተዘጋጀው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አመች /ተገቢ/ ሆኖ መገኘት አለበት::

በድህረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው ባነበቡት ጽሑፍ ላይ በጥልቀት ሊወያዩና ሊከራከሩ ይችላሉ::Celce-Murcia (1991፣204) ድህረ ንባብ ደረጃ በእለቱ ለንባብ የቀረበው ጽሑፍና ዋና ዋና ሐሳብ የሚከለስበት ክፍል ነው:: በተጨማሪም ይህ ክፍል ተማሪዎቹ ካነበቡት ምንባብ የተገነዘቡትን በራሳቸው አገላለፅ ለጓደኞቻቸው የሚያቀርቡበትና እርስበርሳቸው እየተጋገዙ ችሎታቸውን የሚያዳብሩበት ነው:: በጊዜ ንባብ ደረጃ ከቀረበው ትምህርት ተነስተው የተወሰኑ አዳዲስና ተያያዥነት ያላቸውን ቁምነገሮች በማካተት ክፍል ውስጥና እቤታቸው ሰፋ ያለ ልምምድ የሚያከናውኑበት ደረጃ ነው:: ይሁን እንጂ መምህሩ ሁልጊዜ እነዚህን ሦስቱንም የንባብ ክፍሎች ማለማመጃ ደረጃዎች ተግባራዊ ማድረግ አለበት ማለት አይደለም:: ከሦስቱ አንዱን ወይም ሁለቱን ማካሄድ የማያስፈልግበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል መዘንጋት የለበትም:: ለምሳሌ:- መምህሩ ተከታታይነት ያለውን በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ምንባብ በተከታታይ ክፍለ ጊዜያት የሚያስተምር ከሆነ፣በቅድመ ንባብ ላይ ብዙ ሰዓት ማጥፋት አያስፈልገውም (Dubin and Bycina1991፣204) ::

እንዲሁም በድህረ ንባብ ደረጃ ተማሪዎች በግላቸው የተሰጣቸውን ጽሑፍ በዝምታ ካነበቡ በኋላ በተናጠል፣በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎችን

እንዲሰሩ ማነቃቃት ይቻላል፣ጥያቄዎችን በህብረት ወይም በቡድን መስራቱ ደግሞ የበለጠ ጥሩ ይሆናል::ምክንያቱም ይህ አይነቱ አካሄድ እያንዳንዱ ተማሪ የመለሰውን መልስ ለምን እንደመረጠው የማስረዳት እድል ይሰጠዋል:: ይህ እድል በመኖሩም ተማሪው በህብረት ስለሚወያይ አንድ ምንባብ አንብቦ ምን ያህል እንደተረዳ ጥያቄዎቹን በሚሰራበት ወቅትም የቱጋ፣ እንዴት እንደተሳሳተ ሊያውቅ ይችላል (Nuttall 2000፣182) ::

ሆኖም ግን ሶስቱም ደረጃዎች ከፍተኛ ፋይዳ ስላላቸው ሊተኮርባቸው እንደሚገባ የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ:: Williams (1990፣ 40) እነዚህን ደረጃዎች ያጠቃለለ የንባብ ትምህርት አቀራረብ ሁለት ዋነኛ ጥቅሞች አሉት:: የመጀመሪያው ተማሪዎቹ ያላቸው የቋንቋና የአካባቢያዊ እውቀት አንብቦ መረዳትን እንዲያፋጥን በማድረግ ተማሪዎቹ እንዲሳተፉ፣ እንዲነቃቁ ያደርጋል:: ሁለተኛው የንባብ ትምህርት ለብቻው ተለይቶ እንዳይሰጥ የጠበቀ የክሂሎች ቅንጅት እንዲኖር ይረዳል::

## 2.3. የምንባቦች የይዘት ግልፅነትና ተስማሚነት

ምንባቦች ልዩ ልዩ የቋንቋ ይዘቶችን ለማቅረብ የሚያገለግሉ በመሆናቸው የታሰቡትን ይዘቶች ለማቅረብ በሚያስችሉ ሁኔታዎች ተመርጠው መደራጀትና መዘጋጀት ይኖርባቸዋል:: የቋንቋ ይዘቶችን ለማስተማር የሚመረጡ ምንባቦች ከጋዜጦች፣ ከመፅሔቶች፣ከማስታወቂያዎች፣ ከዲስኩሮች ወዘተ. የተወሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ:: በውስጣቸውም የሚገኙት ቃላት፣ ሐረጎችና አረፍተ ነገሮች ከሰዋስዋዊ ግድፈት የጸዱ፣ ግልጽና ተነባቢ መሆን አለባቸው (Cunningsworth 1995፣ 57 ፣ Aebersold and Field 1997፣ 47) ::

የሚቀርቡት የምንባብ ትምህርት ይዘቶች በደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች እድሜ፣ ስሜት ወዘተ. የሚስማሙ መሆን አለባቸው:: የማይከብዱ፣ የማይቀሉ፣ ስሜታቸውን የሚማርኩና ፍላጎታቸውን ያገናዘቡ መሆን ይገባቸዋል:: በቃላት፣ በሰዋስው አጠቃቀም ስርዓትን የጠበቁ መሆን አለባቸው:: የተመረጡት ይዘቶች ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች የሚከብዱ ቃላት ወይም የማይገቡ ሐሳቦችን የያዙ ከሆኑ ከነዚህ የሚዘጋጁትን መልመጃዎች

ለመስራት ችግር ይፈጠራል:: በተመሳሳዩ ከችሎታቸው ዝቅ ያሉ ከሆኑም ተማሪዎቹ በምንባቦቹ ተስበው የቋንቋውን ችሎታ ለማዳበር አይነሳሱም:: ስለዚህ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚቀርቡት ምንባቦች የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን ማካተታቸው ለተማሪዎቻችን ችሎታ መዳበር ወሳኝ ነው (Cunningsworth 1995፣ 75)::

በሌላም በኩል አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚቀርቡ ምንባቦች የተውጣጡ ወይም የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን ያካተቱ ቢሆኑ ይመረጣሉ:: ለዚህም:-

> *... እንደ ልብ ወለድ፣ ግጥም ወዘተ. የመሳሰሉት ኪናዊ ስራዎች የሚነበቡት ራስን ለማስደሰትና ለማዝናናት ሲታሰብ ነው:: ... ገፀባህሪያት በተሳሉበት ምናባዊ ዓለም ውስጥ የሚያደርጉት ልብ አንጠልጣይ እንቅስቃሴ ለአንባቢው አእምሮ ምናባዊ ፍስሐ ያጎናፅፋል:: በአጠቃላይ አንባቢው እንዲገረም፣ እንዲደመምና በገፀባህሪያቱ ውስጥ ራሱን እዲመለከት ያደርጋል:: ነገር ግን በዚህ ሂደት ውስጥ ከደስታ በስተቀር የሚገኝ ሌላ ነገር የለም ብለን ማጠቃለል የለብንም:: ጎን ለጎን አዳዲስ ቃላትን፣ ለየት ያለ ያጻጻፍ ስልትን፣ የሐሳብ አወራረድንና አደረጃጀትን መማር ይቻላል:: እንዲህ አይነቱም ልምድ በቋንቋ የመጠቀም ብቃታችንን ከማሳደጉም በተጨማሪ ለፈጣን የአነባበብ ስልት መዳበር የሚኖረው ድጋፍ ከፍ ያለ ነው (አለም 1995፣8) ::*

ከዚህም ሌላ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር የፈጠራ ሥራዎችም የራሳቸው ፋይዳ አላቸው:: ወንድወሰን (1995፣30) ‹‹ቋንቋን ለማስተማር ተመርጦ በሚቀርብ የፈጠራ ሥራ አማካይነት የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎችን ከማዳበር በተጓዳኝ ተማሪዎች የፈጠራ ሥራው አስማሚ መልእክት የሚባለው ፍች ላይ ለመድረስ በሚያደርጉት ደጋግሞ የማንበብ፣ የቃላትንና የሐረጎችን አውዳዊ ትርጓሜ የማውጣት፣ መልስ የማሰብ ጥረት አንድን ጽሑፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ያተባሉ::››

እንደነ Aebersold and Field (1997) ከሆነ ማንኛውም አይነት ምንባብ ለቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ በመሳሪያነት ሊያገለግ የሚችል ቢሆንም፣ በደረቅ ጽንሰ ሐሳብና በደረቅ ቋንቋ በመሞላቱና በሌሎች ባህሪያቱም ምክንያቶች የትምህርት ተቀባዩን ስሜት የመሳብና የማስደሰት ሃይሉ አነስተኛ ሊሆን ይችላል:: ይህ ከሆነ ደግሞ ተማሪዎችን የማያወያይ፣ የማያከራክር፣ የማያናግርና የማያጽፍ ስለሚሆን፣ የሚቀርቡት የክፍልና የቤት ሥራ መልመጃዎች የቋንቋ ክሂሎትን ብሎም የመመራመርን ችሎታ የማይጠይቁ ይሆናሉ::



ADDIS ABABA UNIVERSITY IES LIBRARY

በሌላም በኩል Dubin and Olshtain (1986) መጽሐፉንና ተማሪውን በተለያየ አውድ ማለትም በዲስኩር፣ በተግባቦት፣ በቃላት፣ በትርጉም ... ውስጥ ሊያገናኝ የሚችል ተስማሚ ይዘት ያለውን፣ የበለጠ ለማወቅ የሚያጓጓና የሚያነቃቃ ምንባብ መምረጥ የመጽሐፉ አዘጋጅ ተግባር ነው::

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦችም ከፍላጎት ጋር የሚሰምሩ፣ በታቻለ መጠን ከደረጃው ጋር የተገናዘቡ እውናዊ የሆኑ፣ በደንብ የተዘጋጁ፣ አላማ ያላቸው ተግባራትን ያካተቱና የማንበቡን ሂደት የሚያግዙ መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም፡-

- ምንባቡ አዳዲስ የቋንቋ ጉዳዮችን ያስተዋውቃል (ሰዋስውና ቃላት)፣ የቋንቋን ተግባራት ያዳብራል? ወዘተ.
- በንባብ ክሂል መዳበር ላይ ያተኮረ ነው?
- ምንባቡ ከሌሎች ክሂሎች ተግባራት ጋር የተያያዘ ነው?
- ምንባቡ በመዝናናትና በአእምሯዊ እርካታ ላይ ያተኩራል?
- ምን ያህል ምንባቦች አሉ?
- የምንባቦቹ ርዝመት ምን ያህል ነው? ጥልቅ ንባብን ወይስ ሰፊ ንባብን የሚያበረታቱ ናቸው?
- ምንባቦቹ ምን ያህል እውናዊ ናቸው?
- ትምህርቱ ተገቢ ነው? ማለትም (ሳቢ፣ የተለያየ ርዕሰ ጉዳይን የያዘ፣ ከባህሉ ጋር ስምሙ የሆነ፣ ወቅታዊ ነው? ወዘተ.)
- ምን ዓይነት ምንባቦችን (የጽሑፍ ዓይነቶችን) (genres) ተጠቅሟል? ተገቢ ናቸው? ወዘተ. (Cunningsworth 1995፥80) ::

ምንባቦች እነዚህን መመዘኛዎች በማገናዘብ ከተመረጡ የታሰበውን ውጤት ሊያስገኙ እንደሚችሉ ከምሁራኑ ገለፃዎች እንረዳለን::

ምንባቦቹ ወቅታዊ መሆን አለባቸው፣ ፀሐፊዎቹም ትምህርቱ ለሚቀርብላቸው አካባቢዎች ማህበራዊ ሁኔታ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው:: Dubin and Olshtain (1986፥156) ‹‹በየትኛውም እድሜ ለሚገኝ ሰው ከወቅቱ ሁኔታና ለወቅቱ ትምህርት የሚስማማው

መመረጥ አለበት:: ምርጫው ከመካከለኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ላሉ በተለያዩ አካባቢዎች ለሚኖሩ ተማሪዎች ተስማሚ መሆን አለበት::››

ለተማሪዎቹ የሚቀርቡት ርዕሶችና የፅሑፍ አይነቶች የማይስቧቸው ከሆኑ፣ እንዲሰሯቸው በሚቀርቡላቸው ክንዋኔዎች ለመሳተፍ ፈቃደኛ እንደማይሆኑ በመግለፅ Harmer (2001፣ 205-206) የሚከተሉትን ያክላሉ:: የማያውቁትን ማህበራዊ ጉዳይ በሚገልፅ የምንባብ አይነት ሊማሩ እንደማይፈልጉ፣ ተማሪዎቹ የሚፈልጓቸውንና በትምህርቱ ላይ ፍላጎት እንዲያድርባቸው የሚረዱ ርእሶችን መምረጥ፣ የተለያዩ ርእሶችንና የጽሑፍ አይነቶችን መምረጥ ወዘተ. ከፍተኛ ፍላጎት ሊያሳድርባቸው ይችላል::

በአንድ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ የተነደፈ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ የትምህርት ይዘቶች ተማሪውን ውጤታማ ሊያደርጉ የሚችሉ ሊሆኑ ይገባል:: ይዘቶች ሲመረጡ ተማሪዎች በቅርብ የሚያገኟቸውና ሊረዷቸው የሚችሉዋቸው፣ ሳቢ፣ እውነተኛ፣ የሚመጥኑና ወደ ተፈለገው ግብ የሚያደርሱ ወዘተ. መሆን ይኖርባቸዋል (Stern 1983፣27)::

የቋንቋ ትምህርት ይዘት በሚመረጥበት ወቅት ጥንቃቄ ያስፈልጋል:: ለዚህም የቋንቋ ትምህርት ይዘት ከመመረጡ በፊት ሊተኮርባቸው የሚገባቸው ነጥቦች መኖራቸውን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ በመግለጽ አለም (1995) እንደሚከተለው ይዘረዝራሉ::

1. የቋንቋ ትምህርት ይዘት በሚመረጥበት ጊዜ የቋንቋው ተማሪ እድሜ፣ የእውቀት ደረጃ፣ የአካባቢ ሁኔታ፣ ፍላጎት ወዘተ. በትኩረት እየተጠና ሊሆን ይገባል፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ያላጤነ የይዘት መረጣ የቋንቋ ተማሪዎችን አላስፈላጊ ችግር ውስጥ ከመክተቱም በላይ የታቀደውን አላማ በጭራሽ ከግብ ሊያደርስ አይችልም፡፡

2. የቋንቋ ትምህርት ይዘት በሚመረጥበት ጊዜ በመርሀ ትምህርት ውስጥ የተነደፈውን አጠቃላይና ዝርዝር አላማ ከግብ ማድረስ የሚችል መሆን አለመሆኑ በትኩረት እየታየና እየተመረመረ ሊሆን ይገባዋል ወዘተ. (አለም 1995፣26-27) ::

በቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡት ይዘቶች ከሚኖራቸው ዋና ዋና አላማዎች መካከል አንዱ የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎች ብቃት ማጎልበት ነው:: ለዚህም ክሂሎች እንደ አይነታቸው በተገቢ መንገድ ተቀናጅተው መቅረብ አለባቸው:: በተገቢው መንገድ

መቀናጀታቸውንና ለልጆቹ ተስማሚ መሆናቸውን ለማወቅ ደግሞ በየጊዜው ፍተሻ/ግምገማ/ ማካሄድ ተገቢ ይሆናል።

ለዚህም የአንድን መጽሐፍ የምንባብ ይዘቶች ስንመረምር ከግንዛቤ ልናስገባቸው የሚገቡ ያሏቸውን ጉዳዮች Cunningsworth እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

- የሚነበበው መጽሃፍ ብዛት፣
- የተካተቱት ምንባቦች አይነት፣
- ከምንባቡ ጋር የተያያዙት መልመጃዎችና ክንዋኔዎች ባህርይና ስፋት ወዘተ.

ምንባቦቹን በተመለከተም ማወቅ የሚገባን፡-

- ምን ያህል ረጃጅም ናቸው?
- ምን ያህል እውናዊ ናቸው?
- ምን ያህል ውስብስብ የሆነ ሰዋስዋዊና ዲስኩራዊ አገባብ አላቸው?
- የቃላቱ ብዛት ምን ያህል ነው?
- ምንባቦቹን ለመረዳት ማንኛውም ለየት ያለ በሰልጠና የተገኘ የቀደመ እውቀት ማስፈለጉን፣ በአጠቃላይ በምንባቡ ውስጥ የተካተቱ መልመጃዎችና ክንዋኔዎች ተማሪዎቹ አንብበው እንዲረዱና እንዲደሰቱ የሚረዷቸው መሆን አለባቸው (Cunningsworth 1995፣74-75) ::

እስከ አሁን የቀረበውን ስንመለከት አንብቦ የመረዳት ትምህርት የታለመለትን ግብ እንዲመታ ተማሪዎቹ በትምህርት ሂደት በተነቃቃ ሁኔታ መሳተፍ አለባቸው። ተማሪዎቹ ሊነቃቁ የሚችሉት ደግሞ ትምህርቱ ፍላጎታቸውን የሚያሟላና ተገቢ ሆኖ ሲቀረጽ ነው። ስለዚህ መማሪያዎቹ ልጆቹ ከሚያውቋቸው ወደማያውቋቸው ይዘቶች የሚወሰዱ፣በግል፣በጥንድ አልያም በቡድን ስራ ላይ ሊውሉ የሚችሉ ወዘተ. መሆን አለባችው። በመሆኑም እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን የCunningsworth (1995)ን፣ እንዲሁም የMcDonough and Shaw (2003)ና የአለም (1995)ን እንደ ሞዴል በመውሰድና እንደ አስፈላጊነታቸው በመምረጥ በዚህ ጥናት አገልግሎት ላይ ውለዋል።

## 2.4 አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር የሚቀርቡ መልመጃዎች ባህርይ

አንብቦ የመረዳት ተግባራት አንዳንድ ጊዜ ተማሪዎችን እንዲገነዘቡ በመርዳት ፋንታ መፈተን መስለው የሚቀርቡበት ጊዜ አለ:: አንዳንድ ጊዜ ምንባቦች ወይም ከነሱ ጋር የተያያዙት ተግባራት በጣም ቀላል ወይም በጣም ከባድ ይሆናሉ:: ይህንን ችግር ለመፍታት አንብቦ መረዳትን በሚያዳብሩ ተግባራት መጠቀም፣ እንዲሁም ምንባቡንና ተግባራቱን በተገቢው መንገድ ማጣጣም ይኖርብናል በማለት Harmer (2001፣207) ያብራራሉ::

በተጨማሪም NUttall (1982) አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር የሚቀርቡ መልመጃዎች የቋንቋ ችሎታን ከመመዘን ይልቅ የንባብ ግንዛቤን የማጠናከር ባህርይ ሊታይባቸው ይገባል:: አላማቸውም ለንባብ የቀረበው ጽሑፍ የተዋቀረበትን የቋንቋ ክፍሎች ማሳወቅ መሆን የለበትም:: የመልመጃዎቹ አቀራረብ ትኩረት የቋንቋ ችሎታን ለመመዘን ከሆነ፣ የንባብ ችሎታን ለማዳበር የሚኖራቸው እገዛ አነስተኛ ስለሚሆን ትኩረታቸው ለግንዛቤ በማንበብ ሂደት ላይ ሊሆን ይገባል (Greenwood 1981) ::

ከምንባብ የሚወጡ መልመጃዎች የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ፣ ውጤታማ ትምህርት ለማስተማር የሚረዱ መሆን አለባቸው:: ስለሆነም አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ሲቀርቡ የትምህርቱን አላማ መሰረት አድርገው ተማሪው አላማውን በተሟላ መንገድ ለማከናወን እስከቻለ ድረስ በ‹‹አዎ››ወይንም ‹‹አይደለም››፣ በ‹‹እውነት››ወይም ‹‹ሐሰት››፣ ‹‹ባዶ ቦታን በመሙላት››፣ በ‹‹ምርጫ›› ወዘተ. መልክ ማቅረብ ይቻላል:: ስለዚህ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝን የአንብቦ መረዳት መልመጃ አዘጋጅ ተማሪውንና ተግባራቱን በማገናኘት ተማሪው ውጫዊና ውስጣዊ ፍንጮችን ተጠቅሞ በቀረበው ይዘት አማካኝነት የቋንቋው ተጠቃሚ እንዲሆን መርዳት ነው(አለም 1995፣ Harmer 2001 እና David 2005) ::

በሌላም በኩል አንብቦ የመረዳትን ጥያቄዎች በሁለት መልክ ማደራጀት ይቻላል:: ይሄውም የምንባቡን አደረጃጀት እንዲገልጹ፣ የምንባቡን ይዘት እንዲያብራሩና እንዲገልጹ ማድረግ ተገቢ መሆኑን አለም (1995) በሚከተለው አይነት ያብራራሉ::

1. የምንባቡን ጠቅላላ አቀነባበር ወይም አደረጃጀት መንገድ እንዲገልጹ ማድረግ:: ካሉ በኋላ፣ በዚህ ስር ሊጠየቁ ስለሚገባቸው ጉዳዮች እንደሚከተለው ያብራራሉ::
    1.1. የምንባቡን ተግባር መጠየቅ (መዘርዝራዊ፣ ቀስቃሽ፣ ኪነታዊ ወዘተ.)
    1.2. የምንባቡን አይነት መጠየቅ (ልቦለድ፣ ኢ-ልቦለድ ወዘተ.)
    1.3. ስለአያያዥ ቃላቶች ተግባር መጠየቅ::
    1.4. በአረፍተ ነገሮች መካከል ስላለው ዝምድና መጠየቅ::
2. የምንባቡን ይዘት እንዲያብራሩና እንዲገልጹ ማድረግ:: በዚህ ስር የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ይቻላል::
    2.1. ግልጽ በሆነ መንገድ የሰፈሩ ግልጽና ያልተሸፈኑ ጥያቄዎችን መጠየቅ::
    2.2 በውስጠ ታዋቂነት የተገለጹ ጉዳዮችን በምንባቡ መሰረትነት መጠየቅ::
    2.3 በግምት ወይም በይመስላል ሊደረስባቸው የሚችሉትን ትርጉሞች መጠየቅ::
    2.4 በምንባቡ የቀረበውን ሐሳብ መገምገም፣ መመዘን (አለም 1995፣ 12) ::

በዚህ አይነት የምንባቡን ተግባርና ይዘት መሰረት በሚያደርግ መንገድ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት ተማሪዎችን ከተለያየ የአነባበብ ስልት ጋር ያስተዋውቃል፤ አንብቦ የመረዳት ችሎታንም ያዳብራል::

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚዘጋጁ ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ከአእምሮታዊ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ፣ የአመራማሪነት ባህርይ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል (Grellet 1981፣4-8):: በሌላም በኩል Sheng (2000) አእምሮታዊ ክሂልን መሰረት ያደረጉ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች:-

1) ለማንኛውም ደረጃና ለተለያዩ ተማሪዎች ፍላጎት ተስማሚ በመሆናቸው፣
2) ተማሪዎች ምንባቡን ከተለያዩ አቅጣጫዎች እንዲመለከቱና የይዘቱን እንድምታዎች እንዲረዱ ስለሚጠይቁ፣
3) ምንባቡን ለመተንተንና ለማጠቃለል ስለሚያስችሉ፣
4) የተማሪዎችን አስተውሎትና የፍጥነት ንባብ ስለሚያዳብሩና
5) የሂስና የትንበያ ክሂሎችን ስለሚያሻሽሉ አስፈላጊ ናቸው ይላሉ::

በተጨማሪም McDonough and Shaw (2003 ፣110) ፣ Aebersold and Field (1997፣ 45)፣ David (2005፣ 13) አእምሮታዊ ሞዴልን መሰረት ያደረጉ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችና ተግባራት አይነቶችን እንደሚከተለው በዝርዝር ያብራራሉ::

1. ቀጥተኛ ጥያቄዎች፣ እነዚህ ጥያቄዎች ተማሪው ብዙ ሳይመራመር ከሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ የተጠየቀውን ነገር በቀላሉ ለመመለስ እንዲችል የሚያግዙ ናቸው:: ለትምህርቱ ከተመረጠው ምንባብ ውስጥ በቀጥታና በተሟላ ሁኔታ ተገቢውን መልስ ለመመለስ የሚረዱ ጥያቄዎችን ያካተቱ ናቸው:: ስለዚህ ተማሪዎች መልሶችን የሚሰጡት እዚያው ምንባቡ ውስጥ በሰፈሩት ቃላት እንጂ የራሳቸውን አገላለጽ መጠቀም አይፈለግባቸውም:: ልጆቹ ባነበቡት ምንባብ ላይ በቀጥታ የተገለጹትን እንዲያስተውሉ ወይም እንዲለዩ የሚጠይቁና አጫጭር መልሶችን የሚፈልጉ ናቸው:: እንዴት?፣ የት?፣ መቼ?፣ ወዘተ. የመሳሰሉት አብዛኛውን ጊዜ ቀጥተኛ ጥያቄዎች ናቸው :: በቀጥተኛ ጥያቄዎች ስር የሚካተቱትም:-
    - ዝርዝሮችን የመለየት ጥያቄዎች፣
    - ቅደም ተከተልን የማስታወስ ወይም የመለየት ጥያቄዎች፣
    - ዋና ዋና ሐሳቦችን የመለየት ጥያቄዎች፣
    - ምክንያትና ውጤቶችን የመለየት ጥያቄዎች፣
    - የገጸባህሪያትን ጠባይ የመለየት ወይም የማስታወስ ጥያቄዎች ወዘተ.
2. የትንበያ ጥያቄዎች :- ጸሐፍት ሊገልጹ የፈለጉትን ቁም ነገር በግልጽ ሳያስቀምጡ ለአንባቢ የሚተውለት አጋጣሚ ብዙ ነው:: ከአንባቢው የሚጠበቀው የማሰብ ችሎታውንና ቀደምት እውቀት ተጠቅሞ ሐሳቦችንና ዝምድናቸውን መረዳት ይሆናል:: ለዚህም ጥያቄዎቹ ቀጥሎ የቀረቡትን አይነት መሆን አለባቸው::
    - ዝርዝር ሐሳቦችን የመተንበይ ጥያቄዎች፣
    - ዋና ዋና ሐሳቦችን የመተንበይ ጥያቄዎች፣
    - ቅደም ተከተልን የመተንበይ ጥያቄዎች፣
    - ምክንያትና ውጤትን የመተንበይ ጥያቄዎች ወዘተ.
3. የግመገማ ጥያቄዎች:- የጸሐፊውን ሐሳብ ከራሳቸው አመለካከት አኳያ በመተንተን የሚመለሱ ጥያቄዎችን ይመለከታል:: እነኝህ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ብቻ የሚጋብዙ ሳይሆን፣ በመልስነት ያቀረቡትን ሐሳብ በማስረጃ

እንዲያጠናክሩ የሚጠይቁም ናቸው:: ልጆቹ ያነበቧቸውን ምንባቦች በተመለከተ እንዲሄሱ የሚጠይቁ ናቸው:: በምንባቦቹ ጥቅም፣ ትክክለኛነት፣ ወቅታዊነት ወዘተ. ዙሪያ እንዲገመግሙ ይጠበቃል:: ጥያቄዎቹም ቀጥሎ የቀረቡትን ይመስላሉ::

- ፈጠራን የመገምገም ጥያቄች፣
- አስተያየትን የመገምገም ጥያቄዎች፣
- ብቃትንና ተገቢነትን የሚገመግሙ ጥያቄዎች፣
- ፋይዳን(ረብን) የሚገመግሙ ጥያቄዎች ናቸው::

4 አቋምን የመግለጽ ጥያቄዎች፡- እነዚህ ጥያቄዎች አንድ ምንባብ በተማሪዎች ላይ የሚፈጠረውን ስነ-ልቦናዊ፣ ስነውበታዊ ስሜቶችን፣ ስነ ጽሁፋዊ ቅርጾችን፣ ስልቶችንና ብልሀቶችን አስመልክቶ የተሰማቸውን በግል መልስ የሚሰጥባቸው ጥያቄዎች ናቸው::

በዚህ ስር የሚነሱ ጥያቄዎችም:-

- የግል አቋምን የሚገልጹ ጥያቄዎች
- በቋንቋና በስልት ዙሪያ አስተያየት የመስጠት ጥያቄዎች ወዘተ. ናቸው::

አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች በዘፈቀደ የሚጻፉ ድንገተኛ ጥርቅሞች ሳይሆኑ፣ ከሚፈለገው አላማ ጋር በተያያዘ መንገድ በስልት ሊዘጋጁ ይገባል:: አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ለማስተማር አመች የሆኑ ስራዎች በውስጣቸው የያዟቸውን ዋነኛና ደጋፊ የሆኑትን ሐሳቦች፣ አንቀጾችንና አረፍተ ነገሮችን ከሌሎቹ የጽሑፎቹ ባህሪያት ጋር ለማያያዝ የሚያስችሉ ቃላትን እንዲረዱ የሚያግዙ መልመጃዎችን ያቀርባሉ(Dubin and Olshtain 1986፣164) :: እንዲሁም ምንባብን እንብቦ ለመረዳት የሚያግዙ ጥያቄዎች የተለያዩ አይነቶች ሲሆኑ፣ ከሁሉም ውስጥ ተማሪው አንብቦ የመረዳት ክሂሉን እንዲጠቀም የሚያደርጉ አገባብን የሚመለከቱ ጥያቄዎችም ይገኙበታል:: በምንባብ ውስጥ ወዳሉ የተወሰኑ አረፍተ ነገሮች ስሜታቸውን በመምራትና ከጥያቄው አረፍተ ነገር አስፈላጊነት ጋር በማያያዝ ትክክለኛውን መልስ እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል (Widowson 1978፣110)::

የሁነቶችን መንስኤና ውጤት መረዳት የሚያስችሉ ትምህርቶች በአንብቦ መረዳት ትምህርት ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች ናቸው:: የምክንያትና የውጤት ጉዳዮች በነጠላ ወይም በተለያዩ የአረፍተ ነገሮች አይነት ውስጥ ሊታዩ ይችላሉ:: ዝምድናቸው

በገሐድ ወይም በውስጠ ታዋቂነት ሊገለጽ ይችላል:: ስለሆነም እነዚህን ሁኔታዎች መሰረት ያደረገ ጥያቄ በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ውስጥ ተካትቶ ልጆቹ ሊለማመዱበት ይገባል (Harris, A. and Sipay, E. 1990፣ 586) ::

አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ሲዘጋጁ በቃልም ሆነ በጽሁፍ ሊቀርቡ በሚችሉበት መንገድ ማደራጀት ይቻላል:: ተማሪዎች የምንባቡን የተለያዩ ክፍሎች በጥልቀት እንዲያነቡ የሚያደርጓቸው መልመጃዎችን መስራት አለባቸው:: ስለዚህ የሚዘጋጁት አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር የምንባቡን ጠቅላላ የአደረጃጀት መንገድ እንዲያብራሩ ፣ የምንባቡን ይዘት እንዲገልጹና እንዲያብራሩ ማድረግ ይቻላል::

ከዚህም ሌላ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች በተለያየ መንገድ መቅረብ ቢችሉም፣ የታለመውን ግብ እንዲመቱ ቀጥሎ በቀረቡት መሰረት መዘጋጀት እንዳለባቸው አለም (1995፣13) ያስረዳሉ::

1. ጥያቄዎች ምንባቡን ባላነበበ ሰው ሊመለሱ የሚችሉ ሊሆኑ አይገባም::
2. ጥያቄዎች ባንድ በተወሰነ የምንባቡ ክፍል ላይ የተመሰረቱ ሳይሆኑ፣ ሁሉንም የምንባቡን (የጽሑፉን) ክፍል በሚዳስሱበት መንገድ የሚዘጋጅበት ሁኔታ ሊመረመር ይገባል::
3. የጥያቄዎቹ ቁጥር እጅግም ሳይበዛ እጅግም ሳያንስ በቂ የሆነ መጠን እንዲኖራቸው ያስፈልጋል::
4. የተለያዩ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የማቅረቢያ መንገዶች አሉ:: ስለዚህም ጥያቄዎችን በተለያየ አቀራረብ መንገድ ለማቅረብ መሞከር አስፈላጊ ይሆናል::
5. ጥያቄዎች አንድ አንባቢ ሊኖረው ከሚገባ የንባብ ስትራቴጂ ጋር የማስተዋወቅ ሃይል ሊኖራቸው ይገባል::
6. ጥያቄዎቹ ተማሪዎች ምንባቡን በበለጠ እንዲረዱ የሚያግዙ መሆን ይኖርባቸዋል::
7. ጥያቄዎቹ የተገለጹበት ቋንቋ ከምንባቡ ቋንቋ የጠነከረ ወይንም የከበደ መሆን አይኖርበትም::
8. የጥያቄዎቹ መልሶች ተማሪው በደረጃው ሊኖረው ከሚገባው የቋንቋ ብቃት የሚልቅ የቋንቋ አጠቃቀም መጠየቅ የለባቸውም::

9.አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች የተማሪውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉበት መንገድ እንጂ የተማሪዉን ችሎታ የሚፈትኑ አይነት ሆነው መቅረብ አይኖርባቸውም::

10.አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ከሌሎች ክሂሎች ጋር ተጣምረውና ተቀናጅተው የሚቀርቡበት መንገድ ማፈላለግ አስፈላጊ ነው::

በዚህ አይነት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችም ቀደም ሲል ስለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች በተለያዩ ምሁራን የተሰነዘሩትን ሁኔታዎች የማያሟሉ ከሆኑ ተማሪዎቹ የምንባቦቹን ልዩ ልዩ ክፍሎች በሚገባ እንዲዳስሱ ስለማይገፋፏቸው አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር አይችሉም ማለት ነው::

በጥቅሉ እስከ አሁን የንባብን ምንነት፣ አንብቦ የመረዳትን ምንነት፣ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚቀርቡ መልመጃዎችን ወዘተ. ለማየት ሞክረናል:: ቀጥለን ከዚህ ሥራ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ጥናቶች እንዳሉ ስንፈትሽ ከዚህ ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ያለው ጥናት የለም:: ሆኖም ግን ትንሽ ተመሳስሎ የሚታይበት በ1986 ዓ/ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ በጌተቸው አዱኛ "ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች የብቃት ደረጃ" በሚል ርእስ የቀረበው ነው:: ይህም ቢሆን ጥናቱ በተካሄደበት ዘመን፣ በክፍል ደረጃ (በተተኳሪው መጽሐፍ) አኳያ ሲታይ ይሄ ነው ተብሎ ተመዞ የሚወጣ ዝምድና የላቸውም::

# ምዕራፍ ሶስት

# የአጠናን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት እንዴት እንደቀረበ መገምገም ነው:: በዚህ መሰረት በመጽሐፉ ውስጥ ያለው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ተፈትሿል::

## 3.1 የመጽሐፍ፣ የትምህርትቤት፣ የተማሪዎችና የመምህራን አመራረጥ

### 3.1.1. የመጽሀፍ አመራረጥ

በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ ለ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ የሆነው መጽሀፍ ለዚህ ጥናት ዋነኛው የመረጃ ምንጭ ነው:: የተመረጠውም ቀደም ሲል አጥኚው ከነበረው ልምድ፣ በየአጋጣሚው ከሚሰማው በመነሳትና በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን አንብቦ የመረዳት ትምህርት አስመልክቶ የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ ነው::

### 3.1.2. የትምህርትቤት አመራረጥ

በድሬዳዋ ከተማ ዘጠነኛ ክፍል የሚገኝባቸው ስምንት ትምህርት ቤቶች:- :- ድሬዳዋ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ፣ መልካ ጀብዱ፣ ለገሐሬ፣ አዲስ ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ፣ ማርያም ሰፈር፣ አፈተ ኢሳ፣ ሳቢያን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃና መደኃኒዓለም ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ፣ በሐረር ከተማ ዘጠነኛ ክፍል የሚገኝባቸው የመንግስት ትምህርት ቤቶች ደግሞ:- አማሬሳ 2ኛ ደረጃ፣ ሐረር ከፍተኛ 2ኛ ደረጃና አባድር ትምህርት ቤቶች ናቸው::

ከነዚህ በድሬዳዋ ከተማ ከሚገኙት ስምንት፣ በሐረር ከተማ ከሚገኙት ዘጠነኛ ክፍል ከሚገኝባቸው ሶስት የመንግስት ት/ቤቶች ውስጥ እንደብዛታቸው በተራ የእጣ ናሙና አመራረጥ /Simple random Sampling/ ዘዴ ከድሬዳዋ የተመረጡት ሶስት ት/ቤቶች ሲሆኑ፣ እነሱም፣ ሳቢያን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ድሬዳዋ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤትና ማሪያም ሰፈር ት/ቤት፣ ከሐረር ከተማ ደግሞ ሐረር ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በጥናቱ ተካትተዋል::

ጥናቱን ለማካሄድ ዘጠነኛ ክፍል የተመረጠው ቀደም ሲል ከነበረ ልምድ፣ በየአጋጣሚው ስለዚህ ክፍል መጽሐፍ ከሚሰማው፣ በተጨማሪም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስላለው አነብቦ የመረዳት ትምህርት የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ ነው:: አጥኚው ደጋፊ መረጃዎችን በድሬዳዋና በሐረር ከተማ ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች የሰበሰበው የአካባቢው ት/ቤቶች፣ መምህራንና ተማሪዎች ተደጋጋሚ የሆነ መረጃ በመስጠት ያልተሰላቹና አጥኚው በሚገባ የሚያውቀው አካባቢ በመሆኑ ለመረጃ መሰብሰብ ከፍተኛ ትብብር ስለሚገኝ ባለው አመችነት ነው፡፡

### 3.1.3. የተማሪዎች ናሙና አወሳሰድ

የተማሪዎችን የናሙና አወሳሰድ በተመለከተም ከላይ በተዘረዘሩት የድሬዳዋና የሐረር ት/ቤቶች ውስጥ በ2000 ዓ.ም. የትምህርት ዘመን በዘጠነኛ ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙት ተማሪዎች በምድብ ብዛት ሳቢያን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 16፣ ድሬዳዋ አጠቃላይ 10፣ ማርያም ሰፈር ት/ቤት 7፣ ሐረር ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 26 ሲሆኑ፣ ከነዚህም ከያንዳንዳቸው 25% ሲወሰድ፣ ከሳቢያን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 4 ምድብ፣ ከድሬዳዋ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት 2 ምድብ፣ ከማርያም ሰፈር ት/ቤት 2 ምድብ፣ ከሐረር ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ደግሞ 6 ምድብ ተወስደዋል::

ቀጥሎም ከያንዳንዱ ት/ቤት 25% ሲወሰድ፣ ከሳቢያን ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በአራቱም ምድቦች ከሚገኙት 300 ተማሪዎች ውስጥ 75 ተማሪዎች፣ ከድሬዳዋ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በሁለቱም ምድቦች ከሚገኙት 130 ተማሪዎች ውስጥ 32፣

ከማርያም ሰፈር ት/ቤት በሁለቱም ምድቦች ከሚገኙት 126 ተማሪዎች ውስጥ 31፣ ከሐረር ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በስድስቱም ምድቦች ከሚገኙ 420 ተማሪዎች ውስጥ 105 ተማሪዎች ተመርጠዋል:: ይሄውም ከያንዳንዱ ከተመረጡት ክፍሎች ማለትም 25% ውስጥ ለምሳሌ በአንድ ክፍል ያሉት 73 ተማሪዎች ቢሆኑ፣ ከነዚህ ውስጥ የሚመረጡት 18 (73x 25/100 = 18) ይሆናሉ:: እነዚህ አስራስምንት ተማሪዎች በስም መቆጣጠሪያ ዝርዝሩ ላይ (73÷18=4) አራት አራት በመዝለል 1፣ 5፣ 9፣ 13....73 የተመዘገቡት 243 ተማሪዎች በተራ የእጣ ናሙና ዘዴ ተወስደው የጽሑፍ መጠይቅ እንዲሞሉ የተደረገ ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ አምስቱ ያልተሟሉ በመሆናቸው ሲቀነሱ፣ ሦስቱ ተማሪዎች ደግሞ በጊዜው ትምህርት ቤት ባለመገኘታቸው መጠይቁን የሞሉት 235 ተማሪዎች ናቸው:: ስለዚህ የሚተነተነውም ከ235 ተማዎች የተገኘ መረጃ ነው፡፡ ይህ የናሙና አወሳሰድ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ለሁሉም እኩል የመመረጥ እድል ስለሚሰጥ ነው::

### 3.1.4. የመምህራን አመራረጥ

ቀደም ሲል በተመረጡት ት/ቤቶች ውስጥ ያሉ የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በመረጃ ሰጪነት የተሳተፉ ሲሆን፣ ቁጥራቸው አነስተኛ በመሆኑ በአራቱም ት/ቤቶች ያሉ 17 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ የጽሐፍ መጠይቅ እንዲሞሉና አስተያየት እንዲሰጡ ተደርጓል::

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በዋነኛነት ከዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የተካሄደ የሰነድ ምርመራ፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች የቀረቡ የጽሑፍ መጠይቆችና ከመምህራን የተገኙ አስተያየቶች አጥኚው ይዞት የተነሳውን አላማ ከግብ ለማድረስ አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡

### 3.2.1. የሰነድ ምርመራ

በ1997 ዓ.ም ተሻሽሎ የታተመው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጭ ነው:: በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ሁሉም ምንባቦችና ከምንባቦቹ የወጡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች በዝርዝር ተመርምረዋል:: በክለሳ ድርሳናት ውስጥ በተካተቱ በ Cunningsworth (1995)፣ በ McDonough and Shaw (2003) ና በአለም (1995) በተሰነዘሩ አንብቦ የመረዳት ንድፈ ሐሳቦችና በሌሎችም መነሻነት የምንባቦቹን የይዘት ግልጽነትና የመልመጃዎችን አቀራረብ የተመለሰከቱ መረጃዎች በዝርዝር ተተንትነዋል::

### 3.2.2. ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ላሉ መምህራን የተዘጋጁት የጽሑፍ መጠይቆች ሁለት ክፍሎች አሏቸው:: በየመጠይቆቹ የመጀመሪያ ክፍል የመምህራኑ ዳራ የተጠየቀ ሲሆን፣ በሁለተኛው ክፍል የተተኳሪ መጽሐፉ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ (ይዞታ) የተመለከቱ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው:: በዚህም በ‹‹ሊከርት ስኬል›› በአምስት ደረጃዎች (በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሚሉ) የቀረቡ 36 ዝግ ጥያቄዎችና አስተያየታቸውን የሚጋብዝ አንድ ጥያቄ በድምሩ 37 ጥያቄዎች ቀርበዋል:: መጠይቆቹ በሙሉ በዚህ ጥናት ምእራፍ ሁለት ላይ የቀረቡት የነ Cunningsworth (1995)፣ McDonough and Shaw (2003) እንዲሁም አለም (1995)ን ንድፈ ሐሳቦች መሰረት በማድረግ በአጥኚው የተዘጋጁ ናቸው:: የጥያቄዎቹን የብቃት ደረጃ ለመጠበቅ እንዲቻል የመጀመሪያው ረቂቅ በጥናቱ አማካሪ ከታየና ተገቢው ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ ለሁለት የስነ ልቡና ትምህርት ክፍል መምህራን ተሰጥቶ ተገቢ የሆነ አስተያየት በመገኘቱ ተስተካክሏል::

### 3.2.3. ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ

ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጁት የጽሑፍ መጠይቆች ለመምህራን እንደቀረቡት ሁሉ ሁለት ክፍሎች አሏቸው:: የመጀመሪያው የተማሪዎቹን ዳራ የሚመለከት ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ተማሪዎቹ የሚገለገሉበትን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የንባብ ትምህርት አቀራረብ፣ ለፍላጎታቸው፣ ለዕድሜያቸው ወዘተ... ያለውን

ተስማሚነትና መልመጃዎችን የተመለከቱ ናቸው። በዚህ ክፍል የተካተቱት 26 ዝግ ጥያቄዎች ናቸው። እነሱም በ‹‹ሊከርት ስኬል›› በአምስት ደረጃዎች (በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በሚል) የቀረቡ ናቸው። መጠይቆቹ በሙሉ በዚህ ጥናት ምእራፍ ሁለት ላይ የቀረቡትን የነ Cunningsworth (1995)፣ McDonough and Shaw (2003)ና አለም (1995) ንድፈ ሐሳቦች መሰረት በማድረግ በአጥኚው የተዘጋጁ ናቸው።የጥያቄዎችን የብቃት ደረጃ ለመጠበቅ እንዲቻል የመጀመሪያው ረቂቅ በአማካሪ ከታየና ተገቢው ማስተካከያ ከተደረገበት በኋላ ለሁለት የስነ ልቡና ትምህርት ክፍል መምህራን ተሰጥቶ ተገቢ አስተያየት በመገኘቱ ተስተካክሏል።

## 3.3 የመረጃ አጠናቃቀርና አተናተን

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦችና በአጠቃላይ አንብቦ የመረዳት ትምህርት የቀረበበትን ሁኔታ በመፈተሽ በምዕራፍ ሁለት ላይ ከቀረበው ትውረት አኳያ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ እንዲሁም ለመምህራንና ለተማሪዎች ከቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች የተገኙትን መልሶች ድግግም በቁጥር በመውሰድ በመቶኛ ተለውጧል። እንደ ጥያቄው አቀራረብ ውጤቱን በማየት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መልስ መስጠቱን መገንዘብ በሚቻልበት ሁኔታ ሰፍሯል። በተጨማሪም ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው ሌላም ከመምህራን አስተያየት የተገኙት መረጃዎች የአይነታዊ የምርምር ዘዴ አካል በሆነው ገላጭ የአተናተን ዘዴ ተተንትነዋል።

# ምዕራፍ አራት
# የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

ይህ ጥናት ይዞት የተነሳው ዓላማ ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን መፈተሽ መሆኑ ባሉት ክፍሎች ተገልጿል:: የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስም በዋናነት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ካሉት ምንባቦችና መልመጃዎች በፍተሻ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች በጽሑፍ መጠይቅ፣ እንዲሁም ከመምህራን አስተያየት በአጋዥነት የተሰበሰቡ መረጃዎች በገላጭ የምርምር ዘዴ ተተንትነው በሚከተለው መልክ ቀርበዋል::

## 4.1. በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኝ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘት ትንተና

በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ምንባቦችና ከምንባቦቹ የወጡ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ቀርበዋል :: ለዚህ ሥራ ትንታኔ እንዲያመች የምንባቦች የይዘት ግልጽነትና ተስማሚነት እንዲሁም የመልመጃዎች አቀራረብ ባህርይ በሚል በሁለት ክፍሎ ለማየት ተሞክሯል::

### 4.1.1. የምንባቦች የይዘት ግልጽነትና ተስማሚነት

በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን (Genres) ያካተቱ ከሆኑ ለተማሪዎቻችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ መዳበር ወሳኝ ናቸው:: የምንባቦቹ የቋንቋ አጠቃቀም በአካባቢው ዕለት ተዕለት አገልግሎት ላይ ከሚውለው ጋር ተስማሚ ከሆኑ፣ በተቻለ መጠን ከደረጃው ጋር የተገናዘቡ፣ እውናዊና ወቅታዊ መሆን አለባቸው:: በተጨማሪም መጠናቸው በጣም ረጃጅም ወይም አጫጭር ያልሆኑና ከተለያዩ የአነባበብ ስልቶች ጋር የሚያስተዋውቁ፣ ሳቢና የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዙ ከሆኑ ወዘተ. የታሰበውን ወጤት ሊያስገኙ ይችላሉ በማለት ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ላይ በ Cunningsworth (1995)ና በሌሎች ምሁራን የተሰነዘሩትን ለማመልከት ተሞክሯል::

በዚህ መሰረት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች የተውጣጡ መሆናቸውን ለማየት ተሞክሯል፡፡ ይሄውም በጠቅላላው 15 ምንባቦች የቀረቡ ሲሆን፣ እነዚህ ምንባቦች ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች የተውጣጡ መሆናቸውን ለማወቅ እንዲረዳን ቀጥሎ የቀረበውን ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ-1- በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች አይነት

| ተ.ቁ. | የምንባቦች አይነት | ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ሥነልሳን | 1 | 6.67 |
| 2 | ልዩ ልዩ ኢ-ልቦለዶች | 8 | 53.33 |
| 3 | አጭር ልቦለድ | 3 | 20 |
| 4 | ግጥም | 2 | 13.33 |
| 5 | ተውኔት | 1 | 6.67 |
| 11 | ጠቅላላ ድምር | 15 | 100 |

ከሠንጠረዥ 1 ማየት እንደሚቻለው ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ -3- አጭር ልቦለድ፣ 8 ኢ-ልቦለድ (ወግ፣ የሕይወት ታሪክ፡ ታሪክ፣ ዘገባ ወዘተ.)፣ 1 ስነ-ልሳንና 1 ተውኔት የተካተቱባቸው የጽሑፍ አይነቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ይዘቶችን ያካተቱ ምንባቦች መቅረባቸው ደግሞ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ እንደሚያዳብሩ ቀደም ሲል በምሁራኑ ከቀረበው ሐሳብ በተረዳነው መሰረት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች የማያሰለቹ፣ የተለያዩ የጽሑፍ አየነቶችን ያካተቱና እውናዊ (Authentic) በመሆናቸው የተማሪውን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ማዳበር ይችላሉ፡፡

እንዲሁም የምንባቦቹ የቋንቋ አጠቃቀም በአካባቢው ዕለት ተዕለት አገልግሎት ላይ ከሚውለው አጠቃቀም ጋር ያለውን ተስማሚነት ከመምህራን የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በአማርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ለሆኑት እንደሚስማማ ተገምቷል፡፡ ይሄውም አፍ-ፈት የሆኑት ከአንደኛ ክፍል ጀምረው አማርኛ ቋንቋን መማር ከመጀመራቸውም በላይ ከአንደኛ ክፍል ጀምረው እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ሁሉንም ትምህርቶች የሚማሩት በአማርኛ ቋንቋ ነው፡፡ በተጨማሪም ከት/ቤት ውጭ በቋንቋው ስለሚጠቀሙበት ለአፍ-ፈቶቹ ባብዛኛው አይከብዳቸውም ወይም ዕለት በዕለት ከሚጠቀሙበት ጋር ይስማማል፡፡ በሌላ

በኩል ለአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ-ፊት ከሆኑት ውስጥ አማርኛን ሦስተኛና አምስተኛ ክፍል መማር ጀምረው እስከ ስድስተኛ ክፍልም በአፍ መፍቻቸው ስለሚማሩ፣ እንዲሁም ከትምህርት ቤት ውጭ በአብዛኛው በአማርኛ ቋንቋ ስለማይጠቀሙ አፍ መፍቻቸው በሆኑትና በተለይም ከገጠር ለሚመጡት ኢ-አፍ ፈቶችና ለከተሜዎቹ በእኩል ደረጃ ተስማሚነት አላቸው ለማለት ያስቸግራል። እዚህ ላይ ሰለሞን (1995፣14) ‹‹በርካታ ክልሎች የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች የመማሪያና የሥራ ቋንቋዎች ሆነዋል። በሥራ ቦታና በየገበያው ቦታ በየክልሉ ቋንቋ መጠቀምም እየተስፋፋ መጥቷል። ይህ ደግሞ በተራው አማርኛን በተፈጥሯዊ መቸት የመልመድን ዕድል እያጠበበውና ቋንቋውን በመማር ብቻ የሚገኝ እያደረገው ይሄዳል። ስለሆነም ተማሪዎች የሚኖራቸው የአማርኛ ቋንቋ ዕውቀትና ችሎታ እጅጉን በትምህርት ቤት በምናቀርብላቸው ትምህርት ላይ የተመሰረተ ይሆናል›› በማለት ይህ ሁኔታ ለትምህርቱ ከፍተኛ ትኩረት መስጠትን እንደሚያስከትል ያቀረቡትን ያስታውሰናል። በተጨማሪም መምህራን በሰጡት አስተያየት ተማሪዎቹ ዘጠነኛ ክፍል ሲደርሱ አፍ-ፈትና ኢ-አፍ-ፈት በአንድ መጽሐፍ እንዲማሩ ሲደረግ ኢ-አፍ ፈቶች መታሰብ እንደሚገባቸው የጠቆሙትም ይህንኑ ጉዳይ ያጠናክረዋል።

ለአንብቦ መረዳት ትምህርት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ ምንባቦች ከጊዜው ጋር የሚሄዱ ወቅታዊ ይዘት ያላቸው መሆን አለባቸው ። በየትኛውም እድሜ ለሚገኝ ሰው ከወቅቱ ሁኔታና ለወቅቱ ትምህርት የሚስማማው ምንባብ መመረጥ አለበት። ምርጫው ከመካከለኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ላሉ በተለያዩ አካባቢዎች ለሚኖሩ ተማሪዎች ተስማሚ መሆን እንዳለበት Dubin and Olshtain (1986፣156) ያቀረቡት ሀሳብ በምዕራፍ ሁለት ተመላክቷል። በተመሳሳዩ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች፣ ለምሳሌ ከገጽ-5-7 ‹‹የጊዜ አጠቃቀም›› በሚል ርዕስ ከቀረበው ውስጥ ‹‹.. በብዙዎቻችን ዘንድ ለተለያዩ ተግባራት የሚውልን ጊዜ የመመደብ ልማድ አላዳበርንም›› የሚለው ጊዜን ለአስፈላጊ ጉዳይ በተገቢ መንገድ ከፋፍሎ መጠቀም አለመቻል ዛሬም ትልቅ ችግር ነው። ይህንን ችግር በማሳወቅ ስለ ሰዓት አጠቃቀም ማስገንዘብ ተገቢ ብቻ ሳይሆን ወቅታዊም ነው። ሌላው ከገጽ 122-126 ‹‹የመንደሩ መርፌ ወጊ›› በሚል ርዕስ የቀረበውም በተለይ አሁን በሐገራችን ካለው የጤና ችግር አኳያ በየመንደሩ የሚካሄደው ህክምና ለብዙ ሰው ጤና መታወክና ለልዩ ልዩ በሽታ መዛመት ምክንያት መሆኑን በሚሰብና ተውኔታዊ በሆነ መንገድ ቀርቦ እናገኛለን።



AAU ... LIBRARY

በተጨማሪም ከገጽ 32-33 የቀረበው ‹‹ድር ቢያብር››፣ ከገጽ 48-51 ‹‹የሕዝብ ብዛትና የአገር እድገት››፣ ከገጽ 71-75 ‹‹እንዲህም ተኖረ›› የሚሉት ወቅታዊ ሁኔታዎችን የተመለከቱ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ምንባቦቹ በጣም ረጃጅም ወይም በጣም አጫጭር ያልሆኑና ከተለያዩ የንባብ አይነቶች ጋር የሚያስተዋውቁ፣ ሳቢና የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዙ ከሆኑ የታሰበውን የትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ ብቃት እንደሚኖራቸው በክለሳ ድርሳን ላይ ተመልክተናል፡፡ እንደነ Day and Bamfored (2002፣ 12) አገላለጽ ማራኪና ተስማሚ የሆኑ፣ በተለይም አጠር ብለው በጥቂት ደቂቃዎች ተነበው የሚያልቁ ምንባቦችን በማቅረብና ተማሪዎቹ እንዲ ለማመዱ በማድረግ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ማዳበር ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር በዘጠነኛው ክፍል መጽሐፍ ላይ ካሉት ምንባቦች ውስጥ አጭር የተባለው ሁለት ገጽ ያለው ሲሆን፣ ይሄም ከገጽ 1 - 2 ‹‹የቋንቋ መሠረተ ሐሳቦች›› በሚል የቀረበው ነው፡፡ ሌላው ረጅም የሚባለው ደግሞ ከገጽ 122-126 ‹‹የመንደሩ መርፌ ወጊ›› በሚል የቀረበው ተውኔትና ሌሎችም ይገኛሉ፡፡ የመጀመሪያው ሁለት ገጽ ሲሆን፣ የቀረበውም በመጽሐፉ መጀመሪያ ላይ ነው፡፡ ከሦስት እስከ አራት ገጽ ያላቸው የቀረቡት ደግሞ ቀጥለው ነው፡፡ ይህም በምሁራኑ ገለጻ መሠረት አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ለማዳበር ፋይዳ እንዳላቸው መረዳት አያዳግትም፡፡

በምንባቦቹ ውስጥ የተካተቱትን ርዕሰ ጉዳዮች ስናይም ‹‹የቋንቋ መሠረተ ሐሳቦች››፣ ‹‹የጊዜ አጠቃቀም››፣ ‹‹የመንደሩ መርፌ ወጊ›› አጭር ልቦለድ፣ ዘገባ፣ የሕይወት ታሪክ፣ ታሪክ፣ ግጥም የመሳሰሉ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮችን አካትተው የያዙ ናቸው፡፡ በተጨማሪም ምንባቦቹ ከተለያዩ የንባብ ስልቶች ለምሳሌ ከጥልቅ፣ ከአሰሳ ወዘተ. ጋር የሚያስተዋውቁ ናቸው፡፡ ለዚህም Harris, A. and Sipay, E. (1990፣ 186) ተማሪዎች ጥልቅ ንባብን ሲማሩ ሰፊ ንባብንም ጎን ለጎን ሊማሩ ይችላሉ፤ ይገባልም፡፡ አለያም ጥልቅ ንባብን ከማካሄዳቸው በፊት ግርፍ ንባብን ሊያካሂዱ ይችላሉ በማለት በገለጹት መሠረት አንዱ የንባብ ስልት ከሌላው ጋር ተያይዞ እንደሚቀርብ ይገልጹልናል፡፡

የምንባቦቹ አጻጻፍ ለእይታ ያላቸውን ግልጽነት በተመለከተም የፊደሎች ቅርጽ ሕትመት ሳይሆን፣ ጥራት የሌለው ፎቶ ኮፒ የሚመስልበት ሁኔታ ይገጥመናል፡፡

ቀለም የበዛበት፣ ሌላው ደግሞ ደብዛዛ ሆኖ እናገኘዋለን። በተለያየ የቀለም አይነት መስህብ እንዲኖረው ማድረግ ባይቻል እንኳ ይሄንኑ አንድ አይንት (ጥቁር ቀለም) አመጣጥኖ ማተም ይቻል ነበር። (ለዚህም ከዘጠነኛው ክፍል አማርኛ መማሪያ ላይ ኮፒ ተደርጎ የቀረበውን አባሪ አንድ ይመለከቷል)።

ምንባቦቹ የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች ምን ያህል ግልጽ ናቸው? የሚለውም ከመምህራን በተገኘው መረጃ መሠረት ምንባቦቹ የሚያስተላልፏቸውን መልእክቶች በሚገባ መገንዘብ የሚችሉ አፍ-ፈት ተማሪዎች ሲኖሩ፣ የሁሉንም ምንባቦች ለመገንዘብ የሚቸገሩ ኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች አሉ። ለምሳሌ ስለ ሰዓት አጠቃቀም በተገቢ መንገድ ማወቅ ያለውን ጥቅም አስመልክቶ የቀረበው፣ ህብረት ሐይል ስለመሆኑ የቀረበውን፣ ስለ ሕዝብ ብዛትና የአገር እድገት የቀረበውን ምንባብ ለመገንዘብ ይቻላል። ሆኖም አፍ -ፈቶችና ኢ-አፍ-ፈቶች ቀደም ሲል ሰለሞን (1995) አማርኛን በተፈጥሯዊ መቸት የመልመድ ዕድል እየጠበበ በመማር ብቻ የሚገኝ እንደሚሆን በገለጹት መሠረት (በተለይም በገጠርና በከተማ የሚኖሩት) በእኩል ደረጃ ይረዷቸዋል ለማለት ያስቸግራል። ለዚህም ቀደም ሲል ቋንቋውን መማር የሚጀምሩበት ደረጃ መለያየት፣ በቋንቋው የመጠቀም ደረጃ ልዩነት የሚፈጥረው ልዩነት መሆኑን ቀደም ሲል መጠቀሱን ያስታውሷል።

በሌላም በኩል የፈጠራ ሥራዎች አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር የራሳቸው ፋይዳ እንዳላቸው በነሱም አዳዲስ ቃላትን የሐሳብ አወራረድንና አደረጃጀትን መማር እንደሚቻልና ለፈጣን የአነባበብ ስልት መዳበር ከፍተኛ ድጋፍ እንዳላቸው አለም (1995) የፃፉትን በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ተመልክተናል። በተጨማሪም በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ተማሪዎች የፈጠራ ሥራው አስማሚ መልእክት ላይ ለመድረስ በሚያደርጉት ደጋግሞ የማንበብ፣ የቃላትንና የሐረጎችን አውዳዊ ትርጓሜ የማውጣት ወዘተ. ሂደት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንደሚያተቡ ወንድወሰን (1995) የገለጹት ተመልክቷል። ከነዚህ አገላለጾችም የፈጠራ ሥራዎች አንብቦ መረዳትን ለማስተማር ያላቸው አገልግሎት ከፍተኛ መሆኑን ነው። በዘጠነኛው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥም ታዲያ የፈጠራ ሥራዎች ተካትተው እናገኛለን። ይሄውም ቀደም ሲል በሠንጠረዥ አንድ ለማመልከት እንደተሞከረው ሦስት አጫጭር ልቦለዶች እነሱም ‹‹አንቻቦ››፣ ‹‹ተማሪው››፣ ‹‹የመጽሐፍ ጥራት›› በሚሉ ርዕሶች የቀረቡ ሲሆኑ፣ ‹‹ያ... ደራሲ››ና ‹‹በስንኝ ቋጠሮ›› የሚሉ ሁለት ግጥሞች፣ እንዲሁም ‹‹የመንደሩ መርፌ ወጊ›› በሚል ርዕስ የቀረበ ተውኔት በጠቅላላው ከአስራ

አምስት ምንባቦች ውስጥ ስድስቱ የፈጠራ ሥራዎች ሆነው እናገኛቸዋለን። ስለሆነም ለዘጠነኛ ክፍል የቀረቡት ምንባቦች የቃላትንና የሐረጎችን አውዳዊ ትርጓሜ ለማወቅ፣ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች ውስጥ የበኩላቸውን እገዛ እንደሚያደርጉ መገመት አያስቸግርም።

ሌላው ፈሊጣዊ፣ ምሳሌያዊ፣ ዘይቤያዊ ወዘተ. አነጋገሮች አንብቦ መረዳትን በማስተማር በኩል እገዛ እንደሚያደርጉ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ። እነዚህ በምንባቦቹ ውስጥ መካተታቸውን ስንፈትሽ ‹‹የጊዜ አጠቃቀም›› በሚለው ርዕስ ከገጽ 5-7 ና ‹‹አንቻቦ›› በሚለው ከገጽ 18-21- ባሉት ውስጥ ለምሳሌ፡ - ‹‹የቀጠሮ አከባበራችን ብዙ ጊዜ ተመዝኖ ‹የአበሻ ቀጠሮ› በሚል ተቀጽላ መጠራቱ የአደባባይ ምስጢር ሆኗል።›› (ገጽ ‹5) - ‹‹በሰዓቱ ተገኝቶ ዕውቀት ከሚቀስመው ተማሪ፣ አውራ መንገድ ላይ ተኮልኩሎ ፀሐይ የሚሞቀውና አላፊ አግዳሚውን የሚዘልፈው ይበረክታል።›› (ገጽ 7) - ከዚህ በተጨማሪም ‹‹አንቻቦ›› በሚለው ርዕስ ከገጽ 18-21 ከቀረቡት ውስጥ ስናይ፡ - ‹‹በዐይነ ሕሊና አያት-ጋዘርን።›› (ገጽ 18) ‹‹እንደአብዛኞቹ የሙርሲ ልጃገረዶች ረዘም፣ ፈርጠም ያለች፣ ከንፈሯ ደም እንደቋጠረ ሥጋ ያላበጠ፣ ጥርሷ ከንፈሯን አልፎ ያላገጠጠ፣ በጥቁር አካሏ ላይ በስሱ የሚፍለቀለቅ በረዶ መሣይ ጥርስ ያላት አይናማ ልጅ ነበረች፣ ያኔ ሲያውቃት።›› (ገጽ 18) ወዘተ. የሚሉትን ከሁለቱ ምንባቦች ውስጥ ተቀንጭበው የተወሰዱትን መመልከቱ ምንባቦቹ እጅግ በርካታ የሆኑ የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን አነጋገሮች ማካተታቸውን ማየት ይቻላል።

በዚህ በዘጠነኛው ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች የይዘት ግልጽነትና ተስማሚነት አስመልክቶ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ በምሁራን የቀረቡትን ትውረቶች መሰረት በማድረግ ለመፈተሽ ተሞክሯል። በዚህ መሰረትም ምንባቦቹ የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን ያካተቱ፣ እውናዊ፣ የቋንቋ አጠቃቀማቸውም ዕለት በዕለት በአካባቢው አገልግሎት ላይ ከሚውለው ጋር በተለይ አማርኛ አፍ መፍቻቸው ለሆኑት ተስማሚ መሆኑን ለማየት ተችሏል። ምንባቦቹ ወቅታዊ፣ የተለያዩ ርዕስ ጉዳዮችን የሚዳስሱና ርዝመታቸው ለተማሪው ተስማሚ ከመሆናቸውም በላይ ተማሪውን ከተለያዩ የንባብ አይነቶች (ጥልቅ፣ ግርፍ፣ አሰሳ ወዘተ.)ጋር የሚያስተዋውቁ ናቸው። የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን እንደፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊና ምሳሌያዊ አነጋገር በተገቢው መጠን ያካተቱ

ምንባቦች በመቅረባቸው የተማሪውን ፍላጎት በማነቃቃት አንብቦ የመረዳትን አላማ ለማሳካት ብቃት እንዳላቸው አጥኚው ተመልክቷል።

ይሁንና በጣም ጥቂት የሆኑ ለደረጃው የሚከብዱ መኖራቸው፣ አንዳንድ አፍ-ፈቶችንና ኢ-አፍ ፈቶችን በእኩል ደረጃ ለማስተማር ችግሮች እንደሚያጋጥሙ (ሰለሞን 1995፣14ን ይመለከቷል)፤ እንዲሁም በህትመት በኩል ያሉት ችግሮችም በትምህርቱ ላይ የሚያሳድሩት የራሳቸው አሉታዊ ተጽዕኖዎች እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው።

## 4.1.2. የመልመጃዎች አቀራረብ ባህርይ

ለምንና እንዴት እንደሚያነቡ የሚያውቁ ተማሪዎችን ለማፍራት የሚያግዝ የንባብ ትምህርት፣ ተማሪውን ከቀረበለት ምንባብ ጋር መስተጋብር ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎ-ችን የሚያመቻቹ የቅድመ ንባብ፣ የጊዜ ንባብና የድህረ ንባብ ክንዋኔዎችን ቢያካትቱ ጥሩ ነው። ተማሪው አንብቦ የመረዳት ችሎታውን እንዲያዳብር በቅድሚያ ያለፈ (ቀደምት) እውቀቱን ወደ ምንባቡ በማምጣት የቀረበለትን ጽሑፍ ይዘት የመተንበይ ችሎታውን ማዳበር የሚያስችሉ ክንዋኔዎች መኖር አለባቸው። በተጨማሪም አንብቦ የመረዳትን ክሂል የሚያዳብሩ መልመጃዎች ለትምህርቱ ድጋፍ በሚሰጡበት መንገድ ቢዘጋጁ ተማሪዎችን በፍላጎታቸው እንዲያነቡ ይገፋፋቸዋል። እንዲሁም ተማሪዎቹ የአንድን ጽሑፍ ሀሳብ ተረድተው የሚፈልጉትን መረጃ የሚያገኙበትን መንገድ የሚያለማምዱ፣ ግልጽና ከመረጃዎ-ች በመነሳት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ የሚመለሱ ሊሆኑ ይችላሉ።

አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር የሚቀርቡ መልመጃዎች በድህረ ንባብ ሊከወኑ ከሚገባቸው ጥያቄዎች በስተቀር ከንባብ በፊት በማቅረብ ልጆቹን የሚያሳትፉ ሊሆኑ እንደሚገባ Ur (1996) በገለጹት መሠረት የዚህ ትምህርት አቀራረብም ሲታይ ከጠቅላላው 15 ምንባቦች ውስጥ 12 (80%) ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ሲኖራቸው፣ 3(20%) ብቻ የላቸውም። በምዕራፍ ሁለት ውስጥ እንዳየነው በቅድመ ንባብ ደረጃ መካሄድ ያለባቸው ክንዋኔዎች የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ለማነቃቃት፣ ቀደምት እውቀታቸውን ከጽሑፉ ይዘት ጋር ለማሰናሰልና የምንባቡን ፍሬ ሐሳብ እንዲገምቱ ማስቻል ነው። በአጠቃላይ ተማሪዎችና መምህራን ለዋናው ትምህርት ራሳቸውን የሚያዘጋጁበትና ራሶቸውን ከምንባቡ ጋር የሚያስተዋውቁበት ትምህርት ነው ማለት ይቻላል። ታዲያ በዘጠነኛው ክፍል መጽሐፍ

ውስጥ በአብዛኛው ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች መቅረባቸው ብቻ ሣይሆን፣ ከላይ የተጠቀሰውን አላማ የሚያሳኩ ናቸው ወይ? ሲባል ገጽ-1- ‹‹የቋንቋ መሠረተ ሐሳቦች›› በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ በፊት የቀረቡትን፡ - ‹‹ቋንቋ ምንድ ነው?›› የሚለውንና ‹‹ቋንቋ እንዴት ተጀመረ?›› እንዲሁም ገጽ 18 ‹‹አንቻቦ›› በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባብ ቀድመው የቀረቡትን፡- ‹‹በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ዘርዝሩ፡፡››ና ‹‹ጋብቻ በተጋቢዎች ፈቃደኝነት ላይ ካልተመሰረተ ምን ችግር ይፈጠራል?›› ወዘተ. የሚሉትን ለአብነት ያህል ብናይ የቀረቡት ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች የተማሪዎችን ቀደምት እውቀት ከጽሑፎች ይዘቶች ጋር በማስናሰልና በማነቃቃት የምንባቦቹን ፍሬ ሐሳቦች እንዲገምቱ የሚያስችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሌላ አባባል እነዚህ ክንዋኔዎች በምንባቡ ውስጥ የሚነሱ አለያም ምንባቦቹ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች በመሆናቸው ከንባብ በፊት መቅረባቸው ተማሪው ቀደምት እውቀቱን ከምንባቡ ሐሳብ ጋር እንዲያዛምድ፣ ጽሑፉን እንዲገምት የሚረዱ ናቸው፡፡

አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ከጠቅላላ የምንባቡ ክፍል መውጣት አለባቸው እንጂ ከተወሰነ ክፍል ብቻ መውጣት የለባቸውም፡፡ ምክንያቱም ከተወሰነ ክፍል ብቻ የሚወጡ ከሆኑ ተማሪው ምንባቡን ሙሉ በሙሉ እንዲያነብ አይጋብዙትም፡፡ ከዚህ አኳያ በዘጠነኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ካሉት ምንባቦች የወጡት ጥያቄዎች በአብዛኛው የምንባቦቹን ክፍሎች የሚዳስሱ ናቸው፡፡ ለምሣሌ «የቋንቋ መሰረተ ሐሳቦች» ከሚለው ምንባብ ከገጽ 2--3

1. ‹‹እስከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ስለቋንቋ የነበረው አመለካከት ምን ይመስል ነበር?››

2. ‹‹ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኂላ ስለቋንቋ የተሰጠው አመለካከት ምን ይመስላል?›› በተጨማሪም ‹‹ድር ቢያብር ›› በሚል ርዕስ ከገጽ 32-33 ካለው ምንባብ ገጽ -34 የወጡትና በፊደል ተራ፡ -

መ. ‹‹ፋታ የማይሰጥ ተልእኮ ምንድ ነው--››

በ. ‹‹ የምንባቡ ዋና መልእክት ምንድ ነው--›› ወዘተ. የሚሉት ጥያቄዎች የምንባቦቹን ክፍሎች የሚዳስሱ ከመሆናቸውም በላይ አንብቦ መረዳትን ለማዳበር የሚቀርቡ ጥያቄዎች ምንባቡን ባላነበበ ተማሪ የሚመለሱ መሆን የለባቸውም በማለት በምእራፍ ሁለት በምሁራን የቀረበውን መስፈርትም እንደሚያሟሉ ከመምህራን ከተገኘው መረጃ ና ከመጽሐፉ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም ጥያቄዎቹ እንደ ምንባቦቹ ሁሉ እውናዊ (Authentic) መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡

አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ለማዳበር ከሚያገለግሉ የጥያቄ አይነቶች ውስጥ ቀጥተኛ ጥያቄዎች ይገኛሉ። እነዚህ የጥያቄ አይነቶችም ተማሪው ብዙም ሳይመራመር ከሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ የተጠየቀውን ነገር በቀላሉ ለመመለስ እንዲችል የሚያግዙ፣ ባነበበው ምንባብ ላይ በቀጥታ የተገለጹትን እንዲያስተውል ወይም እንዲለይ የሚጠይቁ አጫጭር መልሶችን የሚፈልጉ ናቸው። እነሱም እንዴት?፣ የት?፣ መቼ?፣ ወዘተ. በመሳሰሉት መንገዶች ጥያቄ የሚያቀርቡ መሆናቸውን McDonough and Shaw (2003፣ 110) በመጥቀስ በቀጥተኛ የጥያቄ አይነቶች ውስጥ የሚካተቱትን ጭምር በክለሳ ድርሳን ውስጥ ተመልክቷል። እነዚህ የጥያቄ አይነቶች በተተኳሪው መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ጠቅላላ አንብቦ የመረዳት 230 ጥያቄዎች ውስጥ (አባሪ ሁለትን ይመለከቷል) ግልጽና ያልተሸፈኑ 89 (38.7%) ናቸው። እንዲሁም አንብቦ የመረዳትን ክሂል ለማዳበር ከሚረዱት ውስጥ አውዳዊ ፍችን ለማገናዘብ የሚረዱ ጥያቄዎች ይገኙበታል። ለዘጠነኛ ክፍል ከቀረቡት ምንባቦች አውዳዊ ፍችን የሚጋብዙት ከጠቅላላው አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ውስጥ 105 (45.65%) ተካትተዋል። እነዚህ የጥያቄ አይነቶች በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡበት መጠን ከፋይዳቸው አኳያ በቂና ተመጣጣኝ መሆናቸውን አጥኚው ተመልክቷል።

ሌሎች በምንባቡ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት እንዲሁም በምንባቦቹ ውስጥ ባሉ አረፍተ ነገሮች መካከል ስላሉ ዝምድናዎች የሚጠይቁ ጥያቄዎችም አንብቦ መረዳትን ለማዳበር ከፍተኛ የሆነ ድርሻ እንደሚሰጣቸው Mei-yun, y. (1996፣ 183) ሲገልጹ፣ ብዙውን ጊዜ የምንባቦች ይዘትና ቅርጽ የሚገለፀው በአያያዦች ነው። ይሄውም አያያዦች ምክንያትና ውጤትን፣ የድርጊቶችን ቅደም ተከተል ወዘተ. ስለሚጠቁሙ አንብቦ መረዳትን ለማዳበር የሚያስችሉ ሐሳቦችን ጠቋሚዎች ናቸው ብለው ነበር። እንዲሁም Nuttall (2000፣ 28) አንብቦ መረዳት የጽሑፉን ቅደም ተከተላዊ የሐሳብ አገላለጽ፣ አንዱ አረፍተነገር ከፊተኛውና ከተከታዩ ጋር ያለውን የሐሳብ ግንኙነትና ግጥምጥምነት የሚፈጥሩ አያያዦች የጸሐፊው ሐሳብ የሚንፀባረቅባቸው በመሆናቸው ሊተኮርባቸው የሚገቡ ናቸው። ሆኖም በዘጠነኛው ክፍል ለአንብቦ መረዳት ትምህርት በቀረበው ውስጥ የዚህ አይነት ምንም ጥያቄ አልተካተተም።

ለአንብቦ መረዳት ትምህርት ከሚቀርቡ የጥያቄ አይነቶች ውስጥ የተነበበውን ምንባብ ጸሐፊው ለምንና ለማን እንደጻፈው ለመገምገም የሚያስችሉ ናቸው። ተማሪዎቹ የምንባቡን

መልዕክት ምን ያህል እንደተረዱት የሚጠይቅና የመሰላቸውን ሐሳብ የሚሰነዝሩባቸው የጥያቄ አይነቶች ከመሆናቸውም በላይ ለሚሰነዝሩት ምላሽ ተጨባጭ ምክንያቶችን እንዲያመላክቱ የሚጠይቁ ጭምር መሆቸውን በምዕራፍ ሁለት ተመልክተናል። ሆኖም እነዚህ የጥያቄ አይነቶችም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ውስጥ ተካትተው አይታዩም (አባሪ ሁለትን ይመለከቷል)።

በክለሳ ድርሳን ውስጥ Marani (1997፣ 72) የጊዜ ንባብ ጥያቄዎች የልጆቹን ችሎታ ለማጎልበት ከቀረበው ምንባብ ውስጥ ፍሬ ሐሳቡን እንዲገምቱ ፍንጭ የሚያሳዩ ጥያቄዎች ከቀረቡ ከሚያነቡት ጽሑፍ ጋር እያዛመዱ በጥረታቸው መልዕክቱን ፈልፍለው የማውጣት ችሎታቸውን እንዲያብራሩ ያስችላሉ። ስለዚህ በዘጠነኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥም የዚህ አይነት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለምሳሌ፡ - ገጽ - 51 ፊደል ተራ ሐ ‹‹ሕዝብ የአንድ ሀገር ሐብት የሚሆነው እንዴት ነው?››፣ ገጽ -82 ተ.ቁ 1 ‹‹ምንባቡን ቀደም ሲል በገጽ 50 ላይ ካነበባችሁት ጽሑፍ የሚለየው ባህሪ ምንድ ነው?››፣ ገጽ 91 ፊደል ተራ ሠ. ‹‹ምንባቡ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድ ነው?›› እነዚህን ጥያቄዎች መምህራን ከምንባቡ በፊት ጥቁር ሰሌዳው ላይ በመጻፍ እያነበቡ መልሶቻቸውን እንዲያገኙ ወይም በየምንባቡ ጣልቃ ወዘተ. ሊጠይቁ ይችላሉ።

እንዲሁም Day and Bamford (2002) የድህረ ንባብ ትምህርት የተነበበውን ምንባብ ማጠቃለልና ምንባቡን ከተማሪዎች ዕውቀት፣ ዝንባሌ ጋር ማዛመድ ነው። በተጨማሪም ለዚህ ደረጃ ትምህርት ተገቢ ናቸው ተብለው ከሚታመንባቸው ውስጥ ውይይት፣ ክርክር ይገኙበታል። እነዚህ የጥያቄ አይነቶች በዚህ ትምህርት ውስጥም ይገኛሉ። ለምሳሌ፡ - ገጽ 51 ፊደል ተራ ሠ. ‹‹በምንባቡ ውስጥ ከተዘረዘሩት ሌላ ለቤተሰብ ምጣኔ የሚረዱ ተጨማሪ መፍትሔዎች ይኖሩ ይሆን? ካሉ በቡድን ተወያዩና ዘርዝሯቸው››፣ ገጽ 74 ፊደል ተራ ሠ. ‹‹ከዚህ አሳዛኝ ታሪክ ምን መማር ይቻላል?››፣ ገጽ- 82 ተ.ቁ. 4 ‹‹ጽሑፉ በማን ለማን የተጻፈ ነበር?›› በዚህ አይነት የጊዜ ንባብና የድህረ ንባብ ትምህርቶች በሚገባ በመጽሐፉ ውስጥ ተካትተዋል ማለት ይቻላል።

የትምህርት ይዘቶች ለሚፈለገው ትምህርትና ደረጃ የታለመውን ግብ እንዲመቱ ለተማሪዎች ግልጽና ተስማሚ ሆነው በበቂ ሁኔታ በመልመጃዎች ተጠናክረው ከቀረቡ የታሰበውን ዓላማ

ከግብ ለማድረስ አስተማማኝ ይሆናሉ፡፡ ታዲያ በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ክሂሎች አንጻር ይበልጥ ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው ክሂል እንደሆነ ከሚከተለው ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ -2- በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች የወጡ መልመጃዎች መጠን

| ተ.ቁ. | የክሂልና የዕውቀት አይነት | ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | አንብቦ መረዳት | 230 | 33.92 |
| 2 | ማዳመጥ | 29 | 4.78 |
| 3 | መናገር | 70 | 10.32 |
| 4 | መጻፍ | 85 | 12.54 |
| 5 | ሰዋሰውና ቃላት | 203 | 29.94 |
| 6 | ሥነ ጽሑፍ | 61 | 9 |
| | ጠቅላላ ድምር | 678 | 100 |

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት ከያንዳንዱ መልመጃዎች ውስጥ 230 (33.92-) አንብቦ የመዳት ጥያቄዎች ናቸው (አባሪ ሁለትን ይመለከቷል)፡፡ በዚህም ከያንዳንዱ ክሂል አኳያ ሲታይ የተሻለ ትኩረት ተሰጥቶታል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ንባብን ከንግግርና ከጽሑፍ ጋር የሚያገናኙ ናቸው፡፡ ማለትም ጥያቄዎቹ የሚመለሱት በቃል ወይም በጽሑ ስለሆነ እግረመንገዳቸውን የመናገርና የመጻፍ ክሂልንም ማዳበራቸው አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ለአንብቦ መረዳት የቀረቡት ጥያቄዎች በምን እንዲመለሱ እንደተደረገ ለማየት እንዲያመች ቀጥሎ በሠንጠረዥ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 3 በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች

| ተ.ቁ | የሚመለስበት መንገድ | ጠቅላላ ድምር በቁጥር | መቶኛ |
|---|---|---|---|
| 1. | በቃል እንዲመለሱ የቀረቡ | 83 | 36.08 |
| 2. | በጽሑፍ እንዲመለሱ የቀረቡ | 20 | 8.7 |
| 3. | በቃል ወይም በጽሁፍ እንዲመለሱ የቀረቡ | 4 | 1.74 |
| 4. | በምን እንደሚመለሱ ያልተገለፀ | 123 | 53.48 |
| ጠቅላላ ድምር | | 230 | 100 |

በሠንጠረዥ 3 ላይ እንደሚታየው ከቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ 36.08% በቃል እንዲመለሱ፣ 8.7% በጽሑፍ እንዲመለሱ፣ 1.74% በቃል ወይም በጽሑፍ እንዲመለሱ፣123(53.48%) ደግሞ በቃል ወይም በጽሑፍ እንዲመለሱ በግልጽ የማያዙና መልስ እንዲሰጥባቸው ብቻ የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች የንባብ ክሂልን ብቻ ሳይሆን፣የንግግርና የጽህፈት ክሂልንም እግረ መንገዳቸውን የሚያዳብሩ ናቸው።

## 4.2. ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.2.1. በመጠይቁ ክፍል አንድ በቀረቡት ጥያቄዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች

ሠንጠረዥ 4 መጠይቁን የሞሉት መምህራን ዳራዊ ሁኔታ

| | | የመምህራን ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| ፆታ | ሴት | 6 | 35.3 |
| | ወንድ | 11 | 64.70 |
| | ድምር | 17 | 100 |
| የትምህርት ደረጃ | 12 + 2 | 6 | 35.3 |
| | 12+ 3 | 3 | 17.65 |
| | 12+ 4 | 8 | 47.05 |
| የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት | አማርኛ | 17 | 100 |
| | ሌላ | - | - |
| | ድምር | 17 | 100 |
| የአገልግሎት ዘመን | ከ1-5 ዓመት | 3 | 17.65 |
| | ከ6-10ዓመት | 2 | 11.76 |
| | ከ11-15ዓመት | 5 | 29.41 |
| | ከ16-20 ዓመት | 3 | 17.65 |
| | ከ21-25 ዓመት | 2 | 11.76 |
| | 26 ዓመትና በላይ | 2 | 11.76 |
| | ድምር | 17 | 100 |

ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም መጠይቁን በመሙላት የተሳተፉት መምህራን ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት የተመረቁ መሆናቸውን ከምላሻቸው ማወቅ ተችሏል። እንዲሁም አብዛኞቹ (70.6%) መምህራን አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ከፍተኛ ልምድ ያካበቱ በመሆናቸው፣ ጠቃሚ መረጃ ሊሰጡ እንደሚችሉ ይገመታል።

### 4.2.2. በመጠይቁ ክፍል ሁለት ከቀረቡት ጥያቄዎች የተገኙ መረጃዎች ትንተና

#### 4.2.2.1. ምንባቦቹ ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ችሎታ፣ እድሜና አካባቢ ጋር ስላላቸው ግንኙነት

በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች በማስተማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ከተማሪዎች ፍላጎት፣ችሎታ፣ እድሜና አካባቢ ጋር ስላላቸው ግንኙነት የሚጠይቁ ሲሆኑ፣ በእያዳንዱ ጥያቄ ላይ ከመምህራን የቀረበውን ምላሽ ከቀጣዩ ሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

ሠንጠረዥ -5- ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸውን ተስማሚነት በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምንባቦቹ ርዕሶች የተማሪውን የማንበብ ፍላጎት የማነቃቃት ደረጃ | ብዛት | 7 | 8 | 2 | - | - | 17 |
| | | % | 41.18 | 47.06 | 11.76 | - | - | 100 |
| 2 | ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ መጽሐፍ ይዘው ወደ ክፍል የሚመጡበት ጊዜ | ብዛት | 1 | 1 | 2 | 11 | 2 | 17 |
| | | % | 5.88 | 5.88 | 11.76 | 64.71 | 11.76 | 100 |
| 3 | ምንባቦቹ ያላቸውን አንጊነትና ሌሎች የአማርኛ ጽሑፎችን እንዲያነቡ ፍላጎት የማሳደር ደረጃ | ብዛት | 2 | 8 | 5 | 2 | - | 17 |
| | | % | 11.76 | 47.06 | 29.41 | 11.76 | - | 100 |
| 4 | የምንባቦቹ ርዝመት ለተማሪዎቹ ፍላጎት ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 9 | 7 | 1 | - | - | 17 |
| | | % | 52.94 | 41.18 | 5.88 | - | - | 100 |
| 5 | ምንባቦቹ ተማሪዎችን ለማስደሰት ያላቸው ብቃት | ብዛት | 4 | 8 | 4 | 1 | - | 17 |
| | | % | 23.53 | 47.06 | 23.53 | 5.88 | - | 100 |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ እንደተገለጸው ከጥያቄ ቁጥር አንድ እስከ አምስት ለቀረቡት ጥያቄዎች መምህራን የሰጡት ምላሽ ባብዛኛው አዎንታዊ (ድጋፍ) ነው፡፡ ይሄውም በቁጥር አንድ ለቀረበው ጥያቄ የምንባቦቹ ርዕሶች የተማሪውን የማንበብ ፍላጎት ማነቃቃት እንደሚችሉ ከ 15 (88.23%) መምህራን የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡ ርዕሶቹ የልጆቹን

የማንበብ ፍላጎት የማነቃቃት ደረጃቸው መካከለኛ ነው ያሉትም 2 (11.76%) መምህራን ናቸው፡፡

ተማሪዎች በተለይ አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ለማዳበር የግድ መጽሐፋቸውን ይዘው መገኘት አለባቸው፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ ሁለት እንዳየነው አንብቦ የመረዳት ትምህርት መካሄድ ያለበት በዝምታ ንባብ ስለሆነ፣ ይህንን ተግባር ለማከናወን መጽሐፉ የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህንን አስመልክቶ ለመምህራን ከቀረበው መጠይቅ የተገኘው ምላሽ አሉታዊ ነው፡፡ ስለዚህም መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት ውስጥ ልጆቹ መጽሐፋቸውን ይዘው ይመጣሉ ያሉት2(11.76%) ናቸው፡፡ 13(76.47%) ግን ይዘው እንደማይመጡ አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪው መጽሐፉን ሳይዝ መጥቶ የታሰበውን አላማ ያሳካል ለማለት እንደሚያስቸግር ጠቁመዋል፡፡

በተራ ቁጥር 3 ለመምህራን የቀረበውን ጥያቄ በተመለከተም 10(58.82%) መምህራን ምንባቦቹ በከፍተኛ ደረጃ አጓጊነት፣ ፍላጎትን የማነቃቃት ችሎታ እንዳላቸው መግለጻቸውን የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡ የምንባቦቹ ርዝመት ለተማሪዎቹ ፍላጎት በጣም ተገቢ መሆናቸውን በተራ ቁጥር4 ለቀረበው ጥያቄ የተመዘገበው ምላሽ አረጋግጧል፡፡ ይኼውም መጠይቁን ከሞሉት መምህራን 16(94.12%) በሚሆኑት የተሰጠው ምላሽ ተስማሚነታቸውን ያሳያል፡፡ በ1(5.88%) ብቻ አሉታዊ ምላሽ ተስንዝሯል፡፡

በተራ ቁጥር 5 የቀረበው ጥያቄ ቀደም ሲል በተራ ቁጥር -3- ከቀረበው ጥያቄ ጋር በሐሳብ አንድ ሲሆን፣ የተመዘገበው ውጤትም ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ነው፡፡ ይኼውም የ12(70.59%) መመህራን ድጋፍ በመገኘቱ ውጤቱ በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 6 ምንባቦቹ ለተማሪዎች ችሎታ፣ ዕድሜና አካባቢ ያላቸውን ተስማሚነት በተመለከተ የተሰበሰቡ መረጃዎች

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች ለተማሪው የቋንቋ እውቀት ያላቸው ቀረቤታ | ብዛት | 1 | 3 | 6 | 4 | 3 | 17 |
| | | % | 5.88 | 17.365 | 35.29 | 23.53 | 17.65 | 100 |
| 7 | ምንባቦቹ ለተማሪዎች ዕድሜና አካባቢ ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 3 | 9 | 3 | 2 | - | 17 |
| | | % | 17.64 | 52.94 | 17.64 | 11.76 | - | 100 |
| 8 | በምንባቦቹ ውስጥ የሚገኙት ቃላት ከአካባቢው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 7 | 6 | 2 | 2 | - | 17 |
| | | % | 41.18 | 35.29 | 11.76 | 11.76 | - | 100 |

ሠንጠረዥ 6 - መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ 7(41.18%) በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች ለተሪማው የቋንቋ ዕውቀት ቀረቤታ የላቸውም ማለታቸውን፣ 6(35.29%) ደግሞ ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ዕውቀት ያላቸው ቀረቤታ መካከለኛ ነው ማለታቸውን ያሳያል። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ለተማሪው እውቀት ዕድሜና አካባቢ ያላቸውን ተስማሚነት አስመልክቶ በቅደም ተከተል ከመምህራን የተገኘው መረጃ ሲታይ በተ.ቁ. -6 ለቀረበው በ 7 (41.18%) መምራን የተመዘገበው ውጤት ምንባቦቹ ለተማሪው ልምድ ተስማሚነት የላቸውም፣ በ 6 (35.29%) የተመዘገበው ደግሞ ስምምነታቸው መካከለኛ ነው የሚል ነው። ከዚህ የተገኘው ውጤትም አዎንታዊ ወይም አሉታዊ መሆንን አያመለክትም። በዚህ በኩል መምህራን መጠራጠራቸውን አመላካች ምላሽ ተገኝቷል።

በተጨማሪም በተ.ቁ. -7 ‹‹ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ዕድሜና አካባቢ ያላቸውን ተስማሚነት›› በተመለከተም 12(70.59) በከፍተኛ ደረጃ፣ 2(11.76%) በዝቅተኛ ደረጃ፣ 3(17.65%) ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ተስማሚ መሆናቸውን ከሰጡት ምላሽ ገልጸዋል። በምንባቦቹ ውስጥ የሚገኙት ቃላት በአካባቢው ካለው የቋንቷው አጠቀቀም ጋር በከፍተኛ ደረጃ እንደሚስማሙ በሠንጠረዥ -6- ተ.ቁ. 8- ለቀረበው ጥያቄ መምህራን ከሰጡት ውጤት መረዳት ተችሏል።

ሠንጠረዥ 5 እና 6 ስር ለመምህራን ከቀረቡት መጠይቆች ውስጥ በጣም ከፍተኛ የሚል መልስ የተሰጠው በተ.ቁ. 4 «የምንባቦቹ ርዝመት ለተማሪዎቹ ፍላጎት ያላቸው ተገቢነት»

የሚለው ሲሆን፣ ይህም 16(94.12%) መምህራን ከሰጡት ምላሽ ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም በተራ.ቁጥር -1- የምንባቦቹ ርእሶች የተማሪውን የማንበብ ፍላጎት የማነቃቃት ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን 15(88.24%) መምህራን የሰጡት መረጃ ያመለክታል። ሌሎቹም ቢሆኑ የማይናቅ ከፍተኛ ውጤት የተሰጣቸው አሉ። ለምሳሌ በተ.ቁ 8 የቀረበው 13(76.47%) ፣ በተ.ቁ.-7 የቀረበው 12(70.58%) ወዘተ.

በሌላ በኩል በጣም ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ (በጣም ዝቅተኛ) የተገኘው በተ.ቁ..2 «ተማሪዎቹ የአማረኛን ቋንቋ መጽሐፍ ይዘው የሚመጡበት ጊዜ» የሚለው ነው። ለዚህ ጥያቄ ተማሪዎቹ በፍጹም መጽሐፋቸውን ይዘው እንደማይመጡ የ 13(76.47%) መምህራን ውጤት አመልክቷል። አንብቦ የመረዳት ትምህርትን ለማስተማርም ሆነ ለመማር መጽሐፍ ከሌለ ችግር ማጋጠሙ አይቀሬ መሆኑን ከምላሻቸው መረዳት ይቻላል። በምእራፍ ሁለት ምንባቦቹ ለተማሪው ፍላጎት፣ ችሎታ ወዘተ. የሚሰማሙ ከሆኑ የልጆቹ የመማር ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚነቃቃ ተገልጿል። በዚህ ክፍል ከቀረቡትም ባብዛኛው መምህራን ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ችሎታ፣ወዘተ. ተስማሚ ናቸው።

### 4.2.2.2. የምንባቦች ይዘቶች ግልጽነትና ተስማሚነት

የሚቀርቡት የምንባብ ትምህርት ይዘቶች በደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች እድሜ፣ ስሜት፣ ወዘተ. የሚስማሙ መሆን አለባቸው። የማይከብዱ፣ የማይቀሉ፣ ስሜታቸውን የሚማርኩና ፍላጎታቸውን ያገናዘቡ መሆን ይገባቸዋል። በቃላት፣ በሰዋስው አጠቃቀም ስርዓትን የጠበቁና ግልጽ መሆን እንዳለባቸው Cunningsworth (1995፣ 75) መግለጻቸው በክለሳ ድርሳን ተመልክቷል። ከዚህ አኳያ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ምን እንደሚመስሉ እንመልከት።

ሠንጠረዥ -7 የምንባቦችን ይዘቶች ግልጽነት አስመልክቶ የተሰበሰቡ መረጃዎች

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የምንባቦቹ አረፍተ ነገሮች ግልጽነት | ብዛት | 7 | 9 | - | 1 | - | 17 |
| | | % | 41.18 | 52.94 | - | 5.88 | - | 100 |
| 10 | የምንባቦቹ አጻጻፍ (ቅርጽ) ለእይታ ያለው ግልጽነት | ብዛት | - | 3 | 2 | 6 | 6 | 17 |
| | | % | - | 17.65 | 11.75 | 35.29 | 35.29 | 100 |
| 11 | ምንባቦቹ የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች የግልጽነት ደረጃ | ብዛት | 4 | 5 | 5 | 3 | - | 17 |
| | | % | 23.53 | 29.41 | 29.41 | 17.65 | - | 100 |
| 12 | ምንባቦቹ የተሟላ (ቁንጽል ያልሆነ) ግልጽ መልክእት ለማስተላለፍ ያላቸው ብቃት | ብዛት | 6 | 9 | 2 | - | - | 17 |
| | | % | 35.29 | 52.94 | 11.76 | - | - | 100 |

በሠንጠረዥ 7- ላይ እንደሚታየው የአብዛኞቹ 16(94.12%) መምህራን እምነት በምንባቦቹ ውስጥ የሚገኙት አረፍተነገሮች በከፍተኛ ደረጃ ግልጽ ናቸው፡፡ ቀጥሎም በተራ ቁጥር 10 - ለቀረበው ጥያቄ 12 (70.58%) መምህራን የምንባቦቹ አጻጻፍ ለእይታ ግልጽ አለመሆናቸውን በሰጡት ምላሽ ሲያመለክቱ፣ 3(17.65%) ያህሉ ብቻ ግልጽ ናቸው በማለት መልሰዋል፡፡ በተራ ቁጠር 11 - ምንባቦቹ የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች የግልጽነት ደረጃ በሚል ለቀረበውም የ9(52.94%) መምህራን ምላሽ ምንባቦቹ በከፍተኛ ደ፝ጃ ግልጽ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ እንዲሁም ምንባቦቹ የተሟላ (ቁንጽል ያልሆነ) ግልጽ መልእክት የማስተላለፍ ብቃት አላቸው፡፡ ምክንያቱም መጠይቁን ሞልተው ከመለሱት መምህራን መካከል አስራ አምስቱ (88.23%) ምንባቦቹ ግልጽ መልእክት የማስተላለፍ ብቃት እንዳላቸው ጠቁመዋል፡፡ በዚህ ተላውጦ ስር ከቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኞቹ በከፍተኛ ደረጃ ወይም ምንባቦቹ ግልጽ ናቸው የሚሉ ቢሆኑም፣ የምንባቦቹ አጻጻፍ ቅርጽ ለእይታ እንደማይመች መምህራን አልደበቁም፡፡ የምንባቦቹ አጻጻፍ ለእይታ አልተመቸም ማለት ደግሞ ተማሪዎቹን ለንባብ አያነቃቃም ማለት ነው፡፡ የመነቃቃት አለመኖር ደግሞ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ በምሁራን እንደተገለፀው አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በቋንቋ መማሪያነት የሚቀርቡ ምንባቦች የቋንቋውን አጠቃቀም ስርዓት ካላሟሉ፣ ተማሪው በትምህርቱ ላይ አሉታዊ አመለካከት እንዲያዳብር አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ስለዚህ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርቡ ምንባቦች (ከስህተቶች ተነስቶ ትክክለኛውን አጠቃቀም ለማስተማር ካልተፈለገ በስተቀር) የቋንቋን ሕግ ማሟላት አለባቸው። ከዚህ አኳያ መምህራን በተራ ቁጥር 15 ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምስክርነት ምን ይመስላል? ሲባል 13(76.47%) ያህሉ ምንባቦቹ የቋንቋውን ስርዓት በመጠበቅ በኩል ያላቸው ብቃት ከፍተኛ መሆኑን አሳይተዋል። 4(23.53%) ያህሉ ደግሞ ያላቸው ስርዓት የመጠበቅ ብቃት መካከለኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

ምንባቦቹ ከአካባቢው የመገኘታቸውን ሁኔታ በተመለከተ በተራ ቁጥር 16- ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን በመሙላት ከተሳተፉት መምህራን 12(70.58%) ማለትም አብዛኞቹ የሰጡት ምላሽ መጽሐፉ በነፍስ ወከፍ እንደሚዳረስ ያመለክታል። 5(29.41%) ያህሉ ብቻ በመካከለኛ ደረጃ እንደሚገኙ አሳይተዋል። ከዚህም ልጆቹ ምንባቦቹን ከአካባቢያቸው ያለምንም ችግር ማግኘት እንደሚችሉ መረዳት አያስቸግርም። በተጨማሪም ምንባቦቹ አዳዲስ ነገሮችን ለማስተማር ያላቸውን ብቃት አስመልክቶ በተራ ቁጥር 17 ለቀረበላቸው መጠይቅ 14(82.35%) መምህራን ምንባቦቹ አዳዲስ አረፍተ ነገሮችን፣ አገባብን እንደሚያስተምሩ ይገልጻል። 2(11.76%) ያህሉ ደግሞ አዳዲስ አረፍተ ነገሮችን የማስተማር ብቃታቸው ዝቅተኛ ነው፤ 1(5.88%) የሚሆኑት ያላቸው ብቃት መካከለኛ መሆኑን ከሰጡት ነጥብ መረዳት ተችሏል። ስለዚህ ለዚህ ጥያቄ የተገኘው ውጤት ምንባቦቹ አዳዲስ ነገሮችን እንደሚያስተምሩ አመላክቷል።

በተጨማሪም ከምንባቦቹ የሚገኙት ዕውቀቶች በተፈለገው ቦታና ጊዜ ሊተገበሩ እንደሚችሉ 9(52.94%) መምህራን፣ 3(17.65%) ደግሞ ሁሉም በተፈለገው ቦታና ጊዜ ሊተገበር እንደማይችል ከሰጡት ውጤት መገንዘብ ተችሏል። በተራ ቁጥር 19 የቀረበው የምንባቦቹን ወቅታዊነት የተመለከተ ሲሆን፣ አብዛኞቹ 13(76.47%) መምህራን የምንባቦቹ ይዘቶች ወቅታዊ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

እንዲሁም በተራ ቁጥር 20 ለቀረበው የ13 (76.47%) መምህራን ምላሽም ምንባቦቹ ያላቸው ክብደት መካከለኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከዚህም ምንባቦቹ ከባድም ሆነ ቀላል የሚባሉ እንዳይደሉ እንረዳለን፡፡

በሠንጠረዥ 8 ላይ ከቀረቡት መጠይቆች አብዛኞቹ የመምህራንን ድጋፍ ያገኙ ሲሆን፣ እነሱም፡ - በተራ ቁጥር 14ና 17፣ 15፣ 19ና 20 የቀረቡት በተመሳሳይ ከ 14 (82.35%) ና ከ13 (76.47%) የተገኘው ምላሽ ከቀረቡት ዘጠኝ ጥያቄዎች 5ቱ በጣም ከፍተኛ ውጤት በተራ ቁጥር 13ና 16 የቀረቡት ደግሞ 12 (70.58%) መምህራን በሰጡት ምላሽ በከፍተኛ ደረጃ ምንባቦቹ ብቃት ያላቸውና ወቅታዊ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህ አይነት ከጠቅላላው ዘጠኝ ጥያቄዎች በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች ለተማሪው ተስማሚ ስለሆኑ አንብቦ የመረዳትን ትምህርት የማዳበር ብቃት እንዳላቸው ለሰባቱ ከሰጡት ነጥብ ማወቅ አያዳግትም፡፡ ሆኖም ሁለቱ በተራ ቁጥር 10ና 21 ለሰፈሩት የተገኘው ውጤት በጣም ዝቅተኛ ባይሆንም ከፍተኛ የሆነ ምላሽ አይደለም፡፡

ሠንጠረዥ -9- የምንባቦቹ ይዘቶች የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን ያካተቱ መሆናቸውን

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 22 | ምንባቦቹ ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች (ረጅምና አጭር ልቦለድ፣ ጭውውቶች፣ ግጥሞች፣ ወዘተ.) የተውጣጡበት ደረጃ | ብዛት | 10 | 6 | - | 1 | - | 17 |
| | | % | 58.82 | 35.29 | - | 5.88 | - | 100 |
| 23 | ምንባቦቹ የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን እንደ ምሳሌያዊ፣ ፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊ አነጋገር ያሉትን የያዙበት ደረጃ | ብዛት | 6 | 6 | 4 | 1 | - | 17 |
| | | % | 35.29 | 35.29 | 23.53 | 5.88 | - | 100 |
| 24 | ምንባቦቹ እንደመጻፍ፣ መናገር ወዘተ. ያሉ የተለያዩ ክሂሎችን ለማስተማር ያላቸው ብቃት | ብዛት | 1 | 10 | 5 | 1 | - | 17 |
| | | % | 5.88 | 58.82 | 29.41 | 5.88 | - | 100 |

ከሠንጠረዥ 9 መረዳት እንደሚቻለው በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ ከልዩ ልዩ የጽሑፍ አይነቶች የተውጣጡ መሆናቸውን መምህራን ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡ ይሄውም መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ውስጥ 16 (94.11%) የሚሆኑት ምንባቦቹ ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች የተውጣጡ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡ በምንባቦቹ ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሚጠቀሙባቸው አነጋገሮች በሚገባ መካተታቸውን በተመለከተ

ለቀረበው ጥያቄ 12(70.58%) መምህራን በተገቢው ሁኔታ ተካትተዋል በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ በተጨማሪም ምንባቦቹ የተለያዩ ክሂሎችን ለማስተማር ብቃት አላቸው ተብሎ የተገለጸው በ11 (64.76%) መምህራን ነው፡፡ በሠንጠረዥ -9- ከቀረቡት ሦስት ጥያቄዎች ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምንባብቹ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር ብቃት እንዳላቸው ከመምህራን ምላሽ መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.2.2.3. አንብቦ የመረዳት መልመጃ አቀራረብ

ቀደም ሲል በምእራፍ ሁለት ስር እንደተመለከትነው አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር ታስበው የሚቀርቡ መልመጃዎች ከቋንቋ ችሎታ መዛኝነት ይልቅ የንባብ ግንዛቤን የማጠናከር ባህርይ ሊታይባቸው ይገባል፡፡ አላማቸውም ለንባብ የቀረበው ጽሑፍ የተዋቀረበትን የቋንቋ ክፍሎች ማሳወቅ የለበትም ወዘተ. በማለት የመስኩ ምሁራን ገልጸዋል፡፡ በዚህ መሰረትም በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የምሁራኑን አባባል ያገናዘቡ መሆን አለመሆናቸውን ቀጥለን እንመለከት፡፡

ሠንጠረዥ 10 - በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችን በተመለከተ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | ምንባቦቹ ከመነበባቸው በፊት የሚቀርቡ (ቅድመ ንባብ) የመወያያ ጥያቄዎች የሚገኙበት ደረጃ | ብዛት | 5 | 10 | 2 | - | - | 17 |
| | | % | 29.41 | 58.82 | 11.76 | - | - | 100 |
| 26 | በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት | ብዛት | 3 | 6 | 5 | 3 | - | 17 |
| | | % | 17.65 | 35.29 | 29.41 | 17.65 | - | 100 |
| 27 | ከምንባቡ የወጡት መልመጃዎች ምንባቡን ባላነበበ ተማሪ ሊመለሱ የመቻላቸው ሁኔታ | ብዛት | 2 | - | 1 | 4 | 10 | 17 |
| | | % | 11.76 | - | 5.88 | 23.53 | 53.82 | 100 |
| 28 | የመልመጃዎቹና የትዕዛዞቹ ግልጽነትና ትክክለኛነት | ብዛት | 4 | 5 | 2 | 3 | 3 | 17 |
| | | % | 23.53 | 29.41 | 11.76 | 17.65 | 17.65 | 100 |

ሠንጠረዥ -10- ላይ እንደተመለከተው በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ከመነበባቸው በፊት ያለፈ እውቀትን ለማገናዘብ፣ የማንበብ ፍላጎትን ለመቀስቀስ፣ ተማሪዎችንና መምህራንን ከምንባቦቹ ጋር እንዲተዋወቁ የሚረዱ ጥያቄዎች

መቅረባቸውን መጠይቁን ከሞሉት 17 መምህራን ውስጥ ከ 15 (88.23%) የተገኘው ምላሽ አሳይቷል፡፡ ከመምህራኑ 2(11.76%) ያህሉ ደግሞ ከምንባቦቹ በፊት ያሉት የመወያያ ጥያቄዎች የቀረቡት በመካከለኛ ደረጃ ነው ማለታቸውን ከተመዘገበው ውጤት ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን ጥያቄዎቹ በከፍተኛ ደረጃ ለመቅረባቸው ስምምነታቸውን የገለጹት አብዛኞቹ ናቸው፡፡ መልመጃዎቹ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር ተገቢነት እንዳላቸው 9 (52.94%) ከሰጡት ምላሽ ሲረጋገጥ፣ 3 (17.65%) ለማዳበር ያላቸው አቅም ዝቅተኛ እንደሆነ፣ በተጨማሪም 5(29.41%) አንብቦ የመዳትን ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት መካከለኛ መሆኑን እንዳመለከቱ ከሰጡት ውጤት ማወቅ ተችሏል፡፡ በተራ ቁጥር 27 ለቀረበው ለዚህ ጥያቄ ተማሪዎቹ ምንባቡን ሳያነቡ አንብቦ የመረዳትን መልመጃዎች መስራት እንደሚችሉ 2(11.76%) ሲስማሙ፣ 14(77.35%) ደግሞ ምንባቡን ያላነበበ ተማሪ እነዚህን መልመጃዎች መመለስ እንደማይችል ከተመዘገበው ነጥብ መረዳት ተችሏል፡፡

የመልመጃዎችን ግልጽነትና ትክክለኛነት በተመለከተም 9(52.94%) ትእዛዞቹ ግልጽና ትክክለኛ ናቸው ሲሉ፣ 6(35.3%) ግልጽም ሆነ ትክክለኛ እንዳልሆኑ፤ 2(11.76%) ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ትክክለኛ ና ግልጽ ናቸው ማለታቸውን የሰነዘሩት ውጤት ያሳያል፡፡

ሠንጠረዥ 11- አንብቦ የመረዳት ጥያቄ አይነቶችና አቀራረብ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 29 | አንብቦ በመረዳት መልመጃዎች ውስጥ ግልጽና ያልተሸፈኑ ጥያቄዎች የተካተቱበት ደረጃ | ብዛት | 2 | 8 | 5 | 1 | 1 | 17 |
| | | % | 11.76 | 47.06 | 19.41 | 5.88 | 5.88 | 100 |
| 30 | አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አውዳዊ ፍችን ለማገናዘብ ያላቸው እገዛ | ብዛት | 4 | 8 | 5 | - | - | 17 |
| | | % | 23.53 | 47.06 | 29.41 | - | - | 100 |
| 31 | በምንባቦቹ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ያካተቱ መልመጃዎች የሚገኙበት ሁኔታ | ብዛት | - | 1 | 2 | 4 | 10 | 17 |
| | | % | - | 5.88 | 11.76 | 23.53 | 58.82 | 10 |
| 32 | በምንባቦቹ ውስጥ ባሉ አረፍተ ነገሮች መካከል ስላሉ ዝምድናዎች የሚጠይቁ ጥያቄዎች | ብዛት | - | 2 | 1 | 3 | 11 | 17 |
| | | % | - | 11.76 | 5.88 | 17.65 | 64.71 | 10 |
| 33 | ተማሪዎቹ የምንባቦቹን ሐሳቦች ገምግመው በጽሑፍም ሆነ በቃል በማቅረብ የሚያወያዩ ወይም የሚያከራክሩ ጥያቄዎች የሚገኙበት ደረጃ | ብዛት | - | 3 | 4 | 7 | 3 | 17 |
| | | % | - | 17.65 | 23.53 | 41.20 | 17.65 | 100 |
| 34 | ስለምንባቦቹ የሚጠይቁት መልመጃዎች የተጻፉበት ቋንቋ ምንባቦቹ ለተጻፉበት ቋንቋ ያለው ቀረቤታ | ብዛት | 4 | 6 | 4 | 3 | - | 17 |
| | | % | 23.53 | 35.29 | 23.53 | 17.65 | - | 100 |
| 35 | አንብቦ የመረዳት ትምህርቱ ለደረጃዉ ያለው ተስማሚነት | ብዛት | 5 | 4 | 6 | 2 | - | 17 |
| | | % | 29.41 | 23.53 | 35.29 | 11.76 | - | 100 |
| 36 | ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አኳያ ሲታይ በመጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት የተሰጠው ቦታ | ብዛት | 11 | 6 | - | - | - | 17 |
| | | % | 64.71 | 23.29 | - | - | - | 100 |

10(58.82%) መምህራን ግልጽና ያልተሸፈኑ ጥያቄዎች በከፍተኛ ደረጃ መካተታቸውን ገልጸዋል:: እንዲሁም 2(11.76%) የተካተቱት በዝቅተኛ ደረጃ ነው በማለት ሲገልጹ፣ 5(29.41%) ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ መካተታቸውን በሰጡት ውጤት አመልክተዋል:: በተራ ቁጥር 30 ለቀረበው መጠይቅ 12(70.59%) በከፍተኛ ደረጃ የሚል ምላሽ ፣ 5(29.41%) አውዳዊ ፍችን ለማገናዘብ የሚረዱት የቀረቡት በመካከለኛ ደረጃ ነው የሚል ምላሽ ተገኝቷል::

መልመጃዎቹ በምንባቦቹ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት በከፍተኛ ደረጃ አካትተዋል ያሉት መምህራን 1(5.88%) ፣ 14(82.35%) ያካተቱበት መጠን በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ፣ 2(11.76%) በበኩላቸው በመካከለኛ ደረጃ ማካተታቸውን በሰጡት ምላሽ አሳይተዋል:: ምንባቦቹ ውስጥ ባሉ አረፍተነገሮች መካከል ስላሉ ዝምድናዎች የቀረቡ ጥያቄዎች አሉ ያሉት መምህራን 2(11.76%)፣ በፍጹም የሉም ያሉት 14(82.35%)፣ በመካከለኛ ደረጃ አሉ ያሉት ደግሞ 1(5.88%) ናቸው:: ግምገማን የተመለከተ ጥያቄ እንደቀረበ 3(17.65%) መምህራን ውጤት፣ 10(58.85%) የተገኘው ደግሞ እንዳልቀረበ አሳይቷል:: ምንባቦቹ የተፃፉበት ቋንቋና መልመጃዎቹ የተፃፉበት ቋንቋ በጣም ተቀራራቢ ናቸው በማለት 10(58.82%) መምህራን፣ 3(17.65%) ምንም መቀራረብ አይታይባቸውም፣ እንዲሁም የ4(23.53%) መምህራን ምላሽ ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ ይቀራረባሉ የሚል ነው::

በተራ ቁጥር 4.223 ስር መልመጃዎችን አስመልክቶ ከቀረቡት መጠይቆች መካከል ከፍተኛ የሆነ ድጋፍ የተሰነዘረው በተ.ቁ.31 በምንባቦች ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ያካተቱ መልመጃዎች የሚገኙበት ሁኔታ የሚለው ነው:: ውጤቱም 1(5.88%) ከፍተኛ፣ 14(82.35%) ደግሞ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን አመልክቷል:: በተ.ቁ 32 የቀረበውም በምንባቡቹ ውስጥ ባሉ አረፍተ ነገሮች መካከል ስላሉ ዝምድናዎች የሚጠይቁ ጥያቄዎች ብዛት በሚል የሰፈረው ነው:: ለዚህም የተገኘው ምላሽ 2(11.76%) ከፍተኛ፣ 14(82.35%) በጣም ዝቅተኛ 1(5.88%) መካከለኛ የሚል ነው:: በዚህ መሰረት 11.76% አዎንታዊ፣ 82.35% አሉታዊ ምላሽ መቅረቡን እናያለን:: ሌላው ከፍተኛ አሉታዊ ምላሽ የተሰነዘረበት በቁጥር 33 ተማሪዎቹ የምንባቦቹን ሐሳቦች ገምግመው በጽሑፍም ሆነ በቃል በማቅረብ የሚያወያዩ ወይም የሚያከራክሩ ጥያቄዎች የሚገኙበት ደረጃ በሚል የቀረበው ነው:: በውጤቱም 3(17.65%) በከፍተኛ ደረጃ ቀርቧል፣ 10(58.85%) ደግሞ አልቀረበም፣ 4(23.53%) ያህሉ ግን በመካከለኛ ደረጃ መቅረቡን ያሳያል:: ከነዚህ ውጭ በቀሩት ጥያቄዎች ድጋፍ እንደተገኘ ማወቅ ተችሏል::

## 4.3. ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

### 4.3.1. ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት፣ ችሎታ፣ ዕድሜና አካባቢ ያላቸው ተስማሚነት

ለተማሪዎቹ የሚቀርቡት ርዕሶችና የጽሑፍ አይነቶች የማይስቧቸው ከሆነ፣ እንዲሰሯቸው በሚቀርቡላቸው ክንዋኔዎች ለመሳተፍ ፈቃደኛ እንደማይሆኑ በመግለፅ Harmer (2001፣ 205-206) የሚከተሉትን ያክላሉ። የማያውቁትን ማህበራዊ ጉዳይ በሚገልፅ የምንባብ አይነት ሲማሩ እንደማይፈልጉ፣ ተማሪዎቹ የሚፈልጓቸውንና በትምህርቱ ላይ ፍላጎት እንዲያድርባቸው የሚረዱ ርእሶችን መምረጥ፣ የተለያዩ ርእሶችንና የጽሑፍ አይነቶችን መምረጥ ወዘተ. ከፍተኛ ፍላጎት ሊያሳድርባቸው ይችላል።

ሠንጠረዥ -12- ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸውን ተስማማሚነት በተመለከተ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የምንባቦቹ ርዕሶች ምንባቡን እንድናነብ ያላቸው የማነቃቃት ሐይል | ብዛት | 84 | 131 | - | 14 | 6 | 235 |
| | | % | 35.74 | 53.74 | - | 5.96 | 2.55 | 100 |
| 2 | የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ባለኝ ቀን መጽሐፉን ይዤ ለመምጣት ያለኝ ፍላጎት | ብዛት | 45 | 38 | 35 | 58 | 59 | 235 |
| | | % | 19.15 | 16.17 | 14.89 | 24.68 | 25.11 | 100 |
| 3 | ምንባቦቹ ያላቸው አጓጊነትና ሌሎች የአማርኛ ጽሑፎችን እንዳነብ ያሳደሩብኝ ፍላጎት | ብዛት | 98 | 105 | 22 | 10 | - | 235 |
| | | % | 41.70 | 44.38 | 9.36 | 4.26 | - | 100 |
| 4 | በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሆነ፣ በትርፌ ጊዜዬ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች የማነብበት ወቅት | ብዛት | 22 | 46 | 122 | 20 | 25 | 235 |
| | | % | 9.36 | 19.57 | 51.91 | 8.51 | 10.64 | 100 |
| 5 | የምንባቦቹ ርዝመት ለፍላጎቱ ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 74 | 115 | 25 | 17 | 4 | 235 |
| | | % | 31.94 | 48.94 | 10.64 | 7.23 | 1.70 | 100 |

በሠንጠረዥ 12 - ላይ እንደሚታየው የምንባቦቹ ርእሶች ፍላጎታቸውን ለማነቃቃት ያላቸው ሐይል በጣም ከፍተኛ መሆኑን 215(91.49%) ተማሪዎች፣ የማነቃቃት ሐይሉ ዝቅተኛ

መሆኑን ደግሞ 20(8.51%) ተማሪዎች ለጥያቄው የሰጡት ውጤት አሳይቷል፡፡ በተራ ቁጥር 2- ለቀረበው ጥያቄም በዘጠነኛ ክፍል ከሚማሩት መጠይቅ ሞዱዎች ውስጥ 83 (35-32%) በከፍተኛ ደረጃ (ሁሌ) ይዘን እንመጣለን፣ 117 (44.79%) የምናመጣበት ጊዜ ጥቂት ነው፣ 35 (14.89%) ደግሞ የምናመጣበት ጊዜ መካከለኛ ነው በማለት ለጥያቄው በሰጡት መልስ አመላክተዋል፡፡ እንዲሁም በተራ ቁጥር 3 - ለቀረበው ምንባቦቹ ያላቸው አጓጊነት በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ያመለከቱት 203(86.38%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ የማጓጓት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑን 10(4.26%)፣ እንደሁም አጓጊነታቸው መካከለኛ መሆኑን የጠቆሙት ደግሞ 22(9.36%) መሆናቸውን ማወቅ ተችሏል፡፡ በተራ ቁጥር -4- ለቀረበው ጥያቄም 68 (28.99%) በከፍተኛ ደረጃ የሚያነቡ እንደሆነ፣ ከተማሪዎቹ 45(19.15%) እንደማያነቡ፣ 122(51.91%) ደግሞ አልፎ አልፎ እንደሚያነቡ ከሠንጠረዡ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የምንባቦቹ ርዝመት ለደረጃው ተገቢ ነው ሲሉ በምላሻቸው የገለጹት 189(80.43%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ ርዝመታቸው ተገቢ አይደለም ያሉት 21 (8.93%) ሲሆኑ፣ በ 25(10.64%) የተሰጠው ደግሞ የርዝመታቸው ተገቢነት መካከለኛ መሆኑን ያመለክታል፡፡

በዚህ ክፍል ከቀረቡት አምስት መጠይቆች ውስጥ ከፍተኛ በሚል ምላሽ የተሰጠው በተራ ቁጥር-1- ‹‹በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የምንባቦች ርዕሶች ምንባቦቹን እንድናነብ ያላቸው የማነቃቃት ሐይል›› የሚለው ሲሆን፣ ይሄንንም 215(91.49%) ተማሪዎች ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ማነቃቃቱን ጠቁመዋል፡፡ በቀጣይነት ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚያጓጉ በ203(96.3%) ተማሪዎች ከተሰጠው ውጤት ማወቅ ተችሏል፡፡

በሠንጠረዥ 12 ስር የተማሪዎችን ፍላጎት አስመልክቶ ከተገኙት መረጃዎች ውስጥ በዝቅተኛ ደረጃ የሚል ምላሽ የተገኘው በተራ ቁጥር-2- ለቀረበው ነው፡፡ ይሄንንም በ 117(49.79%) ተማሪዎች ከተሰጠው ነጥብ ማወቅ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በሌሎቹ መጠይቆች የተገኘው ውጤት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች ለተማሪዎች ፍላጎት ተስማሚ በመሆናቸው በዚህ በኩል አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር እንደሚያግዙ ከልጆቹ ምላሾች ማወቅ ተችሏል፡፡

ሠንጠረዥ -13- ምንባቦቹ ለተማሪዎች ችሎታ፣ ዕድሜና አካባቢ ያላቸውን ተስማሚነት በተመለከተ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | የመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ከችሎታዬ ጋር ያላቸው ስምምነት | ብዛት | 46 | 25 | 38 | 70 | 56 | 235 |
| | | % | 19.57 | 10.64 | 16.17 | 29.79 | 23.83 | 100 |
| 7 | ምንባቦቹ የሐሳብ ግልጽነት፣ ምሳሌ አሰጣጥ ከችሎታዬ ጋር ያላቸው ስምምነት | ብዛት | 41 | 88 | 72 | 14 | 20 | 235 |
| | | % | 17.45 | 37.45 | 30.64 | 5.96 | 8.51 | 100 |
| 8 | ምንባቦቹ ከአካባቢው እንደልብ የማግኘታቸው ሁኔታ | ብዛት | 123 | 59 | 25 | 10 | 18 | 235 |
| | | % | 52.34 | 25.11 | 10.64 | 4.26 | 7.66 | 100 |
| 9 | ምንባቦቹና በውስጣቸው የተሰጡት ምሳሌዎች ለአካባቢዬና ለዕድሜዬ ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 59 | 66 | 64 | 30 | 16 | 235 |
| | | % | 25.11 | 28.09 | 27.23 | 12.76 | 6.81 | 100 |
| 10 | ምንባቦቹ በአካባቢው ካለው ህብረተሰብ ባህል ጋር ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 105 | 82 | 21 | 13 | 14 | 235 |
| | | % | 44.68 | 34.89 | 8.94 | 5.53 | 5.96 | 100 |
| 11 | ምንባቦቹ እስከ ዛሬ ካለኝ ልምድና በአካባቢዬ ከማያቸው፣ ከምሰማቸውና ከማውቃቸው የቋንቋ አጠቃቀሞች ጋር ያላቸው ስምምነት | ብዛት | 71 | 86 | 42 | 20 | 16 | 235 |
| | | % | 30.21 | 36.60 | 17.87 | 8.51 | 6.81 | 100 |

ከሠንጠረዥ 13 ማየት እንደሚቻለው ምንባቦቹና ችሎታቸው ስምሙ
ያመለከተው 71(30.21%)፣ ስምሙ አለመሆናቸውን 126(53.62%)፣ እንዲሁም በመካከለኛ
ደረጃ ስምምነት መኖሩን ደግሞ 38(16.17%) ተማሪዎች የሰጡት መልስ ነው። እንዲሁም
በተራ ቁጥር -7- ለቀረበው ጥያቄ ምንባቦቹ የያዙት ሐሳብና የምሳሌ አሰጣጥ ግልጽ መሆኑን
ማወቅ የተቻለው 129(54.89%) ተማሪዎች በሰጡት ነጥብ ሲሆን፣ 34(14.47%)
ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ግን ግልጽ አለመሆኑንና አለመስማማቱን ገልጿል። ከሠንጠረዥ
13 መገንዘብ እንደሚቻለው ምንባቦቹ በአካባቢው በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ ይገኛሉ።
ይህንንም 182(77.45%) ተማሪዎች ከጠቆሙት መረዳት ተችሏል። 28(11.92%)
ከሚሆኑት የተገኘው ደግሞ እንደማይገኙ ይገልጻል። ሆኖም በአብዛኞቹ ከተሰጠው ምላሽ
ምንባቦቹ እንደሚገኙ መረዳት ተችሏል። በተራ ቁጥር-9- ለቀረበው ጥያቄም በ
125(53.19%) ተማሪዎች ከፍተኛ፣ በ 46(1957%) ዝቅተኛ፣ በ 64(27.23%) ደግሞ

መካከለኛ ነው የሚል ውጤት ተገኝቷል። ምንባቦቹ በአካባቢው ካለው ህብረተሰብ ባህል ጋር ተስማሚ መሆናቸውን የ187(79.57%) ተማሪዎች ውጤት አሳይቷል። ሌላው በሠንጠረዥ መጨረሻ ላይ ለቀረበው ጥያቄም ምንባቦቹ ከልጆቹ ልምድና ከአካባቢያቸው ከሚሰሟቸውና ከሚያውቋቸው የቋንቋ አጠቃቀሞች ጋር እንደ ሚሰማሙ 157(66.81%) ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ መረዳት ተችሏል።

## 4.3.2. የምንባቦች ይዘቶች ግልጽነትና ተስማሚነት

ሠንጠረዥ -14- የምንባቦቹን ይዘቶችና ግልጽነት በተመለከተ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | የምንባቦቹ አጻጻፍ ወይም ቅርጽ ለእይታ ያላቸው ግልጽነት | ብዛት | 22 | 27 | 39 | 101 | 46 | 235 |
| | | % | 9.36 | 11.49 | 16.60 | 42.98 | 19.57 | 100 |
| 13 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች የሚገልጿቸው መልእክቶች ግልጽነትና ወቅታዊነት | ብዛት | 45 | 117 | 28 | 23 | 22 | 235 |
| | | % | 19.15 | 49.79 | 11.91 | 9.79 | 9.36 | 100 |

ሠንጠረዥ -14- እንደሚያመለክተው የምንባቦቹ ያጻጻፍ ቅርጽ ለእይታ ግልጽ መሆናቸውን ከ 49(20.85%)፣ ምንም ግልጽነት እንደሌላቸው 147(62.55%)፣ እንዲሁም ያላቸው ግልጽነት በመካከለኛ ደረጃ መሆኑን 39(16.60%) ተማሪዎች የሰጡት ውጤት ያሳያል። በዚህም የምንባቦቹ አጻጻፍ ግልጽ እንዳልሆነ መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ግልጽና ወቅታዊ እንደሆኑ በ 162(68.94%) ተማሪዎች የተመላከተው ነጥብ ሲገልጽ፣ በ 45(19.15%) የተሰጠው ደግሞ ግልጽና ወቅታዊነታቸው ዝቅተኛ ነው ይላል። ሆኖም ከአብዛኛው ተማሪ የተገኘው ምላሽ ምንባቦቹ ግልጽና ወቅታዊ መሆናቸውን ገልጿል።

ሠንጠረዥ-15- የምንባቦቹን ተስማሚነት በተመለከተ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ላለሁብት ዕድሜ ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 69 | 142 | 10 | 14 | - | 235 |
| | | % | 29.36 | 60.43 | 4.26 | 5.96 | - | 100 |
| 15 | በምንባቦቹ ውስጥ ቃላት ከአካባቢው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር ያላቸው ተስማሚነት | ብዛት | 111 | 67 | 30 | 16 | 11 | 235 |
| | | % | 47.23 | 28.51 | 12.76 | 6.81 | 4.68 | 100 |
| 16 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች የክብደት ደረጃ | ብዛት | 12 | 53 | 127 | 34 | 9 | 235 |
| | | % | 5.11 | 22.55 | 54.04 | 14.46 | 3.83 | 100 |

በተራ ቁጥር 14- ለተመዘገበው ጥያቄ ምንባቦቹ ላለሁብት ዕድሜ ተስማሚ ነው ያሉት 211(89.79%)፣ ያላቸው ተስማሚነት ዝቅተኛ ነው በማለት ያመላከቱት 14(5.96%)፣ ተስማሚነታቸው መካከለኛ መሆኑን የገለጹት ደግሞ 10(4.26%) ተማሪዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ምንባቦቹ ተማሪዎቹ ላሉብት ዕድሜ ተስማሚ መሆናቸውን ከብዙኋኑ ተማሪ ውጤት መረዳት ተችሏል፡፡ በምንባቦቹ ውስጥ ያሉት ቃላት በድሬዳዋና በሐረር አካባቢ ያለው አማርኛ ተናጋሪ ከሚጠቀምባቸው ጋር ተስማሚ መሆናቸውን በ178(75.74%) ተማሪዎች ነጥብ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም በተራ ቁጥር 16 ምንባቦቹ ከባድ መሆናቸውን 65(27.66%) ተማሪዎች አሳይተዋል፡፡ 43(18.20%) ክብደታቸው ዝቅተኛ መሆኑን፣ እንዲሁም 127(54.04%) ደግሞ ምንባቦቹ ለዚህ ደረጃ ተማሪ ከባድ አለያም ቀላል ናቸው ለማለት አለመቻሉን አመላክቷል፡፡

ሠንጠረዥ -16- ምንባቦቹ ከልዩ ልዩ ጽሑፎች የተውጣጡ መሆናቸውን በተመለከተ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች የተለያዩ ይዘቶች(ረጅምና አጭር ልቦለድ፣ ቀልዶች፣ ግጥሞች ወዘተ.) የተካተቱባቸው ደረጃ | ብዛት | 98 | 72 | 28 | 24 | 13 | 235 |
| | | % | 41.70 | 30.64 | 11.92 | 10.21 | 5.53 | 100 |
| 18 | ምንባቦቹ የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን እንደ ምሳሌያዊ፣ ፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊ አነጋገር ያሉትን የያዙበት ደረጃ | ብዛት | 89 | 67 | 41 | 22 | 16 | 235 |
| | | % | 37.87 | 28.51 | 17.45 | 9.36 | 6.81 | 100 |

ለዚህ የክፍል ደረጃ በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች የተውጣጡበት ደረጃ በጣም ከፍተኛ መሆኑን ከ 170(72.34%) ተማሪዎች ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የተውጣጡ አለመሆናቸውን ያመለከተው ደግሞ በ 37(15.74%) ተማሪዎች የተሰጠው ነጥብ ነው፡፡ 28(11.92%) የሰጡት ደግሞ ምንባቦቹ የተውጣጡት በመካከለኛ ደረጃ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በተጨማሪም የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን አነጋገሮች ምንባቦቹ በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ መያዛቸውን የ 156(66.38%) ተማሪዎች ምላሽ ሲያሳይ፣ የ 37(15.74%) ምላሽ በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን፣ እንዲሁም 41(17.45%) በበኩላቸው የቋንቋው ተጠቃሚ የሚገለገልባቸውን አነጋገሮች የያዙት በመካከለኛ ደረጃ መሆኑን አሳይቷል፡፡

### 4.3.3. የመልመጃዎች አቀራረብ ባህርይ

ይህን ክፍል ለማየት የሚሞከረው ቀደም ሲል በምእራፍ ሁለት እንደተመለከተው ስለአንብቦ መረዳት መልመጃዎች አቀራረብ በCunningsworth(1995)፣ በMcDonugh and Shaw (2003)፣በNuttall (1982) በGrellet (1981)፣ በSheng (2000) ወዘተ. ከተሰነዘሩት መስፈርቶች ውስጥ ለዚህ ጥናት ተስማሚ የሆኑትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሠረት የሚቀርቡት ተግበራት ለተማሪዎች ፍላጎት የሚስማሙ ብቻ ሳይሆኑ፣ ከቀዳሚ እውቀታቸው ጋርም የሚዛመዱ መሆን እንዳለባቸው ምሁራኑ ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህ መሠረት ለ9ኛ ክፍል የተዘጋጁት መልመጃዎች ምን እንደሚመስሉ ቀጥለን እንይ፡፡

ሠንጠረዥ-17- በዘጠነኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ ያሉ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችን በተመለከተ

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመስራት ፍላጎቱ | ብዛት | 63 | 110 | 25 | 18 | 19 | 235 |
| | | % | 26.81 | 46.81 | 10.64 | 7.66 | 8.09 | 100 |
| 20 | መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች ከማንበባችን በፊት የቀረቡ ስለምንባቡ የሚያወያዩ ጥያቄዎች | ብዛት | 107 | 69 | 31 | 19 | 9 | 235 |
| | | % | 45.53 | 29.36 | 13.19 | 8.09 | 3.83 | 100 |
| 21 | ስለምንባቦቹ የሚጠይቁት መልመጃዎች የተጻፉበት ቋንቋ ምንባቦቹ ከተጻፉበት ቋንቋ ጋር በክብደት ያላቸው መቀራረብ | ብዛት | 94 | 74 | 34 | 18 | 15 | 235 |
| | | % | 40.00 | 31.49 | 14.47 | 7.66 | 6.38 | 100 |
| 22 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች አንብቤ መልመጃዎችን ለመስራት ያለኝ መነቃቃት | ብዛት | 43 | 10 | 66 | 10 | 10 | 235 |
| | | % | 18.30 | 45.11 | 28.08 | 4.26 | 4.26 | 100 |
| 23 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ሳይነበቡ ከምንባቦቹ የወጡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያለው ዕድል | ብዛት | 7 | 19 | 23 | 76 | 110 | 235 |
| | | % | 2.98 | 8.08 | 9.79 | 32.34 | 46.81 | 100 |
| 24 | የመልመጃዎችቹ ትእዛዞች ግልጽነት | ብዛት | 25 | 30 | 164 | - | 16 | 235 |
| | | % | 10.64 | 12.76 | 69.79 | - | 6.81 | 100 |
| 25 | ከምንባቦቹ የወጡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንባቦቹን ደጋግሜ እንዳነብ የማድረግ ደረጃ | ብዛት | 61 | 127 | 30 | 10 | 7 | 235 |
| | | % | 25.96 | 54.04 | 12.77 | 4.25 | 2.98 | 100 |
| 26 | ከምንባቦቹ ከወጡት ጥያቄዎች ውስጥ አንብባችሁ የተረዳችሁትን በጽሑፍ እንድትመልሱ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ብዛት | ብዛት | 17 | 43 | 36 | 118 | 21 | 235 |
| | | % | 7.23 | 18.30 | 15.32 | 50.21 | 8.94 | 100 |

ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር የሚችሉት የቀረቡትን ክንዋኔዎች በተደጋጋሚ ሲሰሩ ነው፡፡ ክንዋኔዎችን በተደጋጋሚ ለመተግበር ደግሞ መጀመሪያ በቀረበው ትምህርት ፍላጎት ሊያድርባቸው እንደሚገባ በክለሳድርሳን ላይ ምሁራን ከገለጹት ቁም ነገር ተገንዝበናል ፡፡ ስለተማሪዎች ፍላጎት ለማወቅ ደግሞ የመጀመሪያው ተግባር ራሳቸውን ተማሪዎችን ከመጠየቅ በላይ መረጃ ማግኛ ዘዴ እንደሌለ David (2005) ያስገነዝባሉ፡፡ በሠንጠረዥ -17- መጀመሪያ ላይ በተራ ቁጥር 19 ለቀረበው መጠይቅ 173(73.62%) ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ መልመጃዎቹን የመስራት ፍላጎት እንዳለቸው በምላሻቸው ገልጸዋል፡፡ ሆኖም ግን ሠላሳ ሠባቱ (15.75%) የመስራት ፍላጎት እንደሌላቸው ሲያሳዩ፣ 25(10.64%) ደግሞ መካከለኛ የሆነ ፍላጎት እንዳላቸው አስገንዝበዋል፡፡ ከውጤቱ እንደሚታየው የመስራት ፍላጎት የሌላቸውና መካከለኛ የሆነ ፍላጎት ያላቸውን በአንድ ላይ አድርገን የመስራት ፍላጎት ካላቸው ጋር ብናስተያያቸው እንኳ፣ ፍላጎት ያላቸው ፍላጎት

ከሌላቸውና መካከለኛ ፍላጎት ካላቸው በ 111(47.23%) ብልጫ አላቸው። ስለዚህ ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችን የመስራት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው።

በመጽሐፉ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች እንዳሉም የ176(74.89%) ተማሪዎች ውጤት ሲገልጽ፣ የሃያስምንቱ (11.92%) ውጤት ግን ምንባቦቹ ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች እንደሌላቸው፣ የሃያአምስቱ (10.64%) ደግሞ በመካከለኛ ደረጃ እንዳላቸው አሳይቷል። ከአብዛኞቹ የተገኘው መረጃ ግን በርካታ የሆኑ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመጽሐፉ ውስጥ መኖራቸውን አመልክቷል። መልመጃዎቹ ና ምንባቦቹ የተጻፉበትን ቋንቋ በተመለከተም ከሠንጠረዡ 17 እንደሚታየው ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች የምንባቦቹና የጥያቄዎቹ የቋንቋ አጠቃቀም ተቀራራቢ በመሆኑ ላይ ስምምነት አሳይተዋል።

በተራ ቁጥር 22 ላይ የቀረበው ጥያቄም መልመጃዎችን የመስራት ፍላጎት መኖሩን በ 149(63.41%) ተማሪዎች የተሰጠው ነጥብ ሲያሳይ፣ በ 20(8.52%) የተሰጠው ደግሞ ዝቅተኛ የሆነ የመስራት ፍላጎት እንዳለ፣ የ 66(28.08%) ምላሽ መካከለኛ ፍላጎት መኖሩን ያሳያል። በሌላም በኩል በተራ ቁጥር 23 ላይ ለቀረበው ጥያቄ ከተሰጡት ምላሾች ውስጥ 26(11.08%) ተማሪዎች ምንባቦቹ ሳይነበቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ እንደሚቻል ሲገልጹ፣ ምንባቦቹ ሳይነበቡ በፍጹም ጥያቄዎቹን መስራት እንደማይቻል፣ ያመለከተው ደግሞ 186(79.15%) ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ነው። በዚህም ከምንባቦቹ የወጡትን መልመጃዎች ለመስራት የግድ ምንባቦቹ መነበብ እንዳለባቸው ስምምነት ታይቷል። በክለሳ ድርሳን አለም (1995፣13)'ን በመጥቀስ መልመጃዎች የታለመውን ግብ እዲመቱ ጥያቄዎች ምንባቡን ባላነበበ ሰው መመለስ የለባቸውም ባሉት መሰረት ከመጠይቁ የተገኘው ውጤትም አረጋጧል።

በመጨረሻም በተራ ቁጥር -26- ለቀረበው የተገኘው ውጤት ተማሪዎች የተረዱትን በጽሑፍ እንዲመልሱ የሚያዙ ጥያቄዎች የሚገኙት በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን ከ139(59.15%) ተማዎች የተገኘው ውጤት ያሳያል። እንዲሁም 60(25.53%) ተማሪዎች በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች በከፍተኛ ደረጃ መኖራቸውን ይጠቁማሉ። ይሁንና የአብዛኞቹ ምላሽ በጽሑፍ የሚመለሱ ጥያቄዎች ያሉበት መጠን ዝቅተኛ መሆኑን ይገልጻል።

አንብቦ የመረዳት መልመጃዎችን አስመልክቶ ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ከቀረቡት መጠይቆች ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የሚል ምላሽ የተሰጠው በተራ ቁጥር -25- ‹‹ከምንባቦቹ የወጡትን ጥያቄዎች ለመስራት ምንባቦቹን ደጋግሜ እንዳነብ የማድረግ ደረጃ›› በሚል ለቀረበው ነው፡፡ ይሄውም ከ 188(80%) ተማሪዎች በተገኘው ውጤት ተማሪዎቹ ጥያቄዎቹን ለመስራት ደጋግመው ምንባቦቹን እንደሚያነቡ ተገልጿል፡፡ በዚህም መልመጃዎቹን ለመስራት ምንባቦቹ በተደጋጋሚ ካልተነበቡ በቀላሉ መልሳቸውን ማግኘት እንደማይቻል መገንዘብ ተችሏል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ከተማሪዎች ለ 26 ዝግ መጠይቆች ከተሰጡት ምላሾች ውስጥ ለ-18- ጥያቄዎች አዎንታዊ፣ ለ -4-ጥያቄዎች አሉታዊ እንዲሁም ለ -4- ጥያቄዎች ደግሞ መካከለኛ (ገለልተኛ) ምላሽ ተገኝቷል፡፡ በዚህ መሰረት ይህም ለክፍል ደረጃው የቀረበው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ አንብቦ የመዳትን ችሎታ ለማዳበር ብቃት እንዳለው ይጠቁማል፡፡

## 4.4. ከሰነድ ምርመራ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ውጤት ትንተና

ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸውን ተስማሚነት፣ የምንባቦቹን ይዘቶች ግልጽነትና ተስማሚነት፣ እንዲሁም የመልመጃዎችን አቀራረብ አስመልክቶ ከሰነድ ፍተሻ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኙት ውስጥ ቀጥሎ የቀረቡትን በአንድነት እንመልከት፡፡

### ሀ. ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት ያላቸው ተስማሚነት

ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች መጀመሪያ ላይ የቀረበላቸው መጠይቅ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የምንባብ ርዕሶች ተማሪዎቹ ምንባቦቹን እንዲያነቡ ማነቃቃትና አለማነቃቃታቸውን የተመለከተ ነበር፡፡ ለዚህ ጥያቄ በ 15(88.24%) መምህራን ውጤት የምንባቦቹ ርዕሶች የተማሪውን ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያነቃቁ ሲገልጽ፣ በተመሳሳዩ

215(91.49%) ተማሪዎች የሰጡት ውጤትም ከመምህራን የተገኘውን ምላሽ አጠናክሮታል፡፡ ምዕራፍ ሁለት ላይ Harmer (2001 205-206) ለተማሪዎች የሚቀርቡ ርዕሶችና የጽሑፍ አይነቶች ተማሪዎችን የማይስቧቸው ከሆኑ፣ እንዲሰሯቸው በሚቀርቡላቸው ክንዋኔዎች እንደማይሳተፉ ገልጸው ነበር፡፡ በዚህ መሰረት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ርዕሶች ግን የተማሪዎችን ፍላጎት በከፍተኛ ደረጃ ስለሚያነቃቁ ርዕሶቹ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ እንደሆነ የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

ለተማሪዎች ፍላጎት መነቃቃት አስተዋጽኦ ካላቸው ጉዳዮች ውስጥ McDonough and Shaw (2003)ና Cunningsworth (1995) እንደሚሉት የምንባቦች ርዝመት አንዱ ነው፡፡ ምንባቦቹ በጣምም ሳይረዝሙ፣ በጣምም ሳያጥሩ ተመጥነው ከቀረቡ የልጆቹን ስሜት የመግዛት ችሎታ ይኖራቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው አብዛኞቹ ምንባቦች ከሦስት ገጽ ያልበለጡ (ያውም መጽሐፉ አነስተኛ ቁመትና ስፋት ያለው ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ) መሆናቸው በዚህ ደረጃ ላለተማሪ ስለማያሰለቹ ተስማሚ ናቸው፡፡ ይህንኑ አስመልክቶ ለመምህራን በተራቁጥር 4፣ ለተማሪዎች ደግሞ በተራ ቁጥር -5- ቀርቦ 16(94.12%) በጣም ከፍተኛ በሆነ ደረጃ እንደሚያስደስት፣ በምላሻቸው ሲያመለክቱ፣ 189(80.43%) ተማሪዎችም በክፍተኛ ደረጃ እንዳስደሰታቸው ከሰጡት ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ምሁራኑ እንዳሉት የምንባቦቹ ርዝመት ለተማሪዎቹ ፍላጎት ተስማሚ በመሆኑ በዚህ በኩል ለአንብቦ መረዳት ችሎታ መዳበር የበኩሉን እገዛ ያደርጋል፡፡

ሌላው በዚህ ክፍል ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ተመሳሳይ በሆነ ተራ ቁጥር 2 ቀርቦ የነበረና በሁለቱም ወገኖች የተለያየ ውጤት የተመዘገበበት ተማሪዎቹ ክፍለ ጊዜ ባላቸው ቀን የአማርኛ መማሪያ መጽሐፋቸውን ይዘው መምጣት አለመምጣታቸውን የሚመለከት ነበር፡፡ በዚህም 13(76.47%) መምህራን ልጆቹ መጽሐፋቸውን ይዘው እንደማይመጡ ሲጠቁሙ፣ 117(44.79%) ደግሞ መጽሐፋቸውን ይዘው እንደሚመጡ ያመለክታሉ፡፡ ይሁን እንጂ መጽሐፋቸው እንደማይለያቸው የሚያመለክት ምላሽ የሰጡት አብዛኞቹ ተማሪዎች ቢሆኑም ከአጠቃላዩ ቁጥራቸው አኳያ ከግማሽም ያልዘለሉ (ያልደረሱ) በመሆናቸው

መጽሐፋቸውን ይዘው እንደማይመጡ መረዳት ይቻላል። ስለዚህ መጽሐፍ ሳይኖር አንብቦ የመረዳት ትምህርት እንዴት ሊዳብር ይችላል? ያስኛል።

## ለ. የምንባቦቹ ይዘቶች ግልጽነትና ተስማሚነት

የምንባቦቹ አጻጻፍ (ቅርጽ) ለእይታ ያለውን ግልጽነት በተመለከተ ከመጽሐፉ የተገኘው መረጃ በህትመት ችግር ምክንያት አልፎ አልፎ ለእይታ እንደሚያስቸግር በተራ ቁጥር 4.1 ‹‹በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኝ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘት ትንተና›› በሚለው ስር ተመልክቷል። በተመሳሳዩ ነጥብ ላይ ለመምህራንና ለተማሪዎች በተራ ቁጥር 10 እና 13 እንደቅደም ተከተላቸው ቀርቦ፣ በውጤቱም 12 (70.58) መምህራን የሰጡት ዝቅተኛ (አሉታዊ) ሲሆን፣ 147(62.55%) ተማሪዎች የሰጡትም አሉታዊ ነው። ከዚህም የምንባቦቹ ቅርጽ ለእይታ ግልጽ እንዳይደለ መረዳት አያዳግትም።። አልፎ አልፎም ቢሆን ምንባቦቹ በአይን ለማየት የሚያስቸግሩ ከሆኑ በትምህርቱ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽእኖ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም።

በተጨማሪም የምንባቦቹን የክብደት ደረጃ ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የሚያስችግሩ ያሉ መሆኑን፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም መምህራን ምንባቦቹ አይከብዱም ሲሉ፣ 127(54.04%) ተማዎች ምላሽ የምንባቦቹ ክብደት መካከለኛ እንደሆነ ይጠቁማል። ከዚህም ተማሪዎቹ ምንባቦቹ ቀላል ናቸው ለማለት እንዳልደፈሩ መረዳት ይቻላል። እንደ Cunningsworth (1995፣75) ከሆነ ይዘቶቹ በደረጃው ለሚገኙ ተማሪዎች የሚከብዱ ወይም የሚቀሉ፣ ለተማሪው የማይገቡ ሐሳቦችን የያዙ ከሆኑ ወዘተ. ተማሪዎቹ በምንባቦቹ ተሰበው አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማዳበር አይነሳሱም። ስለዚህ አማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ በሚማሩት ዘንድ ችግር መኖሩን የሚያመላክት ፍንጭ ይታያል።

## ሐ. ምንባቦቹ ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች ስለመውጣጣታቸው

‹‹ምንባቦቹ ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች (ረጅምና አጭር ልቦለድ፣ ጭውውቶች፣ ግጥሞች ወዘተ.) የተውጣጡበት ደረጃ›› ለሚለው ከሰነዱ መረዳት እንደሚቻለው በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት 15 ምንባቦች ሲሆኑ፣ አጭር ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት፣ ወግ፣ ዘገባ፣ ወዘተ.

የመሳሰሉ የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች ተካትተዋል (ሠንጠረዥ አንድን ይመለከቷል)፡፡ የምንባቦቹን የተለያዩ አይነትነት በተመለከተ ለመምህራን በተራ ቁጥር 22፣ ለተማሪዎች ደግሞ በተራ ቁጥር 17 ቀርቦ 16(94.11%) መምህራን በጣም ከፍተኛ፣ 170(72.34%) ተማሪዎች ደግሞ ምንባቦቹ በከፍተኛ ደረጃ የተውጣጡ እንደሆኑ አሳይተዋል፡፡ በተጨማሪም ምንባቦቹ የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸው እንደ ምሳሌያዊ፣ ፈሊጣዊና ዘይቤያዊ አነጋር ያሉትን ያካተቱበትን ደረጃ ለማወቅ በተደረገው ፍተሻ ቀደም ሲል በመጽሐፉ ውስጥ ስለሚገኝ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘት ትንተና ስር ለማመልከት እንደተሞከረው ምንባቦቹ እነዚህን የተለያዩ አጠቃቀሞች በሚገባ አካትተው ተገኝተዋል፡፡ ይሄንንም 12(70.58%) መምህራንና 157(66.81%) ተማሪዎች ከሰጡት ውጤት ማወቅ ተችሏል፡፡

አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚቀርቡ ምንባቦች የተውጣጡ ወይም የተለያዩ የጽሑፍ አይነቶችን ያካተቱ ቢሆኑ እንደሚመረጥ አለም (1995፣8) ያሉትን በክለሳ ድርሳን ውስጥ በተመለከትነው መሰረት ከሰነድ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም ለዘጠነኛ ክፍል የቀረበው ትምህርት ብቃት እንዳለው አመልክቷል፡፡

### መ. የመልመጃዎች አቀራረብ ባህሪይ

በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ቅድመንባብ የመወያያ ጥያቄ የተማሪዎችን ፍላጎት በማነቃቃት አንብቦ የመረዳትን ችሎታ እንደሚያዳብር፣ ተማሪዎች ስለርዕሱ እንዲያስቡ በማድረግ ምንባቡን የማንበብ ፍላጎታቸውን እንደሚያነቃቃ Aebersold and field (1997፣ 67-68) ፣ የሚመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ቅድመ ንባብ ተግባራት የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነቃቃት ወሳኝ መሆኑን ደግሞ Day and Banfored (1998፣ 76-78) ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች የተማሪዎቹ ትኩረት ከሚያነቡት ጽሑፍ በሚያገኙት መረጃ ላይ እንዲሆን ያደርጋል በማለት McDonough and Shaw (2003 ፣85) ያቀረቡትን በምዕራፍ ሁለት በተመለከትነው መሠረት ለዘጠነኛ ክፍል ከቀረቡት 15 ምንባቦች ውስጥ 12 ቅድመንባብ የመወያያ ጥያቄዎች እንዳላቸው ቀደም ሲል ከሰነድ ምርመራ ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም በቀረበላቸው መጠይቅ መሰረት 15 (88.23%) መምህራንና 176(74.89%) ተማሪዎች እንዳመለከቱት ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች በመጽሐፉ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ እንደተካተቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ለዚህ የክፍል ደረጃ የቀረበው አንብቦ የመረዳት ትምህርት

በምሁራኑ የቀረበውን ሐሳብ ስለሚያሟላ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር በዚህ በኩል ብቃት አለው።

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር የሚዘጋጁ ጥያቄዎች በተቻለ መጠን ከእምሮታዊ ሁኔታ ጋር የሚዛመዱ የአመራማሪነት ባህርይ ያላቸው መሆን ይገባል። (Grellet 1981፣ 4-8)። እንዲሁም Sheng (2000) አእምሮታዊ ክሂልን መሰረት ያደረጉ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ለማንኛውም ደረጃና ለተለያዩ ተማሪዎች ፍላጎት ተስማሚ ናቸው። ተማሪዎች ምንባቡን ከተለያየ አቅጣጫ እንዲመለከቱና የይዘቱን አንድምታዎች እንዲረዱ ስለሚጠይቁ፣ የሂስና የትንበያ ክሂሎችን ስለሚያሻሽሉ አስፈላጊ ናቸው። ይህንንም በክለሳድርሳን ውስጥ በተመለከተነው መሰረት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ምን ይመስላሉ? ስንል ጥያቄዎቹ ለተማሪዎቹ ፍላጎት ተስማሚ መሆኛቸውን ለተማሪዎች በተራ ቁጥር 19ና 22 ላይ ቀርበውላቸዋል። ለነዚህ ተመሳሳይና መልመጃዎችን የመስራት ፍላጎትን ለተመለከቱ ጥያቄዎች በተገኘው ምላሽም ከፍተኛ ፍላጎት እንዳላቸው ታውቋል። ከላይ የተጠቀሱት ምሁራንና Harmer (2001፣ 205-206) ባሉት መሠረት ለቀረቡላቸው ርዕሶችና ጽሑፎች ከፍተኛ ፍላጎት ስላላቸው ከነዚህ የወጡትን መልመጃዎች የመስራት ከፍተኛ ፍላጎት አሳይተዋል።

ቀጣዩ ደግሞ ተማሪዎቹ የምንባቦቹን ሐሳቦች ገምግመው በጽሑፍም ሆነ በቃል በማቅረብ የሚያወያዩ ወይም የሚያከራክሩ አእምሮታዊ ጥያቄዎች የሚገኙበትን ደረጃ የሚያመለክት ሲሆን (አባሪ ሁለትን ይመለከቷል)፣ ከሰነድና ከመምህራን የተገኘው መረጃ ግምገማን የተመለከተ አንድም ጥያቄ በአንብቦ መረዳት መልመጃ ስር እንዳልተካተተ አሳይቷል። ስለዚህ ምሁራኑ በተለይም Sheng (2000) አእምሮታዊ ጥያቄዎች የሂስና የትንበያን ክሂሎች ስለሚያሻሽሉ አስፈላጊ ናቸው ባሉት መሰረት ከአእምሮታዊ ጥያቄዎች ውስጥ አንዱ የሆነው የግምገማ ጥያቄ አለመካተቱ ደግሞ ትምህርቱን የተሟላ እንዳይሆን ማድረጉ አይቀሬ ነው።

# ምዕራፍ አምስት
# ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን መፈተሽ እንደሆነ በምዕራፍ አንድ ተጠቅሷል:: በተጨማሪም በዚሁ አብይ የጥናቱ አላማ ስር ያሉት የምንባቦቹ አመራረጥ የተማሪዎችን ፍላጎት ማሟላትና አለማሟላታቸውን፣ ከችሎታቸው፣ ከዕድሜያቸውና ከአካባቢያቸው ጋር መጣጣም አለመጣጣማቸውን፣ የምንባቦቹ ይዘቶች ለተማሪዎቹ ያላቸውን ግልጽነትና ተስማሚነት፣ አንብቦ የመረዳት ትምህርት (መልመጃ) አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን መፈተሽ የሚሉት ቀርበዋል::

እንዲሁም የንባብን ምንነት፣ አንብቦ የመረዳትን ምንነት፣ አንብቦ የመረዳትን ትምህርት አቀራረብ፣ የንባብ ትምህርት ይዘቶችን ግልፅነት ወዘተ. በሚመለከት በአንብቦ መረዳት ላይ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ ምሁራን የሚያቀርቧቸውን ዋና ዋና ነጥቦች ሰፋ ባለ መልኩ በጥናቱ ክፍል ሁለት ለመመልከት ተሞክሯል:: በክፍል ሦስት ለጥናቱ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያገለገሉ የሰነድ ምርመራ፣ ለመምህራንና ለተማሪዎች የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ወዘተ. ቀርበው በዝርዝር ተገልፀዋል:: ይህም ከዚህ በታች ተጠቃሎ ቀርቧል::

ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት፣ ችሎታ ወዘተ. ያላቸውን ተስማሚነት በሚመለከት በሰነድ ምርመራና በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት ተሰብስበው ተተንትነዋል:: በዚህም የምንባቦቹ ርዝመት፣ የርዕሶች ሳቢነት የተማሪዎችን ፍላጎት ለማነቃቃት የሚያስችሉ ሆነው ተገኝተዋል:: እንዲሁም ምንባቦቹ ለተማሪዎች ዕድሜና አካባቢ ቀረቤታ እንደላቸው የታወቀ ሲሆን፣ ምንባቦቹ በሕትመት ችግር ምክንያት አልፎ አልፎ ለእይታ ግልጽነት እንደሌላቸው ተረጋግጧል:: ከቀረቡት ምንባቦች ውስጥ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩት የሚከብዱ መኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል:: ምንባቦቹ ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች የተውጣጡና የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን እንደፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ያሉትን በከፍተኛ ደረጃ ማካተታቸውም ታውቋል:: ሌላው በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው አንብቦ የመረዳት ትምህርት፡ - ቅድመንባብ፣ ጊዜ ንባብና

ድህረንባብ ክንዋኔዎችን ማካተቱ ተረጋግጧል። መልመጃዎቹ ምንባቦቹን ባላነበበ ሰው የማይመለሱ ከመሆናቸውም በላይ እንደ ምንባቦቹ ሁሉ እውናዊ (Authentic) መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል። እንዲሁም ግልጽና ያልተሸፈኑ፣ አውዳዊ ፍችን ለማገናዘብ የሚያስችሉ ጥያቄዎች መካተታቸው ታውቋል። ጥያቄዎቹም ለተማሪዎቹ ፍላጎት ተስማሚ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል።

በሌላ በኩል መልመጃዎቹ በምንባቦቹ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት፣ በምንባቦቹ ውስጥ ባሉ አረፍተነገሮች መካከል ስላሉ ዝምድናዎች የሚጠይቁ ጥያቄዎች፣ የግምገማ ጥያቄዎች በመልመጃዎቹ ውስጥ እንዳልተካተቱ መረዳት ተችሏል። በተጨማሪም በአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ስር ከቀረቡት 230 ጥያቄዎች ውስጥ -123- በቃል ይሁን በጽሑፍ በምን እንደሚመለሱ ያልተገለጹ ጥያቄዎች መኖራቸውም ታውቋል። ከዚህም ሌላ ተማሪዎች የአማርኛ መማሪያ መጽሐፋቸውን ይዘው እንደማይመጡ ከመምህራንና ከራሳቸው የተገኘው መረጃ አረጋግጧል።

በአጠቃላይ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ለማዳበር የቀረበው ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ የቀረበ ጠንካራ ክፍል እንዳለው ሁሉ፣ ሊሻሻል የሚገባው ክፍል መኖሩንም ማወቅ ተችሏል። እንዲሁም የትምህርቱ አቀራረብ ማማር ብቻ ሳይሆን፣ ከዚህ ጋር ለትምህርቱ የሚመደበው ክፍለ ጊዜ፣ ልጆቹ ይዘውት የሚመጡት ዕውቀት ያለበት ሁኔታ ወዘተ. ከግምት ውስጥ መግባት እንዳለባቸው ከመምህራን አስተያየት መረዳት ተችሏል።

## 5.2. አስተያየት

ከመረጃዎቹ የተገኙትን ውጤቶች መሠረት በማድረግ የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል።

1. መልመጃዎቹ በምንባቦቹ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት፣ በአ.ነገሮች መካከል ስላሉ ዝምድናዎች የሚመለከቱና የግምገማ ጥያቄዎች የማካተቱባቸው ሁኔታዎች ቢመቻቹ፣

2. አብዛኞቹ ምንባቦች ለቀረቡለት ደረጃ ተገቢ ናቸው ቢባልም እንዳንድ ለደረጃው የሚከብዱ ተብለው የተገመቱት የሚሻሻሉበት መንገድ ቢታሰብ፣
3. ከመምህራን አስተያየት አንብቦ የመረዳት ትምህርት በጥሩ ሁኔታ መቅረቡ ብቻ ሳይሆን፣ ለትምህርቱ የተመደበው ክፍለ ጊዜ በጣም ማነስ፣ የተማሪዎች ያለፈ ልምድ እጅግ አነስተኛ መሆን፣ በተቻለ መጠን የሚሻሻሉበት መንገድ ቢፈለግ፣
4. አንብቦ የመረዳት ትምህርት ሲዘጋጅ ኢ-አፍ-ፈቶችንም ከግንዛቤ ቢያስገባ፣
5. ለአንብቦ መረዳት የሚቀርቡ መልመጃዎች በቃል ወይም በጽሑፍ በየቱ እንደሚመለሱ ቢገለጽ (ልጆቹ ደክም በሚሉበት ክሂል እንዲመልሱ ለመምህራን ቢጠቅም)፡፡
6. በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ለተማሪቹ ፍላጎት ተስማሚ ናቸው ቢባልም በህትመት ምክንያት የምንባቦቹ አጻጻፍ (ቅርጽ) ለእይታ ግልጽ አለመሆን፣ የቀለም መብዛትን የመሳሰለው የመማር ፍላጎትን ከሚቀንሱ ጉዳዮች ውስጥ የሚካተት በመሆኑ የሚስተካከልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡
7. ተማሪዎች መጽሐፋቸውን ይዘው የሚመጡበት ሁኔታ በመምህራንና በትምህርት ቤቶች አስተዳደር ቢታሰብበት የተሻለ ይሆናል፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች


ሰለሞን ተሰማ፡፡ (1995)፡፡ ‹‹ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸው፡፡›› ከጥቅምት 25-29/1995 ዓ.ም. ለአማርኛ እንደሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ (ከ/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት) አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋዬ ሸዋዬ ፡፡ (1981) ፡፡ ‹‹ስነልሳንና ቋንቋን ማስተማር›› አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ (ያልታተመ)፡፡

ተሾመ ፎርሲዶ ፡፡ (1997) ፡፡ ‹‹በከምባታ ጠንባሮ ዞን የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውና የማንበብ ፍጥነታቸው ፡፡›› ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ሚሚያ የቀረበ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ (ያልታተመ) ፡፡

አለም እሸቱ ፡፡ (1995)፡፡ ‹‹በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር ፡፡›› ከጥቅምት 25-29/1995 ዓ.ም. ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ (ከ/ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት) አዲስ አበባ ፣ (ያልታተመ) ፡፡

________ና ፅጌ አበበ (አሻሻዮች)፡፡ (1997)፡፡ አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ ዘጠነኛ ክፍል፡፡ ተሻሽሎ የወጣ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡

ወንድወሰን አዳነ ፡፡ (1995) ፡፡ ‹‹አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ፋይዳ ፣ አመራረጥና አደረጃጀት ፡፡››አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የተቀረጹትን የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶች ለማሻሻል በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ ፡፡ (ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት ፣ አዲስ አበባ፣ (ያልታተመ) ፡፡

ጌታቸው አዱኛ ፡፡ (1986) ፡፡ ‹‹ለአስረኛ ክፍል የተመረጡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ምንባቦች ብቃት ደረጃ ፡፡›› ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ሚሚያ የቀረበ ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፣ (ያልታተመ)፡፡

------------፡፡ (1995) ፡፡ ‹‹የሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ ማስተማሪያ መሣሪያ አዘገጃጀትና አጠቃቀም ፡፡›› ከጥቅምት 25-29/1995 ዓ.ም. ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጁ የ7ኛ ና የ8ኛ ክፍሎች መርሃ ትምህርቶችን ለማሻሻል

ለተዘጋጀው አውደ ጥናት የቀረበ (ከሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ኢንስቲትዩት/ አዲስ አበባ ፤ (ያልታተመ) ::

Aebersold, J.A. and M.L. Field, (1997). **From Reader to Reading Teacher Issues and Strategies for Second Language Classrooms.** Cambridge: Cambridge University Press.

Athkins, J. et-al (1995). **Skill development Methodology (Part 2).** Addis Ababa: Addis Ababa University.

Bright, J. McGregor. (1981). **Teaching English as a second Language.** Harlow: Longman Group Ltd.

Byrne, D. (1988) **Teaching Writing Skills**. Singapore: Longman Group Ltd.

Celce-Murcia, M.(eds.) (1991). **Teaching English as a Second or Foreign Language (2nd ed).** Bosten: Hinle and Hinle Publisher Ltd.

Cunningsworth, A. (1984). **Evaluation and selecting ELT teaching materials.** London: Heinemann International.

________(1995). **Choosing Your Course Book**. Oxford: Heinemann Publisher.

David, A. (2005). **Reading Skills in English.** Delhi: Common-wealth publishers.

Davies, F. (1995). **Introducing Reading.** London: Penguin Group.

Day, R. and Bamford, J. (1998). **Extensive Reading in the Second Language Classroom.** New York: Cambirdge University Press.

________ (20002) "Reaching Reluctant Readers". **English Teaching Forum.** Vol. 38. Number 3 PP. 12-17.

Dubin, F. and D. Bycina (1991). "Academic reading and the ESL/EFL teachers." In celce-Murcia Mariliana. (ed.) **Teaching English as a Second or Foreign Language.** Bosten: Heinle and Heinle Publisher. PP. 195-208.

_______and E.Olshtain (1986). **Course Design**. Cambridge: Cambridge University Press.

Gough, P. Hover, W. And Peterson, C. (1996). "Some Observations On a Simple View of Reading." In Cornoldi, C. and Oakhill, J. (eds.) **Reading Comprehension Difficulties: Process and Intervention.** New Jersey: Lawrence Erlbaum Associates, Inc. PP. 1-13.

Grant, N. (1987). **Making Most out of your text book**. New yourk: Longman.

Grellet, F. (1981). **Developing Reading Skills: A practical Guide to Reading Comprehensive Exercises**. Cambridge: Cambridge University press.

Greenwood, J. (1981) " Comprehensiion and Reading" In Abbott, G. and Wingard, P. (eds.) **Teaching of English as an International Language: A practical Guide**. Oxford: OXford University Press.

Harmer, J. (1991). **The Practice of English Language Teaching**. London: Longman Group (UK) Limited.

_________(2001). **The Practice of English Language Teaching**. Cambridge: Cambridge Pearson Educational

Harris, A. and Sipay, E. (1990). **How to increase Reading Ability: A guide to Developmental and Remedial Methods**. London: Longman Group Ltd.

Hutchinson, T. and Eunice Torres (1994). " The text book as Agent of change" **ELT journal**. Vol.48.No.4.pp.315-328.

_______, and Waters (1987). **English for specific Purposes: A learning centered approach**. New York: Cambridge University Press.

Johnson, P. (1982). "Effects on Reading Comprehension of Building Background Knowledge." **TESOL Quarterly** 16:4,503-516.

Larsen –Freeman, D. (1986). **Techniques and Principles in Language Teaching.** Oxford: Oxford University Press.

Lindsay and Knight (2006). **Learning and Teaching English**. Oxford: Oxford University Press

Marani, S.D. (1997). **Human Development And Reading Instruction.** Massachussettes: Educators Publishing Service, Inc.

McDonough, J. and Ch. Shaw (1993). **Materials and Methods in ELT**. Cambridge: Black well Publisher Ltd.

________(2003). **Materials and Methods in ELT**. Oxford; Oxford University Press.

Mei-yun, Yue. (1997). "Teaching Efficient EFL" in Karal, T. (ed.) **Teacher Development: Making the Right Moves.** Washington, D.C: United States Information Agency.

Nunan, D. (1988). **Syllabus design**. Oxford: Oxford University Press

Nuttall, C. (1982). **Teaching Reading Skills in A Foreign Language**. London: Heinemann Educational Books Ltd.

________(2000). **Teaching Reading Skills for in A Foreign Language**. London: Heinemann educational Books.

O'neill, R. (January 1982). "Why use Textbooks?" **ELT Journal**. Vol.36, No, 2, pp.104-111.

Papalia, Anthony (1987). "Interaction of reader and text." In Rivers, W.M. (ed.) **Interactive Language Teaching.** Cambridge: Cambridge University Press.

Silberstein, S. (1994). **Techniques and Resources in Teaching Reading**. Oxford: Oxford University Press.

Sheldon L.E. (ed.) (1987) **ELT Textbooks and materials Problems in Evaluation and development** . London, Oxford University Press.



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

Sheng, H.J. (2000). "A cognitive Model for Teaching Reading Comprehenstion" in **The English Teaching Forum**. Vol.38, Num.4.pp.12-15.

Smith, F. (1985). **Reading**. Cambridge: Cambridge University Press.

Stern, H.H. (1983). **Fundamental Concepts of Language Teaching**. Hong Kong: Oxford University Press.

_______(1992). **Issues and Options in Language Teaching.** Oxford University Press.

Tomlinson, B. (2004). **Materials Development in Language Teaching**. Cambridge University Press.

Ur, p. (1996). **A course in Language Teaching: practice and Theory.** Cambridge: Cambridge University Press.

Wallace, C. (1992). **Reading.** Oxford: Oxfored University Press.

Widdowson, H. G. (1978). **Teaching Language as Communication**. Oxford: Oxford University Press

Wiener, H.S. and Bazerrnan, C. (1997). **Reading Skills Hand Book.** (7th ed.) Boston and New York: Houghton Mifflin Company.

Williams, E. (1990). **Reading in the Classroom**. London: McMillan Publishers, Ltd.

Zhenyu, Z. (1997). "Intensive Reading: Getting your students to See the Forest as well as the Trees." **English Teaching Forum.** Vol. 35, No. 1, PP. 40-43.

# አባሪዎች

## ቅድመ ንባብ የመወያያ ነጥቦች

1. ተደራሲ ማለት ምን ማለት ነው?
2. አንድ ጸሐፊ የሚያዘጋጀውን ጽሑፍ ሌሎች እንዲያነቡለት ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?

## የንባብን ስሜት መቀስቀስ

ጸሐፊ ተጨንቆና ተጠቦ የድርሰት አጻጻፍ ሥርዓትና ህግጋትን ጠብቆ አንድ የጽሑፍ ሥራ ያዘጋጃል። ነገር ግን ያዘጋጀው ጽሑፍ የአንባቢን የንባብ ስሜት የማይቀሰቅስ ከሆነ አድራሻ እንደሌለው ደብዳቤ ተቀባይ በማጣት የያዘውን እንደያዘ ይቀራል። ስለዚህ የንባብን ስሜት ወይም ፍላጐት ለመቀስቀስና አንባቢ እጅ ገብቶ እንዲነበብና መልእክቱ እንዲጣጣም ታስቦ የሚቀርብ ጽሑፍ ከሁሉ አስቀድሞ የአንባቢን የንባብ ስሜትና ፍላጐት ወጥሮ እንዲይዝና ስሜቱን ኮርኩሮ እንዲያነቃቃው ተደርጐ መዘጋጀት አለበት።

ጸሐፊ አንድ ጽሑፍ ለማዘጋጀት በሚነሳበት ጊዜ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሱን መጠየቅ አለበት። የጽሑፌ አንባቢ ምን አይነት ሰው ነው? እድሜው ምን ያህል ነው? ሙያውስ? የትምህርት ደረጃውና የኑሮ አቋሙ ምን አይነት ነው? ለምስነዘረው ሀሳብ ምን አይነት ግምት ይኖረው ይሆን?የቋንቋዬ አጠቃቀም፣ የአረፍተ ነገሮቼ አሰካክ፣ የአንቀጾቼ አደራደር ሀሳቤን በግልፅ ያስተላልፉ-ሉ? ወዘተ.

ጸሐፊ እነዚህንና ሌሎች ተመሣሣይ ጥያቄዎችን ራሱን በመጠየቅ በጽሑፉ ላይ የሚያሰፍረው ሃሳብ በሁነኛ መልሶች ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል። እንዲሁም አንድ ጸሐፊ ሃሳቡ እንዲሳካለት ከፈለገ የተደራሲያኑን አጠቃላይ ፍላጐት ለማሟላት የተቻለውን ጥናትና ምርምር ከማድረግ መቦዘን የለበትም። እዚህ ላይ ጸሐፊው የአንባቢዎቹን ፍላጐት እንዴት አድርጐ

የጥበብን ዘር የሚያበራይ
በፀሀይ ኮከብ በጨረቃ
በብርሀን አክሊል ምጡቅ ሲቃ
በኡራኑስ ቀለበት ሰፊ ሀገር
በብእር ጫፍ ተወርውሮ፣ የሚሳደር
በክንፈቱ በምጥቀቱ
ጨረቃ ቀንታ እንባ እያነቃት
ፀሀይ ለንቦጭዋን ስትጥል
የራሱ ተሞጋሽ ቅኔ ምንጭ
የራሱ ሙሽራ ቅምጥል
እንደልጃገረድ ሚስቱ
እንደሚያኩራት ታውቃለች
የጫጉላ ቀን ቅኔዋን
ከእርሱ ትጠብቃለች
መልኳን የውብቷን ድንበር
    የሚኩለው
እርሱ ነውና አዝማሪዋ
ሊያቀማጥላት የታደለው
ለፍስሀ ቀን ብቻ ሳይሆን
ለእምባም ቀን ተድላ አለው
    ያ...ደራሲ.

(ደረጀ በሳይነህ፣ ብቤን፣ 1997፣ በከፊል የተወሰደ)

## መልመጃዎች

### አንድ:- አንብቦ መረዳት

*ግጥሙን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።*

. ግጥሙ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድነው?

# የቤተ መፃሕፍት አጠቃቀም መመሪያ

ቤተመፃህፍት ከተለያዩ የእውቀት ዘርፎች ላይ የተፃፉ መፃህፍት በሥርዓት ተዘጋጅተው የሚከማቹበት የእውቀት ማዕከል ነው።

የቤተመፃህፍትን አጠቃቀም ለማወቅ የትምህርት ቤታችሁን የቤተመፃህፍት ሠራተኞች አነጋግሩ። የምትፈልጉትን መጽሐፍ እንዲያ ወጡ ከመጠየቃችሁ በፊት በቤተመፃሕፍት በሚዘጋጁ ተሳቢ ሳጥኖች (ካቶሎግ) ውስጥ በፊደል ተራ ከሚቀመጡ ካርዶች ላይ ለየመጽሐፉ የተሰጠውን መለያ ቁጥር እንዴት ፈልጋችሁ ማግኘት እንደም ትችሉ ያስረዳችኋል።

1. የቤተመፃህፍት ሥነ ሥርዓት
   1.1. በፀጥታ መሥራት
   1.2. የግል መፃህፍትን ወደቤተመፃህፍት ይዞ አለማግባት
   1.3. በመፃህፍቱ በተገቢው መልክ መገልገል ወዘተ.
2. መፃህፍትን በአይነታቸው መለየት እንዲቻል የመፃሕፍት መለያ ደንቦችን በመከተል በመደርደሪያዎች ላይ እንዴት ተለይተው እንደተቀመጡ አስተውሉ።
3. መፃህፍት በቤተመፃህፍት ውስጥ በሚከተሉት ዝርዝር ካርዶች ተመዝግበው በፊደል ተራ ወይም በመለያ ቁጥር ተራ ገብተው ይቀመጣሉ።
   3.1. በደራሲ ስም
   3.2. በአርዕስት (በመጽሐፍ ስም)
   3.3. በይዘት (በዕውቀት ዘርፍ)
4. የካርዶች አይነትና አገልግሎት
   4.1. የደራሲ ካርድ፡- የደራሲው ስም በካርድ ራስጌ በመጀመሪያው መስመር ላይ ይገኛል።



# መልመጃዎች

## ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

፩. በምንባቡ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

ሀ. ባለታሪኳን «ግትር» ያሰኟት ሁለት ዐበይት ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው?

ለ. የባለታሪኳ እናት ለባለታሪኳ ያወረሷት ምንድን ነው?

ሐ. ባለታሪኳን «አብዛኛዎቹ ወንዶች» የሚያሳድዋቸው ናቸው በማለት የጠቀሰቻቸውን ባህሪያት ዘርዝሩ።

መ. አንዳንድ ሴቶች ቀንጆ የሆነች ጓደኛ እንድትኖራቸው የሚጥሩት ለምን ዓላማ ነው?

ሠ. «የኔ ጓደኞች የሚኖሩት ለብር ስለብር ነው» በሚለው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ብር የሚለው ቃል ለምን የተደጋገመ ይመስላችኋል?

ረ. «በእኔ እምነትና ሕይወት ውስጥ ይገቡና» ማለት ምን ማለት ነው?

፪. በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃሎችና ሐረጎች ፍቺ በማያዛቡ ሌሎች ቃሎችና ሐረጎች ተክታችሁ ተናገሩ።

ሀ. ከፊል ፀባዬ የተወረሰው ከሷ መሆኑን አልክድም።

ለ. እናቱ ከዓላማዋ ፍንክች የማትል ሴት ነበረች።

ሐ. ወንዶች ውብትሽ አልኪረግፍ ድረስ ሊጠቀሙብሽ ይችላሉ።

መ. ለሚያቅልሽ ሁሉ ላለመረታት ቀጠንቀቂ።

ሠ. ከዚህ ድፁ ጋር እንዴት ትጎዳኛለሽ?

# አባሪ ሁለት

| | | | የምንባብ ቅደም ተከተል፣ መገኛ ገጽ የመልመጃ ቁጥር ፣ የጥ. ብዛት | ድምር | መቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀጥተኛ ምላሽ የሚሹ ጥያቄዎች | በቃል/በንግግር/ የሚመለሱ | | 3፣21፣ ፩ ፣ 8 9፣74፣--*- ፣5<br>4፣29፣፪ ፣5 11፣91፣--*--፣5<br>5፣34፣፩፣10 13፣115፣፩፣6<br>6፣43-44፣፩፣5 | 44 | 19.13 |
| | በጽሁፍ የሚመለሱ | | 7፣51፣፩ ፣ 7 | 7 | 3.04 |
| | በምን እንደሚመለስ ያልተገለጸ | አስረዱ | 1፣2፣፩ ፣4 10፣82፣--*--፣8<br>8፣63፣፩ ፣10 | 22 | 9.57 |
| | | ምርጫ | 1፣3፣፪፣5 14፣128፣ ፫ ፣4<br>12፣101-102፣ሀ*፣7 | 16 | 6.96 |
| | ድምር | | | 89 | 38.7 |
| በራስ አገላለጽ የሚመለሱ ጥያቄዎች | በቃል የሚመለሱ | | 4፣28፣፩፣ 5 | 5 | 2.17 |
| | በጽሁፍ የሚመለሱ | | 5፣35 ፬፣10 | 10 | 4.35 |
| | በቃል ወይም በጽሁፍ | | 2፣8፣፫፣4 | 4 | 1.74 |
| | ድምር | | | 19 | 8.26 |
| አውዳዊ መልስ የሚጋብዙ ጥያቄዎች | በቃል የሚመለሱ | | 2፣7፣፩፣10 13፣115፣፪ ፣ 5<br>6፣44፣፪፣5 | 20 | 8.69 |
| | በጽሁፍ የሚመለሱ | | ---------------------- | --------- | -------- |
| | በምን እንደሚመለሱ ያልተገለጹ | አዛምድ | 2፣8 ፣፪ 6 14፣127፣፩ ፣5<br>3፣22፣ ፫፣5 15፣ 134፣ ፪፣ 5<br>5፣34፣-35፣ ፪፣10 | 31 | 13.48 |
| | | አገባባዊ ፍች ስጡ /ተከ/ | 3፣21-22፣፪፣9 12፣102፣ለ*፣6<br>5፣35፣፫፣10 15፣135፣ ፫፣6<br>7፣52፣፪፣9 15፣135፣፬ ፣ 5<br>8፣63፣፪ ፣9 | 54 | 23.48 |
| | ድምር | | | 105 | 45.65 |
| የማምገማ ጥያቄዎች | ---------------<br>--------------- | | ----------------------<br>---------------------- | ---------<br>--------- | --------<br>-------- |
| የማስታወስና የማገናዘብ ጥያቄዎች | በቃል የሚመለሱ | | 14፣127-128፣ ፪፣7 15፣134፣ ፩፣ 7 | 14 | 6.09 |
| | በጽሁፍ የሚመለሱ | | 7፣52፣፫ ፣ 3 | 3 | 1.30 |
| | በምን እንደሚመለሱ ያልተገለጹ | | --------------------<br>-------------------- | ------<br>------ | -----<br>----- |
| | ድምር | | | 17 | 7.39 |
| | አጠቃላይ ድምር | | | 230 | 100 |

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል የድህረምረቃ መርሀ ግብር

በ2000 ዓ.ም በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደርና በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሚገኙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ::

ውድ መምህር:-

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ያለውን አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ አስመልክቶ ከመምህራን መረጃ መሰብሰብ ነው:: እርስዎ ይህን መጠይቅ እንዲሞሉ የተፈለጉትም ለጥናቱ የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ላቅ ያለ መሆኑን በመገንዘብ ነው:: ስለሆነም ጥናቱ የተሳካ እንዲሆን ጥያቄዎቹን በግልጽነት እንዲመልሱለት አጥኚው በትህትና ይጠይቃል ::ለቀና ትብብሮም በቅድሚያ ያመሰግንዎታል ::

**መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም::**

I. አጠቃላይ መረጃ

1. የት/ቤቱ ስም ______________________
2. ፆታ ______________________
3. የትምህርት ደረጃ ______________________
4. የሰለጠኑበት የትምህርት ዓይነት ______________________
5. የአገልግሎት ዘመን ______________________
6. የሚያስተምሩበት የክፍል ደረጃ ______________________

## II. አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብን አስመልክቶ የቀረቡ ጥያቆዎች መመሪያ

ለእያንዳንዱ ጥያቄ በመልስነት ሊቀርቡ ይችላሉ ተብለው የታሰቡ አምስት አማራጮች አሉ:: እነሱም በጣም ከፍተኛ፤ከፍተኛ መካከለኛ፤ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ የሚሉት ሲሆኑ ትክክል ነው የሚሉትን በጥያቄው ፊት ለፊት ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ በመልሱ አቅጣጫ የ«X» ምልክት በማድረግ ያመልክቱ::

| ተ.ቁ. | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የምንባቦቹ ርዕሶች የተማሪውን የማንበብ ፍላጎት የማነቃቃት ደረጃ | | | | | |
| 2 | ተማሪዎች የአማርኛን ቋንቋ መጽሐፍ ይዘው ወደ ክፍል የሚመጡበት ጊዜ | | | | | |
| 3 | ምንባቦቹ ያላቸውን አጓጊነትና ሌሎች የአማርኛ ጽሑፎችን እንዲያነቡ ፍላጎት የማሳደር ደረጃ | | | | | |
| 4 | የምንባቦቹ ርዝመት ለተማሪዎቹ ፍላጎት ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 5 | ምንባቦቹ ተማሪዎችን ለማስደሰት ያላቸው ብቃት | | | | | |
| 6 | በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች ለተማሪው የቋንቋ ልምድ ያላቸው ቀረቤታ | | | | | |
| 7 | ምንባቦቹ ለተማሪዎች ዕድሜና አካባቢ ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 8 | በምንባቦቹ ውስጥ የሚገኙት ቃላት ከአካባቢው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 9 | የምንባቦቹ አረፍተ ነገሮች ግልጽነት | | | | | |
| 10 | የምንባቦቹ አጻጻፍ (ቅርጽ) ለእይታ ያለው ግልጽነት | | | | | |
| 11 | ምንባቦቹ የሚያስተላልፏቸው መልእክቶች የግልጽነት ደረጃ | | | | | |
| 12 | ምንባቦቹ የተሟላ (ቁንጽል ያልሆነ) ግልጽ መልክእት ለማስተላለፍ ያላቸው ብቃት | | | | | |
| 13 | ምንባቦቹ የቋንቋውን ዓላማ ለማሳካት ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 14 | የምንባቦቹ የቋንቋ አጠቃቀም በአካባቢው ዕለት ተዕለት አገልግሎት ላይ ከሚውለው አጠቃቀም ጋር ያለው ተስማሚነት | | | | | |
| 15 | ምንባቦቹ የቋንቋን ሥርዓት የመጠበቅ ብቃታቸው | | | | | |
| 16 | ምንባቦቹ በአካባቢው እንደልብ የመገኘታቸው (መጽሐፉ ለሁሉም ተማሪዎች) የመዳረሱ ደረጃ | | | | | |
| 17 | ምንባቦቹ አዳዲስ ነገሮችን (የቃላትን አገባብ) የማስተማር ብቃታቸው | | | | | |
| 18 | ከምንባቦቹ የሚገኙት ዕውቀቶች በተፈለገው ቦታና ጊዜ ያላቸው ተተግባሪነት | | | | | |
| 19 | የምንባቦቹ ይዘቶች ያላቸው ወቅታዊነት | | | | | |
| 20 | የምንባቦቹ የክብደት ደረጃ (የሐብ ጥልቀት) ምን ያህል ነው? | | | | | |
| 21 | የምንባቦቹ ይዘቶች ከቀላል ወይም ከሚታወቀው ጀምረው ወደማይታወቀው እያደረጉ የመሄድ ደረጃቸው | | | | | |
| 22 | ምንባቦቹ ከተለያዩ የጽሑፍ አይነቶች (ረጅምና አጭር ልቦለድ፣ ጭውውቶች፣ ግጥሞች፣ ወዘተ.) የተውጣጡበት ደረጃ | | | | | |
| 23 | ምንባቦቹ የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን እንደ ምሳሌያዊ፣ ፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊ አነጋገር ያሉትን የያዙበት ደረጃ | | | | | |
| 24 | ምንባቦቹ እደመጻፍ፣ መናገር ወዘተ. ያሉ የተለያዩ ክሂሎችን ለማስተማር ያላቸው ብቃት | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | ምንባቦቹ ከመነበባቸው በፊት የሚቀርቡ (ቅድመ ንባብ) የመወያያ ጥያቄዎች የሚገኙበት ደረጃ | | | | | |
| 26 | በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር ያላቸው ተገቢነት | | | | | |
| 27 | ከምንባቡ የወጡት መልመጃዎች ምንባቡን ባላነበበ ተማሪ ሊመለሱ የመቻላቸው ሁኔታ | | | | | |
| 28 | የመልመጃዎቹና የትዕዛዞቹ ግልጽነትና ትክክለኛነት | | | | | |
| 30 | አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አውዳዊ ፍችን ለማገናዘብ ያላቸው እገዛ | | | | | |
| 31 | በምንባቦቹ ውስጥ ያሉትን አያያዥ ቃላት ያካተቱ መልመጃዎች የሚገኙበት ሁኔታ | | | | | |
| 32 | በምንባቦቹ ውስጥ ባሉ አረፍተ ነገሮች መካከል ስላሉ ዝምድናዎች የሚጠይቁ ጥያቄዎች | | | | | |
| 33 | ተማሪዎቹ የምንባቦቹን ሐሳቦች ገምግመው በጽሑፍም ሆነ በቃል በማቅረብ የሚያወያዩ ወይም የሚያከራክሩ ጥያቄዎች የሚገኙበት ደረጃ | | | | | |
| 34 | ስለምንባቦቹ የሚጠይቁት መልመጃዎች የተጻፉበት ቋንቋ ምንባቦቹ ከተጻፉበት ቋንቋ | | | | | |
| 35 | አንብቦ የመረዳት ትምህርቱ ለደረጃዉ ያለው ተስማሚነት | | | | | |
| 36 | ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች አኳያ ሲታይ በመጽሐፉ ውስጥ ለአንብቦ መረዳት የተሰጠው ቦታ | | | | | |

37. በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 3.7 ከምንባቦቹ የወጡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንባቦቹን ደጋጋሚ እንዳነብ የማድረግ ደረጃውስጥ የቀረበውን አንብቦ የመረዳት ትምህርት አስመልክቶ ያልተነሳ (አንብቦ የመረዳትን ትምህርት ይጎዳል ወይም ይጠቅማል) የሚሉት ሐሳብ ካለ በአጭር በአጭሩ በተሰጡት ቦታዎች ላይ ያስፍሩ፡፡

ሀ. ____________________

ለ. ____________________

ሐ. ____________________

መ. ____________________

# አባሪ አራት

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል
## የድህረ-ምረቃ መርሀ ግብር

በ2000 ዓ.ም. በድሬዳዋ ከተማና በሐረር ከተማ በሚገኙ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች 9ኛ ክፍል በሚማሩ ተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ።

ውድ ተማሪዎች፡ -

የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አንብቦ የመረዳት ትምህርት የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማዳበር በተገቢ መንገድ ሙቅረብ አለመቅረቡን ለማወቅና የመፍትሄ ሀሳብ ለመሰንዘር ለታቀደ ጥናት መረጃ መሰብሰብ ነው።

ጥናቱ የታሰበውን ግብ እንዲመታ በመጠይቁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጥሞና በማንበብ ትክክለኛ ናቸው የምትሉዋቸውን መልሶች እንድትሞሉ፣ አጥኚው ይጠይቃል። ለሚደረግለት ቀና ትብብርም በቅድሚያ ያመሰግናችኋል።

ማሳሰቢያ፡ - መጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም

i. አጠቃላይ መረጃዎች

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ክፍት ቦታዎች በትክክለኛ መረጃዎች ይሙሉ።

1. ፆታ______________________________________
2. ዕድሜ_____________________________________
3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ______________________________

ii. አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች መመሪያ

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አምስት አማራጭ መልሶች መካከል ትክክል ነው ለምትሉት በአቅጣጫው የ "X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ፡፡

| | ጥያቄዎች | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ምንባቦቹ ለተማሪዎች ፍላጎት፣ ችሎታ... ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የምንባቦች ርዕሶች ምንባቦቹን እንድናነብ ያላቸው የማነቃቃት ሀይል፡፡ | | | | | |
| 2 | የአማርኛ ክፍለ ጊዜ ባለን ቀን መጽሀፉን ይዤ ለመምጣት ያለኝ ፍላጎት | | | | | |
| 3 | ምንባቦቹ ያላቸው አጓጊነትና ሌሎች የአማርኛ ጽሁፎችን እንዳነብ ያሳደሩብኝ ፍላጎት | | | | | |
| 4 | በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ በትርፍ ጊዜዬ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሉትን ምንባቦች የማነብበት ወቅት | | | | | |
| 5 | የምንባቦቹ ርዝመት ለደረጃው ያላቸው ተገቢነት | | | | | |
| 6 | በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ከችሎታዬ ጋር ያላቸው ስምምነት | | | | | |
| 7 | የምንባቦቹ የሐሳብ ግልጽነት፣ ምሳሌ አሰጣጥ ከችሎታዬ ጋር ያላቸው መስማማት | | | | | |
| 8 | ምንባቦቹ ከአካባቢው እንደልብ የመገኘታቸው ሁኔታ | | | | | |
| 9 | ምንባቦቹ በውስጣቸው የተሰጡት ምሳሌዎች ከአካባቢዬና ከእድሜዬ ጋር ያላቸው ተዛምዶ | | | | | |
| 10 | ምንባቦቹን በአካባቢው ካለው ህብረተሰብ ባህል ጋር ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 11 | ምንባቦቹ እስከ ዛሬ ካለኝ ልምድና በአካባቢዬ ከማያቸው፣ ከምሰማቸውና ከማውቃቸው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር ያላቸው ተዛምዶ | | | | | |
| 12 | የምንባቦቹ አጻጻፍ ወይም ቅርጽ ለእይታ ያላቸው ግልጽነት | | | | | |
| 13 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች የሚገልጿቸው መልእክቶች ግልጽነትና ወቅታዊነት | | | | | |
| 14 | በመጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ላለሁበት ዕድሜ ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 15 | በምንባቦቹ ውስጥ የሚገኙት ቃላት ከአካባቢው የቋንቋ አጠቃቀም ጋር ያላቸው ተስማሚነት | | | | | |
| 16 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች የክብደት ደረጃ | | | | | |
| 17 | በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች የተለያዩ ይዘቶች (ረጅምና አጭር ልቦለድ፣ ቀልዶች፣ ግጥሞች ወዘተ.) የተካተቱባቸው ደረጃ | | | | | |
| 18 | ምንባቦቹ የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምባቸውን እንደ ምሳሌያዊ፣ ፈሊጣዊ፣ ዘይቤያዊ አነጋገር ያሉትን የያዙበት ደረጃ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች የመስራት ፍላጎቴ | | | | | |
| 20 | መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች ከማንበባችን በፊት የቀረቡ ስለምንባቡ የሚያወያዩ ጥያቄዎች | | | | | |
| 21 | ስለምንባቦቹ የሚጠይቁት መልመጃዎች የተጻፉበት ቋንቋ ምንባቦቹ ከተጻፉበት ቋንቋ ጋር በክብደት ያላቸው መቀራረብ | | | | | |
| 22 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ምንባቦች አንብቤ መልመጃዎችን ለመስራት ያለኝ መነቃቃት | | | | | |
| 23 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት ምንባቦች ሳይነበቡ ከምንባቦቹ የወጡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ያለው ዕድል | | | | | |
| 24 | የመልመጃዎችቹ ትእዛዞች ግልጽነት | | | | | |
| 25 | ከምንባቦቹ የወጡትን ጥያቄዎች ለመመለስ ምንባቦቹን ደጋግሜ እንዳነብ የማድረግ ደረጃ | | | | | |
| 26 | ከምንባቦቹ ከወጡት ጥያቄዎች ውስጥ አንብባችሁ የተረዳችሁትን በጽሑፍ እንድትመልሱ የሚጠይቁ ጥያቄዎች ብዛት | | | | | |

ADDIS ABABA UNIVERSITY ILS LIBRARY

# ዲክላራሲዮን

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት ተማሪ ይህ ጥናት የራሴ ሥራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ጽሑፎች ምንጮች በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡ - የሺጥላ ምንይልሸዋ

ፊርማ፡ ____________

አድራሻ፡ - አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ

የማስረከቢያ ቀን፡ - 16/10/2000 ዓ.ም.